DISTRICT OF COLUMBIA
DEPARTMENT OF MOTOR VEHICLES

የመንዳት(የአሽከርካሪዎች) ማንዋል



ወደ የጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎች ደህንነት የሚያደርስ የ“ራዕይ ዜሮ” አኪያሄድ

ዲስትሪክቱ በከተማው ጎዳናዎች ላይ የሚጓዙትን ሁሉ ህይወት ለመከላከል ቆራጥ ነው። ራዕይ ዜሮ፣ ከተማው ጎዳና ላይ በተሽከርካሪዎች ምንክያት የሚደርሰውን ሞት ወደ ዜሮ ለመቀነስ ያለውን ግብ ይወክላል። በጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎች ምክንያት የሚደርሰውን ሞት እና ከፍተኛ አደጋዎች ልንከላከላቸው የምንችለው ነው።

“ራዕይ ዚሮ” ምንድን ነው?
“ራዕይ ዚሮ” ምንም ሞት ወይም ከፍተኛ አደጋ የሌለበት የጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎች የህይዌይ ሲስተም ላይ ለመድረስ የታቀደ በርካታ ሀገሮችን ያካተተ የጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎች የደህንነት ፕሮጀክት ነው።
በ 1997 በሲውድን ተጀምሮ፣ በኖርዌይ፣ ዘ-ኔዘርላንድስ፣ እና ዩናይትድ ኪንግደም በአለም አቀፍ ደረጃ ተግባር ላይ እየዋለ ነው። እቅድ በማውጣት ሂደት ላይ ያሉ የዩ.ኤስ. ከተሞች ቦስተን፣ ቺካጎው፣ ሎስ አንጀለስ፣ ኒው ዮርክ ሲቲ፣ ፖርትላንድ፣ ሳን ፍራንሲስኮ፣ ሲያትል እና ዋሽንግተን ዲሲን ያካትታሉ።
የራዕዮ ዋናው መርህ ማንም ሰው በጎዳናው የተሽከርካሪዎች ሲስተም ላይ መሞት ወይም በከፍተኛ ደረጃ መጎዳት የለበትም የሚል ነው፤ እናም የአፈጻጸም እቅዶቹ በሚከተሉት ዋና ዋና ቁልፍ ዘርፎች ላይ የተገነቡ ናቸው፡

- የደህንነት ዴታ
- ማስተማር እና ህብረተሰቡን ማዳረስ
- ማስፈፀም
- ኢንጂነሪንግ እና መሰረተ-ልማት

“ራዕይ ዚሮ” ለምን?
የጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎች ለህይወት የሚያሰጉ ናቸው እና ዋሽንግተን ዲሲ ጎዳቶችን እና ሞትን የሚቀንስ ሁለገብ ፕሮግራም በመቅረጽ የጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎችን ደህንነት የሚያሻሽል ከፍተኛ ጉዳቶችን እና ሞትን ለመቀነስ እየሞከረ ነው። ማንኛውም የህይወት ማጣት ተቀባይነት የለውም እናም በዲስትሪክት ከተማው ጎዳናዎች ላይ አንድ ሞት ተቀባይነት የለውም!

በዲስትሪክቱ ውስጥ የተከናወኑት ነገሮች
የዲስትሪክቱ የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት (District Department of Transportation (DDOT))፣ ከህግ አስፈጻሚው፣ የፍትህ ሰራተኞች፣ የግል ተቋማት እና ለህብረተሰቡ መብት ተከራካሪዎች ጋር በጋራ በመስራት የዲስትሪክቱን የህይዌይ ደህንነት ፕሮግራም ለማቀናበር እና ስራ ለማካሄድ ተመድቧል። ዲዲኦቲ (DDOT) ዜሮ-ከትራፊክ ጋር የተገናኘ ሞት እና ዜሮ ከፍተኛ ጎዳት ያለበት ደህንነቱ የተጠበቀ እና ውጤታማ የትራንስፖርቴሽን ሲስተም ለመፍጠር ቁልፍ ከሆኑ ሽሪኮች ጋር ይሰራል። የዚህ አብይ ስራ ቁልፍ ተጨባጭ ተፈጻሚ ተግባሩ የትራፊክ ደህንነትን ለማሻሻል እና ሞትን ለመቀነስ አምስት

ወሳኝ የትኩረት መደቦችን (Critical Emphasis Areas (CEA's)) ለይቶ ያወጣው የዲሲ የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት የሀይዌይ ደህንነት ፕላን (DC Department of Transportation Highway Safety Plan) ነው።

እነዚህ አምስት መደቦች የሚከተሉት ናቸው:

- ከፍተኛ አደገኝነት(ሪስክ) ያላቸው ነጂዎች
- የእግረኞች እና የብስክሌቶች ደህንነት
- ኢንጂነሪንግ/የአገልግሎት ሰጪዎች መሰረተ-ልማት
- ልዮ ተሽከርካሪዎች
- ልዮ የኢላማ መደቦች

የጎዳና ላይ ተሽከርካሪዎችን ሞት የሚቀንስ ሀይለኛ የሆነ የስራ ግቦች እና ሁለገብ የተግባር እቅድ በመጠቀም፣ ዲስትሪክቱ ወደ ዜሮ ሞት የመድረስ ሙከራውን ለመጨመር እና መንገዶቹን ለሁሉም መንገድ ተጠቃሚዎች ደህንነትን የሚያሰጠብቅ እና አመቺ ለማድረግ ቆርጧል።

ደህንነት የተጠበቀ አነዳድ የሚገጥመው ተግዳሮት
ደህንነትን የሚያስጠብቅ ነጂ ለመሆን ብዙ ችሎታን ይፈልጋል፤ ልምድ፣ ሀላፊነት፣ እና ውሳኔን ይጠይቃል። ሰዎች ከሚያደርጓቸው ውስብስብ ነገሮች መሀከል አንዱ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ ሰዎች በመደበኛ ሁኔታ ከሚያደርጉት ሊጎዳ ከሚያደርስ እና ሊገድል ከሚችል ጥቂት ነገሮች መሀከል አንዱ ነው።

ደህንነት የሚያስጠብቅ አነዳድ አደጋዎችን አስቀድሞ የማየት ችሎታን እና ሌሎች ጥፋት ሲያጠፉ ማለፍን ይጠይቃል፣ በተለይም መገናኛ መንገዶች እና የእግረኛ መሻገሪያ ጋር ሲደርሱ። በተጨማሪም፣ ነጂዎች ለራሳቸው እና ለሌሎች ደህንነት ሲሉ ባጠቃላይ ጤነኛ የመሆን፣ ለመንዳት በስሜት ብቁ መሆን እና በመጠቀም ላይ ያሉት ተሽከርካሪ በጥሩ ሁኔታ የሚሰራ መሆኑን የማረጋገጥ ሀላፊነት አለባቸው። ነጂን እና የህብረተሰቡን ደህንነት ስጋት ውስጥ የሚጥሉት ሁለት የአደገኝነት መንስኤዎች ተዘናግቶ መንዳት እና በሌላ ነገር ተፅእኖ ላይ ሆኖ መንዳት ናቸው።

ተዘናግቶ መንዳት
ተዘናግቶ መንዳታ አደገኛ ወረርሽኝ ነው፣ እና ካሉት ከብዙዎች ትርጉሞች መሀከል የግለሰቡን ሀሳት ከዋናው ከመንዳት ስራው የሚሰርቅ ማንኛውም ተግባር ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። በየአመቱ 400,000 ሰዎች በተዘናጉ ነጂዎች በሚከሰት ግጭቶች ምክንያት ጉዳት ይደርስባቸዋል ተብሎ ይገመታል። እታች የተዘረዘሩት ነገሮች ያዘናጋሉ ብለን ላናስብ ብንችልም፣ ሁሉም መዘናጋቶች ነጂውን፣ ተሳፋሪውን፣ ብስኪሌቶችን እና የቆሙትን ሰዎች ደህንነት አደጋ ላይ እንደሚጥል ማሳሰቡ አስፈላጊ ነው።
በአብዛኛው የሚዘወተሩ መዘናጋቶች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- መብላት እና መጠጣት
- የእጅ ስልክ ወይም ስማርት ስልክ መጠቀም
- ቴክስት ማድረግ
- መቆነጃጀት(መሰናዳት)
- ማንበብ
- የናቪጌሽን ሲስተም መጠቀም
- ሬድዮ፣ ሲዲ መጫወቻን ወይም MP3 ማጫወቻን ማስተካከል
- ከተሳፋሪዎች ጋር ማውራት

ተጽእኖ ላይ ሆኖ መንዳት
በአልኮል፣ በሀጋዊ ወይም ህገ-ወጥ አደንዛዝ እጽ(ድራግ) እና በማንቀላፋት ተጽእኖ ላይ ሆኖ መንዳት ሁሉም በተጽእኖ ላይ ሆኖ መንዳት ተብለው የሚጠሩት አካሎች ናቸው። በተጹእኖ ላይ ሆኖ መንዳት እጅግ አደገኛ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ለሆነ የገንዘብ ቅጣት እና ለእስርም ጭምር ሊያመራ ይችላል። ጥናቶች በአልኮል ተጽእኖ ላይ ሆኖ መንዳት ከትራፊክ ጋር ከተዛመቱት ሞቶች አንድ ሶስተኛውን ገደማ እንደሚይዙ ፣እና አደንዛዝ እጾች(ድረጎች) ከትራፊክ ጋር የተያያዙ ሞት 18%ው ን እንደሚይዙ ያሳያሉ። ጥቂት ቁልፍ ነጥቦች :

- **የአልኮል ውጤት –** የደም የአልኮል መጠን (blood alcohol concentration (BAC)) ላይ ተጽእኖ የሚያደርጉ ነገሮች
    - በምን ያህል ፍጥነት እንደሚጠጡት
    - የሰውነት ክብደት
    - ሆድ ውስጥ ያለው ምግብ
    - የአልኮሉ ጥንካሬ(ኮንሰንትሬሽን)
    - መድሀኒቶች
    - ድካም፣ ጭንቀት እና ስሜት (ሙድ)

- **ደንዝዞ(እንቅልፍ እንቅልፍ እያለ) መንዳት –** በእንቅልፍ ማጣት ምክንያት ተጽእኖ ኖሮቦት የሞተር ተሽከርካሪን መንዳት። እንቅልፍ ማጣት የሞተር ተሽከርካሪዎች ግጭት ትልቅ ምክንያት ነው። ብዙ ሰዎች እንቅልፍ ማጣት መንዳት ላይ ያን ያህል ተጽእኖ እንዳለው አይገነዘቡም፣ አንዳንድ ግዜ ከአልኮልም በላይ ነው። “መስኮቶችን ወደታች ማውረድ ወይም ሙዚቃውን መጨመር” ንቃት ላይ የሚያመጡት ውጤት ጥቂት ወይም ምንም እንዳልሆነ ጥናቶች አረጋግጠዋል፣ ቡና እና ሌላ ካፌን ያላቸው ረዳት ነገሮች ሀይልን የሚጨምሩት ለአጭር ግዜ ብቻ እንደሆነ። ደንዝዞ መንዳትን ከሁሉ በተሻለ ሁኔታ ለመከላከል በቂ “እንቅልፍ” ማግኘት ከሁሉ የተሻለ ነው።

ነጂዎች በቂ እንቅልፍ ለማግኘት ሁልቀን ቅድሚያ መስጠት አለባቸው፣ እንቅልፍ ያጡ ግዜ ለመንዳት እንቢ ይበሉ፣ እና እንቅልፍ እንቅልፍ ካሎት ደህና ወደሆነ ቦት ከመንገዱ ይውጡ።

መንገዱን መጋራት

የሚነዱት መኪና ይሁን፣ ትራክ ይሁን፣ ኤስዩቪ ይሁን፣ የንግድ ተሽከርካሪ ይሁን፣ ሞተር ሳይክል ይሁን፣ ብስኪሌት ይሁን ወይም እየተራመዱ ይሁን መንገዱን ከሌሎች ሰዎች ጋር ይጋራሉ። መንገዱ ብዙ ተጠቃሚዎች አሉት እና ደህንነት መጠበቁን እና አግባብ ያለው የትራፊክ ፍሰት መኖሩን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ተጠቃሚዎች የተወሰኑ የጎዳና ላይ ደንቦችን፣ ህጉን አና መብቶችን መከተላቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

ነጂዎች

ብዙ ግዜ ስለነጂዎች ስናስብ፣ አውቶሞቢል የሚነዱ ግለሰቦችን ብቻ ነው ምናስበው። ነገር ግን፣ ትርጉሙ ብስኪሌቶችን፣ ባሶችን፣ ሞተርሳይክሎችን፣ ቀላል ትራኮችን፣ የንግድ ተሽከርካሪዎችን እና ማንኛውንም በሀዲድ ላይ የማይሰራ ማንኛውም ተሽከርካሪ እንዲያካትት ሆኖ መተርጎም አለበት። ይህንን ሰፊ ትርጉም መጠቀም የትራፊክ ደህንነት መጠንን እና የመንገዶች መጋራትን አስፈላጊነት በሰፊው ለማየት ይረዳል። በ 2013 ብቻ በዩናይትድ ስቴትስ 5.7 ሚሊዮን የሞተር ተሽከርካሪዎች ግጭቶች፣ ከ 32,000 በላይ ከሞተር ተሽከርካሪዎች ጋር የተዛመቱ ሞቶች እና 2.3 ሚሊዮን የተጎዱ ሰዎች ነበሩ። ነጂዎች ሁልግዜ የትራፊኩን ፍሰት እና አካባቢያቸውን እያጤኑ መወሰን ያለባቸውን ውሳኔዎች ቀድመው መተንበይ አለባቸው። ሲነዱ እና እታች ያሉትን የደህንነት ምክሮች ሲጠቀሙ ለባለብስኪሌቶች እና እግረኞች የተለየ ትኩረት ይስጡ።

- **የተሽከርካሪዎች ደህንነት ለባለብስኪሌቶች**
  - **ለብስኪሌቶች ቢያንስ 3 ጫማ ርቀት ይስጡ**
  - **በሮችን ከመክፈቶ በፊት ባለብስክሌቶችን ይመልከቱ**
  - **ሲታጠፉ ለባለብስክሌቶች ቅድሚያ ይስጡ**

- **የተሽከርካሪዎች ደህንነት ለእግረኞች**
  - **ሁልግዜ ቅድሚያ ይስጡ እና የማለፍን መብት ይስጡ**
  - **ሲታጠፉ ለእግረኞች ቅድሚያ ይስጡ**
  - **መገናኛዎች እና የእግረኛ መሻገሪያ ቦታዎች ጋር ሲደርሱ ጥንቃቄን ይውሰዱ**
  - **የእግረኛ መሻገሪያ ቦታዎች ጋር የቆመን ተሽከርካሪ በፍጹም አይለፉት**

እግረኞች

እግረኛ በእግር፣ በዊልቼር፣ በስትሮለር፣ እየተራመደ፣ እየሮጠ ወይም ዱብዱብ እያለ የሚጓዝ ማንኛውም ግለሰብ ተብሎ ሊተሮጎም ይችላል። በአማካኙ በዩኤስ እግረኛ በየ 2 ሰአቱ ይገደላል እና በየ 8 ደቂቃው በትራፊክ ግጭት ይጎዳል። እግረኞች በጎዳና ላይ ከሁሉም በይበልጥ ከሚጋለጡት ተጠቃሚዎች መሀከል ናቸው፤ ልጆች መጠናቸው ትንሽ ስለሆነ እና ስለትራፊክ ደንቦች ልምድ ስለሌላቸው በትራፊክ ግጭቶች ምክንያት ለሚመጣ ጉዳት እና ሞት በበለጠ አደጋ ላይ ናቸው። ማስታወስ ያለብን የእግረኞች ደህንነት ምክሮች:

- **መንገዶችን በእግረኛ መሻገሪያዎች እና መገናኛ መንገዶች ላይ ይሻገሩ**
- **በበለጠ የሚታዩ ይሁኑ እና ነጂዎች እንዳዩት እርግጠኛ ይሁኑ**
- **በእግረኛ መሄጃው ላይ መራመድ ከሁሉም ይልቅ ደህንነትን ያስጠብቃል**

ባለብስክሊቶች

በዩኤስ በየአመቱ በብስክሊት/ተሽከርካሪ ግጭቶች በአማካኝ ከ 700 ሰዎች በላይ ህይወታቸውን ያጣሉ። ይሄ በቀን ከሁለት ሰዎች በትንሽ የሚያንስ ማለት ይሆናል። በ 2013 ከ 66,000 በላይ የሚሆኑ ባለብስኪሌቶች በተሽከርካሪ ግጭቶች ተጎድተዋል። ብስክሌት መንዳት ጤናማ እና በተፈሮው ደህንነትን የሚያስጠብቅ ቢሆንም ብስኪሌት መንዳት እና መንገዱን ከሌሎች ተሽከርካሪዎች ጋር ከመጋራት ጋር አብሮ የሚመጣ አደጋዎች አሉ። ብስክሌቶች ከተሽከርካሪዎች ጋር ተመሳሳይ የጎዳና ላይ መብቶች አሉዋቸው፣ እና ደህንነት መጠበቁን ለማረጋገጥ ባለብስክሌቶች የሚከተሉትን ማድረግ አለባቸው:

- የመንገድ ላይ ደንቦችን ይከተሉ
- በቀይ መብራት ላይ እና የማቆሚያ ምልክቶች ላይ ያቁሙ
- ሁልግዜ የጭንቅላት መከላከያ ጡር (ሄልሜት) ያድርጉ
- መኪኖችን ሲያልፉ በመከፈት ላይ ላሉ በሮች ይጠንቀቁ
- በዳውንታውን አካባቢ በእግረኞች መሄጃ ላይ አይንዱ

በጥቅሉ፣ ራዕይ ዚሮ የነጂዎችን፣ የባለብስኪሌቶችን እና የእግረኞችን ጎዳናዎችን መጋራት እና የጎዳና ላይ ደንቦችን የመጠቀም ጥረት ይጠይቃል። በቅርቡ የዲስትሪክት ነጂ ሊሆኑ እንደመሆኖ መጠን፣ የሁላችንንም ደህንነት ለማስጠበቅ እርሶ የድርሻዎን ያደርጋሉ ብለን እየተማመንንቦት ነው!

ማውጫ

መግቢያ.....4

የመንጃ ፈቃድ ፈተና ሂደት.....5

የመንጃ ፈቃዶችና ሌሎች ፈቃዶች ዓይነቶች.....10

ሌሎች አገልግሎቶች.....14

መታወቅ ያለባቸው አስፈላጊ ነገሮች.....16

የነጂ (የአሽከርካሪ) መረጃ.....18

የማሽከርከር (የመንዳት) ደንቦች.....57

የማቆምያ (ፓርኪንግ) ደንቦች.....61

የትራፊክ ደንቦች.....65

ማሳያዎች/ሲግናሎች፣ምልክቶች እና ስላቶች/ማርኪንጎች.....72

ምልክቶችን በቀለማት እና በቅርፆች ስለመለየት.....76

የመቆጣጠሪያ ምልክቶች.....81

መግቢያ

ይህ ማኑዋል ሁሉም አሽከርካሪዎች ማወቅ የሚገባቸውን የደህንነት አነዳድ ደንቦችን እና አሰራሮችን የሚመለከት መረጃ ይሰጣል። ይህ ማኑዋል ሁሉን የመንዳት ዘርፎች ላይ መረጃ ይሰጣል። ማንዋሉን ሙሉ በሙሉ በጥንቃቄ ማንበብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። ይህንን ማኑዋል ካላነበቡ እና ካላጠኑ የዲሲ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት የሚያስፈልገውን የእውቀት ፈተና አያልፉም። ፈተናውን በሚፈተኑበት ወቅት ይህንን ማኑዋል እንዲያነቡ አይፈቀድልዎትም።

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በሚገኙ የሕዝብ መንገዶች ላይ አንድን ባለሞተር ተሽከርካሪ ወይም ሞተርሳይክልን የሚያንቀሳቅስ ማናቸውም ሰው የመንጃ ፈቃድ ሊኖረው ይገባል። ወደ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በነዋሪነት ከተዛወሩበት እለት ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ የዲሲ የመንጃ ፈቃድ ሊኖርዎ ይገባል።

በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት የዲሲ የመንጃ ፈቃድ ሊያገኙ ይችላሉ፡

- እድሜዎ ቢያንስ 17 ኣመት ከሆነ (የለማጅ ፈቃድ በ16 ኣመት)
- የህጋዊ ሙሉ ስም፣ የትውልድ ቀን፣ የሶሻል ሴኪሪቲ ቁጥር እና ሁለት(2) የዲሲ ነዋሪነት ማረጋገጫን ማቅረብ ከቻሉ፤
- የእውቀት ፈተናን፣ የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናን እና የማየት ግምገማን በስኬታማ ሁኔታ ካጠናቀቁ፣
- ከ18 አመት በታች ከሆኑ፣ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት(ኮንሰንት) ካሎት፤
- ከዚህ በፊት የነበሮት ማንኛውንም የመንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ወረቀት ካስረከቡ፣
- ፈቃዶ ታግዶ፣ ተሽሮ ወይም ተከልክሎ የማያውቅ ከነበረ፣
- የህክምና መስፈርቶቹን ካሟሉ፣
- ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ላይ ያልተከፈለ እዳ ወይም በሌላ ግዛቶች በመንቀሳቀስ ላይ የተገኘ የትራፊክ ጥሰት ያልተከፈለ የገንዘብ ቅጣት ከሌሎት።

ይህ ማኑዋል የንግድ ያልሆነ ተሽከርካሪዎችን (የተሳፋሪ መኪና) ለመንዳት የሚያስፈልጉትን መረጃ ይሰጣል። የንግድ ተሽከርካሪ ለመንዳት ፈቃድ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የንግድ ፈቃድ ማኑዋል (Commercial Driver License (CDL) Manual) ማንበብ እና ማጥናት ይኖርቦታል። ሞተርሳይክል ለመንዳት ፈቃድ ከፈለጉ፣ ከዚህ ማኑዋል በተጨማሪ የሞተር ሳይክል ማንቀሳቀሻ ማንዋልን (Motorcycle Operation Manual) ማንበብ አለቦት።

የመንጃ ፈቃድ ፈተና ሂደት

የነጂ የእውቀት ፈተና

የመንጃ ፈቃድ የእውቀት ፈተና በማንኛውም የዲኤምቪ አገልግሎት ማእከል ሊወሰድ ይችላል። ፈተናዎቹ በሚከተሉት ቋንቋዎች ይሰጡ ይችል ይሆናል፡

እንግሊዘኛ	አረብኛ
ስፓኒሽ	ፖርቹጊዝ
ፈረንሳይኛ	ጃፓንኛ
ቪየትናሚዝ	ራሻን
ማንዳሪን	ታጋሎግ
ኮሪያን	ካንቶኔዝ
አማርኛ	ታይ
ጀርመንኛ	

በተጨማሪም፣ ፈተናዎቹ በተች ስክሪን ምላሽ መስጫ፣ በድምጽ (ኦድዩ) እና በእይታ(ቪዝዋል) ሊቀርቡ ይችላሉ።

የመደበኛ ፈተናው በኮምፒተር ይሰጣል እና 25 ጥያቄዎች ይኖሩታል። የማለፊያ ነጥቡ ቢያንስ 20 ትክክል መልሶችን (80%) ያካትታል። በ 16 – 20 እድሜ መሀከል ከሆኑ፣ የተመረቀ የፈቃድ ፕሮግራም (Graduated Licensing Program) እንዲሁም የቀስ በቀስ አዋቂ ነጂዎችን ማሳደጊያ (ግራድ) GRAD (Gradual Rearing of Adult Drivers) ተብሎ የሚጠራው ፕሮግራም ላይ ይደረጋሉ። የግራድ(GRAD) ፈተናው በኮምፒተር የሚሰራ 30 ጥያቄዎች ያካተተ ይሆናል። የማለፊያ ነጥቡ ቢያንስ 24 ትክክል መልሶችን(80%) ያካትታል። የእውቀት ፈተና በሚወስዱበት በእያንዳንዱ ግዜ የ$10 ክፍያ አለው።

የእውቀት ፈተናው የእርሶ የትራፊክ ህግ፣ የመንገዶችን ደንቦች፣ የሞተር ተሽከርካሪ ህጎችን እና ደህንነት የሚያስጠብቅ አሰራሮችን እውቀቶትን ለመመዘን የተዘጋጀ ነው። የሚፈተኑበት መረጃ እዚህ መመሪያ ውስጥ አለ።

ለ ደረጃ D (Class D) የመንጃ ፈቃድ የናሙና ጥያቄዎች:

1. የትራፊክ ምልክቱ አረግጓዴ ቢሆን እና የፖሊስ መኮንን እንዲያቆሙ ቢጠቁሞት፣ እርሶ ማድረግ ያለቦት:
   A. የትራፊክ መኮንኑን መታዘዝ
   B. የትራፊክ ምልክቱን መታዘዝ
   C. መጀመሪያ የትራፊክ መኮኑን መታዘዝ፣ ቀጥሎ ደግሞ ምልክቱን
   D. ከፊት ለፊቶ ያለው ተሽከርካሪ የሚያደርገውን ማድረግ

2. ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ማለፍ የተፈቀደሎት መሆኑን ለማወቅ ከሁሉ የተሻለው መንገድ :
   A. ብልጭ ድርግም የሚል አረንጓዴ መብራት መኖሩን ማየት
   B. ከፊት ለፊቶ ያለው መንገድ ቀጥ ያለ መሆኑን ማየት
   C. ከፊት ለፊቶ ያለው ተሽከርካሪ ለማለፍ ይቻላል የሚል ጥቆማ ሲያደርግ ማየት
   D. ሙሉ ወይም የተቆራረጡ የመስመር ምልክቶች መኖራቸውን ማየት

3. በኢንተርስቴት ውስጥ አጭር መግቢያ ሲኖር እና ፍጥነት መጨመሪያ መስመር(አክስለሬሽን ሌን) ሳይኖር ሲቀር፣ ማድረግ ያለቦት:
   A. በመጨረሻው ቀኝ ባለው የትራፊክ መስመር(ሌን) መግባት እና ከትረፊኩ ፍሰት ጋር ተመሳሳይ ፍጥነትን መጨመር
   B. የዋናው መንገድ በመንገዱ ጎን ያለው ቦታ(ሾልደርን) በመጠቀም የትራፊኩ ፍጥነት ጋር መድረስ
   C. በትራፊኩ ክፍተት ሲያገኙ ብቻ መግቢያው ላይ ፍጥነት መጨመር

መልሶች: 1-A፣ 2-D፣ 3-C

ከሌላ አገር ወይም ከሌላ ክልል(ስቴት) የሆነ የሚሰራ የመንጃ ፈቃድ ያላቸው የውጭ አገር ዜጎች፣ የዲሲን የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት የሚፈልጉ ከሆነ የእውቀቱን እና የአይን ፈተና መውሰድ እና ማለፍ አለባቸው።

የዲሲ የመናጃ ፈቃዶ ከ365 ቀናት በላይ ተቃጥሎ የቆየ ከሆነ፣ የእውቀት ፈተናውም ወይም የዲሲን የኢንተርኔት(ኦንላይን) ትራፊክ ትምህርት-ቤት ኮርስ መውሰድ እና ማለፍ አለቦት።የዲሲ የመንጃ ፈቃዶ ከ 545 ቀናት በላይ ተቃጥሎ የቆየ ከሆነ፣ የእውቀት ፈተናውን እና የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናን እንዲወስዱ እና እንዲያልፉ ይጠየቃሉ። የመንጃ ፈቃዶ ከተሻረ፣ እንደገና ለማግኘት በሚሉበት ወቅት፣ የእውቀት ፈተናውን እና የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናን እንዲወስዱ እና እንዲያልፉ ይጠየቃሉ።

የዲሲ የመንጃ ፈቃድ እያወጡ ወይም እያሳደሱ ከሆነ እና የመንጃ ፈቃዶ ሲቃጠል 70 አመቶ ወይም ከዚያ በላይ ከሆኖት፣ የዲሲ የመንጃ ፈቃድ ወይም የመታወቂያ ወረቀት ማመልከቻው ላይ የበሰሉ ነጂ (Mature Driver) የሚለውን ክፍል ባደረጉት የህክምና ምርመራ መሰረት ደህንነትን በተጠበቀ መልኩ የሞተር ተሽከርካሪ ለመንዳት ችሎታው እንዳሎት በማረጋጋጥ በህኪም ማስሞላት አለቦት።

የመንዳትን እውቀት ፈተናን ከወደቁ፣ ፈተናውን ከወደቁበት አንስቶ እስከ 72 ሰአታት ድረስ እንደገና ለመፈተን አይፈቀድሎትም። የእውቀት ፈተናዎን በተከታታይ ስድስት(6) ግዜ ከወደቁ፣ ከመጀመሪያው ከወደቁት ፈተና ቀን አንስቶ እስከ አስራ ሁለት(12) ወራት ድረስ እንደገና መፈተን አይፈቀድሎትን።

የማየት ችሎታ ግምገማ

የማየት ችሎታዎን ለመገምገም፣ አንድ ማሽን ውስጥ እንዲመለከቱ እና መስመሮች ላይ ያሉ ነገሮችን ለዲኤምቪ ተወካዩ እንዲያነቡ ይጠየቃሉ። ይህ ግምገማ የአይኖ እይታዎ እና የወርድ እይታዎ (peripheral vision) ደህንነትን ባስጠበቀ መልኩ የሞተር ተሽከርካሪን ለመንዳት የዲስትሪክቱን መመዘኛ እንደሚያሟላ ይወስናል። ይህ የህክምና ምርመራ አይደለም። የእይታ ግምገማውን ከወደቁ ከአይን ህክምና ባለሙያ የአይን ሪፖርት እንዲያመጡ ይጠየቃሉ። የእይታ ግምገማውን ለማለፍ መነፀር ወይም ኮንታክት ሌንስ ማድረግ ካስፈለጎት፣ ሲነዱ እነዚህን ነገሮች ማድረግ አለቦት፣ እናም መንጃ ፈቃዶ ይህንኑ ገደብ ያሳያል።

የማስተካከያ የእይታ ሌዘር ቀዶ ጥገና (corrective vision laser surgery) የነበሮት ከሆነ፣ የማስተካከያ ሌንስ ገደቡን ከመንጃ ፈቃዶ ለማስነሳት የህኪም ማረጋገጫ ያስፈልጋል።

የጎዳና ላይ የችሎታ ፈተና

የጎዳና ላይ የመንዳት ችሎታ ፈተናው እንደፈለጉ የማንቀሳቀስ ችሎታን፣ በትራፊክ ውስጥ መንዳትን፣ የመታጠፊያ መጠቆሚያዎችን የመጠቀም ችሎታዎን፣ ደህንነት በተጠበቀ መንገድ ተሽከርካሪውን መቆጣጠር መቻል እና ትይዩ (ፓራራል) ፓርኪንግን ያካተተ ይሆናል። የጎዳና ላይ ፈተናው በዲሲ መንገዶች ላይ ይሰጣል። ለእያንዳዩንዱ የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተና $10 ክፍያ ይከፈላል።

በአጠቃላይ፣ ለተመሳሳይ ደረጃ የሚሰራ የሌላ ስቴት ፈቃድ ካሎት እና ወደዲሲ የመንጃ ፈቃድ የሚቀይሩት ከሆነ የጎዳና ላይ ፈተናው ቀሪ ይሆንሎታል። የዲሲ የመንጃ ፈቃዶ ከ 545 ቀናት በላይ ተቃጥሎ ከቆየ፣ የእውቀት አና የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናዎችን እንዲወስዱ እና እንዲያልፉ ይጠየቃሉ።

የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናዎቹ በቀጠሮ ብቻ ነው ማስያዝ የሚቻለው። የመንጃ ፈቃድ የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተና ቀጠሮ ዲኤምቪ ለማስያዝ፣ የሚሰራ የለማጅ ፈቃድ ሊኖሮት ይገባል። የጎዳና ላይ ፈተናዎን በኢንተርኔት (ኦንላይን) በ www.dmv.dc.gov ወይም 311 በመደወል ሊያሲይዙ ይችላሉ።

ቀጠሮ የተያዘበት የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተና በሁለት የስራ ቀናት ውስጥ ካልተሰረዘ የ $30 ብር የመሰረዣ ክፍያን ያስከትላል። የጎዳና ላይ ፈተናዎን ከሁለት የስራ ቀናት በፉት ከሰረዙ ወይም ዲኤምቪ የጎዳና ላይ ፈተናዎን ከሰረዘው ይህ ክፍያ አይደረግም። የጎዳና ላይ ፈተናዎን 311 በመደወል ሊሰርዙት ይችላሉ።

የጎዳና ላይ ፈተና ቀጠሮ ባለቦት ቀን የሚከተሉትን ማድረግ አለቦት:

- ቢያንስ ከቀጠሮዎ ሰአት ከ 10 ደቂቃ በፊት መድረስ፣
- የተሽከርካሪዎችን መስፈርቶች የሚያሟላ ተሽከርካሪ ውስጥ ሆነው መምጣት፣
- የሚሰራውን የለማጅ ፈቃዶን ማምጣት፣
- እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ ፈቃድ ካላቸው ነጂ ጋር አብረው መሆን፣
- የሚሰራ ምዝገባ እና የኢንሹራንስ ማረጋገጫ ያለው ተሽከርካሪ ማምጣት፣ እና
- የደህንነት ቀበቶዎን(ሲት ቤልቶን) ማድረግ።

ግራድ (GRAD) ፕሮግራም (ከ 16 – 20 እድሜ) ውስጥ ከሆነ ያሉት፣ የተሞላ ለመሸጋገሪያ ፈቃድ ብቁነት ማረጋገጫዎን (Certificate of Eligibility for Provisional License)፣ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች ያለበትን ቅጽ ያምጡ።

የለማጅ ፈቃድ ካሎት እና ወደ ጎዳና ላይ ፈተናው ፈቃድ ያለው እና 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነው ነጂ ጋር ሳይሆን ብቻዎን ከመጡ፣ ፈተናዎን መውሰድ አይችሉም። የጎዳና ላይ ፈተናውን ከወደቁ፣ ፈተናውን ከወደቁበት አንስቶ ከ72 ሰአታት በፊት እንደገና ለመውሰድ አይፈቀድሎትም። የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናውን ለስድስት(6) ተከታታይ ግዚያት ከወደቁ፣ የመጀመሪያውን ፈተና ከወደቁበት ቀን አንስቶ እስከ እስራ ሁለት (12) ወራት ድረስ እንደገና ለመፈተን አይፈቀድሎትም።

ለጎዳና ላይ ችሎታ ፈተና የሚጠቀሙበት **ተሽከርካሪ** የሚከተሉትን ማሟላት አለበት:

- በወንበሮቹ መሀከል የሚገኝ የእጅ ኢመርጀንሲ ፍሬን ያለው። በወንበሮቹ መሀከል ባለ የእጅ ኢመርጀንሲ ፍሬዩ ምትክ፣ ተሽከርካሪው ሁለተኛ መሪ እና/ወይም በተሳፋሪው በኩል ያለ ፍሬን ወይም የመንጃ ፈቃድ ፈታኙ በቀላሉ ሊደርሱበት የሚችሉት ሌላ የሆነ የኢመርጀንሲ የደህንነት መሳሪያ ያለው፣
- ከማንኛውም ሌላ ክልል(ስቴት) ወቅታዊ ምዝገባ ያለው፣
- የሞተር ተሽከርካሪ ሃላፊነት (ሊያቢሊቲ) ኢንሹራንስ ካርድ ወይም ፖሊሲ ያለው፣
- ካርዱ/ፖሊሲው ተሽከርካሪውን መጥቀስ አለበት አናም የሚቃጠልበትን ቀን ማካተት አለበት።
- የሚሰራ ኢንስፔክሽን ስቲከር የተለጠፈበት(ተሽከርካሪው በተመዘገበበት ክልል(ስቴት) መደረግ ያለበት ከሆነ)፣
- የፊት እና የሃላ ታርጋ ማሳየት(ተሽከርካሪው በተመዘገበበት ክልል(ስቴት) መደረግ ያለበት ከሆነ)፣
- በትክክል የሚሰሩ የፍሬን መብራት፣ ምልክት መስጫዎች፣ ክላክስ(ጥሩንባ)፣ እና የሹፌር/ተሳፋሪ መስኮት እና በሮች ያለው፣
- በትክክል የተገጠሙ ወደ ሃላ ማሳያ መስተዋት እና ሁለቱ የጎን ማሳያ መስታዋቶች ያለው፣
- ያልተከለለ የእይታ ስፋት የሚሰጥ ምንም ያልተሰነጠቀ እና ፍንጥርጣሪ የሌለው የፉት መስተዋት ያለው እና ወደሃላ ማሳያ መስታዋቱ ላይ ምንም ነገር ያልተንጠለጠለበት፣

- በጥሩ ሁኔታ ያሉ እና በአግባቡ የተነፉ ጎማዎች ያሉት። የመቀየሪያ(ስፔር)(ዶናት) ጎማዎች ተቀባይነት የላቸውም፣
- የኪራይ ተሽከርካሪዎች የጎዳና ላይ ፈተና መጠቀም የሚፈቀደው ፈተናውን የሚወስደው ሰው ስም የኪራይ ውሉ ላይ ለኪራይ ተሽከርካሪው ፈቃድ እንዳለው ነጂ እና አግባብ ያለው ኢንሹራንስ ሽፋን እንዳለው ተደርጎ ከተመዘገበ ብቻ ነው፣ እና
- ዝቅ ያለ ነጃድን ጨምሮ፣ ምንም ሰርቪስ ወይም የማስጠንቀቂያ የሚል መብራት ዳሽቦርዱ ላይ ያልበራ።

እታች ባሉት አንድ ወይም ከዚያ በላይ ለሆኑ ምክንያቶች የጎዳና ላይ ፈተናዎ ሊሰረዝ ይችል ይሆናል:

- ፈታኙ ፍሬኑ ጋር ለመድረስ ወይም በአደጋ(ኢመርጀንሲ) ግዜ ተሽከርካሪውን ለማቆም ችግር ይኖርብኛል ብለው ካመኑ፣
- አመቺ ያልሆ የአየር ሁኔታ ወይም ከዲኤምቪ ቁጥጥር ውጪ የሆነ መንገዱን አደገኛ ሊያደርግ የሚችል ሌላ ሁናቴ ካለ፣ ወይም
- እርሶ እና ተሽከርካሪዎ የጎዳና ላይ ፈተና መስፈርቶችን በሙሉ ሳያሟሉ ከቀሩ።

የመንጃ ፈቃዶች እና ሌሎች ፈቃዶች አይነቶች

የለማጅ ፈቃድ

እድሜዎ ከ21 አመት በታች ከሆነ፣ በቀስ በቀስ አዋቂ ነጂነት ማሳደጊያ ፕሮግራም (Gradual Rearing of Adult Drivers (GRAD) Program) ስር መንቀሳቀስ አለቦት። የግራድ (GRAD) ፕሮግራም አዲስ ነጂዎችን (16-20 እዱሜ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ እድል ከማግኘታቸው በፉት ደህንነትን በጠበቀ መንገድ የመንዳት ልምድ እንዲያዳብሩ ይፈቅዳል። የለማጅ ፈቃድ እርሶ፣ እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው እና ትክክል የሆነ(የሚሰራ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ያላቸው ሹፌር የፉት ተሳፋሪ ወንበር ላይ ሆነው አብረዎት እየተቆጣጠሮት ባሉበት ተሽከርካሪ እንዲያዘዋውሩ ያስችሎታል። የለማጅ ፈቃድ ለማግኘት እድሜዎ ቢያንስ 16 አመት መሆን፣ የእውቀት ፈተና ማለፍ፣ እና የማየት ችሎታ ግምገማን ማለፍ አለቦት። ከ 18 አመት በታች ከሆኑ፣ በተጨማሪም፣ በወላጆ/ሞግዚቶ የተፈረመ የወላጅ የስምምነት ቅጽ ሊኖሮት ይገባል። የለማጅ ፈቃዱ ለአንድ አመት ይሰራል። ግራድ ፕሮግራም (GRAD program) ውስጥ ከሆኑ እና የመሸጋገሪያ ፈቃድ ደረጃ መሸጋገር ከመቻሎ በፊት የለማጅ ፈቃዶ ከተቃጠለ፣ የእውቀት ፈተናን እንደገና መውሰድ እንዳይኖርቦት የለማጅ ፈቃዶ ከተቃጠለ በሃላ በ365 ቀናት ውስጥ ማሳደስ አለቦት።

የመሸጋገሪያ የመንጃ ፈቃድ

የመሸጋገሪያ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት እድሜዎ ቢያንስ 16 አመት ከ 6 ወር ሊሆን ይገባል። ቢያንስ ለ 6 ወራት የሚሰራ የለማጅ ፈቃድ ኖሮት ሊቆዩ ይገባል እና ምንም ነጥብ የሚያስገኝ በመንቀሳቀስ ላይ የተገኘ ነጥብ ሊኖሮት አይገባም። እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው እና ትክክል የሆነ(የሚሰራ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ያላቸው ነጂ አብረዎት ሆነው ቢያንስ የ40 ሰአት የመንዳት ልምምድ እንዳደረጉ የሚያረጋግጥ የተፈረመ የ40 ሰአት ለመሸጋገሪያ ፈቃድ ብቁነት ማረጋገጫ (Certification of Eligibility for Provisional License) ማቅረብ አለቦት። የጎዳና ላይ ችሎታ ፈተናን መውሰድ እና ማለፍ አለቦት። የመሸጋገሪያ ፈቃዱ ለአንድ አመት ይሰራል እናም ሊታደስ ይችላል። እድሜዎ ከ18 አመት ከመሆኑ በፊት አንድን ተሽከርካሪ ክፍያ ለማግኛ መንዳት አይፈቀድሎትም።

ሙሉ የመንጃ ፈቃድ

የመሸጋገሪያ ፈቃዶን ቢያንስ ለ6 ወራት ይዘው ከቆዩ በሃላ የሚከተሉትን ማድረግ አለቦት:

- ለ 12 ተከታታይ ወራት ምንም ነጥብ የሚያስገኝ በመንቀሳቀስ ላይ የተገኘ ጥፋት አይኑሮት፣
- የምሽት መንዳትን ቢያንስ ለ10 ሰአታት ልምምድ ያድርጉ፤ እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው እና ትክክል የሆነ(የሚሰራ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ያላቸው ነጂ አብረዎት ሆነው ቢያንስ የ 10 ሰአት የምሽት የመንዳት ልምምድ እንዳደረጉ የሚያረጋግጥ የተፈረመ የሙሉ የመንጃ ፈቃድ ብቁነት ማረጋገጫ (Certification of Eligibility for Full Driver License) ቅጽ ማቅረብ አለቦት፣ ከዚያ በሃላ ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ሊሰጦት ይችላል።

የግራድ ፕሮግራም (GRAD program) ላይ ለመሳተፍ የማይጠበቅቦት ከሆነ፣ የለማጅ ፈቃድ መስፈርቶቹን በሙሉ ካጠናቀቁ በሃላ የጉዳና ላይ ችሎታ ፈተናውን መውሰድ እና ማለፍ አለቦት፣ ከዚያ በሃላ ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ይሰጦታል።

በመደበኛው የመንጃ ፈቃድ፣ የጠቅላላ የተሽከርካሪ ክብደት ደረጃ (gross vehicle weight rating) (GVWR) 26,001 ፓውንድ በታች የሆነው ለንግድ ጥቅም ያልሆነ፣ በሞተር የሚንቀሳቀሱ ሳይክሎች፣ እና እስከ አስራአምስት (15) ሰዎች የሚይዝ የተሳፋሪዎች ቫን ማንቀሳቀስ ይችላሉ። የመንጃ ፈቃዶን ይዘው ለመቆየት ደህንነትን የሚጠብቁና ሀላፊነት የሚወስዱ ነጂ መሆን አለቦት።

የቀስ በቀስ አዋቂ ነጅዎች ማሳደጊያ (ግራድ) (GRAD) ፕሮግራም

ለግራድ (GRAD) የተፈቀዱ የመንጃ ሰአታት

የለማጅ ፈቃድ
እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነጂ አብሮት መኖር አለባቸው።
ሁሉም ቀን 6:00am – 9:00pm

የመሸጋገሪያ ፈቃድ
ሴፕቴምበር – ጁን
ሰኞ – ሀሙስ፣ 6:01am – 10:59pm
አርብ – እሁድ፣ 6:01am – 11:59pm

ጁላይ እና ኦገስት
ሁሉም ቀን 6:01am – 11:59pm

ከ 17 – 18 እድሜ መሀከል ላሉ መስፈርቶች የተጫኑበት ሙሉ ፈቃድ
ሴፕቴምበር – ጁን
ሰኞ – ሀሙስ፣ 6:01am – 10:59pm
አርብ – እሁድ፣ 6:01am – 11:59pm

ጁላይ እና ኦገስት
ሁሉም ቀን 6:01am – 11:59pm

ወደ ስራ ወይም ከስራ፣ ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር የደረገው ዝግጅት፣ የሀይማኖት ወይም የእስፖርት ዝግጅቶች ወይም እርሶ ተሳታፊ የሚሆኑበት ተዛማች የስልጠና ግዜዎች በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ በሲቪክ ድርጅት፣ ወይም ሌላ ለአቅመ አዳም ላልደረሱ ሀላፊነት የሚወስድ ተመሳሳይ ተቋም ስፖንሰር የተደረ ተዛማች የስልጠና ግዜ ለመሄድ፣ ወይም እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነ የሚሰራ(ትክክለኛ) የመንጃ ፈቃድ ያላቸው ሹፌር የመቀመጫ ቀበቶ(ሲት ቤልት) አድርገው እና ከእርሶ አጠገብ ያለው የተሳፋሪ ወንበር ላይ ሆነው አብሮ ካሉ፣ በግራድ የተከለከሉ ሰአታት ውስጥ ማሽከርከር ይችላሉ።

21 አመት ላይ የግራድ (GRAD) ነጅዎች ከፕሮግራሙ ይለቀቃሉ። የለማጅ ፈቃድ ይዘው ባሉበት ወቅት እድሜዎ 21 አመት ሲሞላ ወዲያውኑ የጎዳና ላይ ፈተና ቀጠሮ መውሰድ ይችላሉ። ምንም አይነት የመንዳት ማረጋገጫ ቅጽ ወይም የስድስት(6) ወር ይዞ የመቆያ ግዜ አያስፈልግም።

የመሸጋገሪያው ፈቃድ ደረጃ ላይ፣ እድሜዎ 21 አመት ሲሞላ ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ለማግኘት የዲኤምቪ የአገልግሎት ማእከል ጋር መሄድ ይችላሉ። ምንም አይነት የመንዳት ማረጋገጫ ቅጽ ወይም የስድስት (6) ወር ይዞ የመቆያ ግዜ አያስፈልግም።

የግራድ ፕሮግራም (GRAD Program) ገደቦች

የለማጅ ፈቃድ:
ብቻዎን መንዳት **አይችሉም**። እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው እና ትክክል የሆነ(የሚሰራ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ያላቸው ነጂ የፉት ተሳፋሪ ወንበር ላይ ሆነው አብረዎት መኖር እና መመሪያ መስጠት አለባቸው። ለለማጅ ፈቃድ ባለይዞታዎች የመንጃ ሰአቶቹ የተወሰኑ ናቸው። እርሶ እና ተሳፋሪዎቾ በሁሉም ሰአታት የመቀመጫ ቀበቶ(ሲት ቤልት) ማድረግ አለባችሁ። አንድን ተሽከርካሪ ክፍያ ለማግኘት መንዳት አይችሉም። የንግድ መኪናን ማንቀሳቀስ አይችሉም። እየነዱ የእጅ ስልክ(ሞባይል) ወይም ሌላ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን መጠቀም አይችሉም(እጅን ነጻ የሚያደርግ መሳሪያ ቢኖረውም ባይኖረውም)።

እድሜያቸው 16 ½ - 20 አመት ለሆነ ሹፌሮች የመሸጋገሪያ ፈቃድ
ለብቻዎ መንዳት ይችላሉ። እድሜያቸው 21 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናቸው እና ትክክል የሆነ(የሚሰራ) ሙሉ የመንጃ ፈቃድ ያላቸው ነጂ የፉት ተሳፋሪ ወንበር ላይ የሆኑ እና የመቀመጫ ቀበቶ ያደረጉ እንድ(1) ተሳፋሪ እና እና ሌላ ማንኛውም የእርሶ ወንድም/እህት፣ ልጅ ወይም ወላጅ የሆኑ ተሳፋሪ ጋር መንዳት ይችላሉ። እርሶ እና ተሳፋሪዎቾ በሁሉም ግዜያት የደህንነት ቀበቶ(ሲት ቤልት) ማድረግ አለባችሁ። ለመሸጋገሪያ ፈቃድ ነጅዎች የመንጃ ሰአታት የተወሰኑ ናቸው። እድሜዎ ከ18 አመት በታች እያለ አንድን ተሽከርካሪ ክፍያ ለማግኘት ማንቀሳቀስ አይችሉም።

መስፈርቶች የተጣሉባቸው ሙሉ ፈቃድ (እድሜ ከ18 አመት በታች):
ለብቻዎ መንዳት ይችላሉ። እድሜዎ ከ 18 አመት በታች ከሆነ፣ እድሜያቸው 21 አመት በታች ከሆኑ ከሁለት (2) ተሳፋሪዎች በላያ ካልሆኑ ጋር ሆነው መንዳት ይችላሉ። ይህ ገደብ ወንድም/እህቶ ወይም ልጆ ለሆኑ ተሳፋሪዎች አይሰራም።እድሜዎ ከ 18 አመት በታች ከሆነ፣ ለክፍያ ሳይሆን ለመዝናናት ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ የተሳፋሪ ተሽከርካሪ ወይም የሞተር ባይስክል ውጭ የሆነ የሞተር ተሽከርካሪ ማሽከርከር አይችሉም። እርሶ እና ተሳፋሪዎቾ በሁሉም ግዜያት የደህንነት ቀበቶ(ሲት ቤልት) ማድረግ አለባችሁ። እድሜዎ ከ 18 አመት በታች ከሆነ፣ ለወላጆ/ለህግ ሞግዚቶ የግራድ (GRAD) ጥሰቶቾን ማሳሰቢያ ይሰጣቸዋል። እድሜያቸው ከ 17 – 18 አመት መሀከል ለሆኑ ሙሉ ፈቃድ ነጅዎች የመንጃ ሰአታቶቹ የተወኑ ናቸው።

የግራድ ፕሮግራም (GRAD Program) ማስፈጸሚያ

የለማጅ ፈቃድ ደረጃዎች:
ከ18 በታች ከሆኑ፣ የግራድ ጥሰቶቹን ለወላጆ/ለህግ ሞግዚቶ ማሳሰቢያ ይሰጣል። ያመኑበት፣ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት፣ ወይም የተፈረደበት ማንኛውም በመንቀሳቀስ ላይ የሚደረግ ነጥብ የሚያስይዙ ጥሰቶች፣ ለመሸጋገሪያ ፈቃድ ለማመልከት መጠበቅ ያለቦትን ግዜ መጠን ያራዝሙታል። ወደ መሸጋገሪ ፈቃድ ደረጃ ከመሸጋገሮ በፊት ለስድስት(6) ተከታታይ ወራት ከማንኛውም ነጥብ ከተሰጠባቸው ወይም ሊያሰጥ ከሚችል በመንቀሳቀስ ላይ ከተሰጠ ጥሰት ነጻ መሆን አለቦት። በለማጅ ፈቃድ ግዚያቶቹ 8 ወይም ከዚያ በላይ የሆነ ነጥብ ከተያዘቦት ወይም የግራድ ፕሮግራም ገደቦችን ከጣሱ፣ የለማጅ ፈቃዶ ለዘጠና(90) ቀናት ለመታገድ እና መልሶ ለማግኛ ክፍያ ይጋለጣሉ።

የሽግግር ፈቃድ ደረጃ:
ከ18 በታች ከሆኑ፣ የግራድ ጥሰቶን ለወላጆ/ለህግ ሞግዚቶ ማሳሰቢያ ይሰጣል። ያመኑበት፣ ጥፋተኛ ሆነው የተገኙበት፣ ወይም የተፈረደበት ማንኛውም በመንቀሳቀስ ላይ የሚደረግ ነጥብ የሚያስይዙ ጥሰቶች፣ ለሙሉ ፈቃድ ማመልከት መጠበቅ ያለቦትን ግዜ መጠን ያራዝመዋል። መስፈርቶች የተጣሉባቸውን ወደ ሙሉ ፈቃድ ከመሸጋገሮ በፊት ለአስራ ሁለት (12) ተከታታይ ወራት ከጥሰት ነጻ መሆን አለቦት። በሽግግር ፈቃዶ ግዜያቶ ማንኛውንም የግራድ ፕሮግራም ገደቦችን ከጣሱ፣የግራድ ፕሮግራም ጥሰቶች የመጀመሪያ፣ ሁለተኛ፣ ሶስተኛ ወይም ከዚያ በላይ መሆናቸው ላይ ተመስርቶ የሽግግር ፈቃዶ ለሰላሳ(30)፣ ስልሳ (60) ወይም ዘጠና(90) ቀናት መታገድ ይጋለጣል። እነዚህ ቅጣቶች የሚሰጡት አግባብ ካላቸው ከሌሎች ማንኛውም ቅጣቶች በተጨማሪ ነው። በተጨማሪም፣ እንደሌላ ማንኛውም ነጂ፣ ነጥቦ በጥቅሉ 10 ከደረሰ ወዲያውኑ ይታገዳሉ። ከታገዱ በሃላ፣ የመሸጋገሪያ ፈቃዶን መልሶ ለማግኘት መልሶ የማግኛ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋሉ።

ሌሎች አገልግሎቶች

አካል ለጋሽ (Organ Donor)
የአካል እና ቲሹ ለጋሽ መሆንን የሚመርጡ ሰዎች ልግስናን አለም ላይ ለውጥ እንደማምጫ መንገድ አድርገው ያዩታል። የህክምና ሳይንሱ መላቅ የሰው ልጅ አካልን በመቀየር የግለሰቦችን ጤና ለመመለስ ያስችላል። አንድ ለጋሽ እስከ ስምንት ሰዎችን ህይወት ሊያተርፍ ይችላል እናም እስከ ሀምሳ ሌሎች ህይወት ሊያሻሽል ይችላል።

ይህን ያውቁ ኖሯል?

- በሁሉም እድሜ ያሉ እና የጤና ሁኔታ ያላቸው ሰዎች ለጋሾች መሆን ይችላሉ፣ የስኳር በሽተኞች፣ ሄፒቴቴስ ወይም ሌላ የጤና ሁኔታ ያላቸው ሳይቀር።
- ለለጋሾት ቤተሰቦች ምንም አይነት ክፍያ የለውም ወይም ለአካል ልገሳው ሂደት ርስት(ከኢስቴት) ወጪ የለውም።
- አብዛኞቹ ዋና ዋና በዩኤስ ያሉ ሀይማኖቶች የአካል እና የቲሹ ልገሳን ይደግፉሉ።
- ልገሳ የክፍት ሳጥን ቀብር አማራጭን አያግድም።
- የአካል እና የቲሹ መወሰድ የሚደረገው ሁሉም ህይወትን የማትረፊያ ሙከራዎች ከተሟጠጡ እና ሞት በህጋዊ መንገድ ከታወጀ በሃላ ብቻ ነው።

እንዴት መመዝገብ ይቻላል?

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ፣ እድሜዎ 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ ከሆነ የመለገስ ፈቃዶን በመንጃ ፈቃድ ማመልከቻ ላይ ለአካል/ቲሹ ልገሳ ጥያቄው "አዎ" የሚለው ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ ሊጠቁሙ ይችላሉ።

ለቤተሰቦ እና ለህይወት ባለጋራዎ በሞቶ ግዜ እርሶን ወክለው መናገር እንዲችሉ ለጋሽ መሆን እንደሚፈጉ መንገር አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም፣ ለጋሽ የመሆን ፍላጎቶን ለሀኪሞ፣ የሀይማኖት መሪዎ፣ እና ጠበቃዎ ማጋራት አለቦት።

ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ያግኙ:

- የዩኤስ የጤና ዲፓርትመንት እና የሰዎች አገልግሎት (US Department of Health and Human Services) በ www.organdonor.gov
- አሜሪካ የህይወት ልገሳ (Donate Life America) በ www.donatelife.net ወይም 1-866-BE-A-DONOR።

የልዩ አገልግሎቶች (Selective Service) ሲስተም
የዲሲ የመንጃ ፈቃዶን በሚያገኙበት ወቅት በዲኤምቪ ለልዩ አገልግሎቶች መመዝገብ ይችላሉ። ከምዝገባው ለመውጣት በዲሲ ዲኤምቪ የመንጃ ፈቃድ ማመልከቻ ሂደት በኩል የማስቀሪያ ቅጽን (waiver form) ካልመረጡ በስተቀር፣ ዲሲ ዲኤምቪ እድሜያቸው በ 18 – 25 መሀከል የሆኑ ወንዶችን ለልዩ አገልግሎት ይመዘግባል።

ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ያግኙ:

Registration Information Office
Selective Service System
Data Management Center
P.O. Box 94638
Palatine, IL 60094-4638
ስልክ: 847-688-6888
TTY: 847-688-2567
www.sss.gov

ለመምረጥ መመዝገብ
የዩኤስ ዜጋ ከሆኑ እና ከሚቀጥለው ምርጫ በፊት እድሜዎ 18 አመት ወይም ከዚያ በላይ የሚሆን ከሆነ፣ በመንጃ ፈቃድ ማመልከቻዎ ላይ ለምዝገባ ጥያቄው "አዎ" የሚለው ሳጥን ላይ ምልክት በማድረግ እና የዲሲ የመራጮች መመዝገቢያ ቅጽን (DC Voter Registration Form) በሞሙላት ለመምረጥ የመመዝገብ ፍላጎቶን ማመልከት ወይም የምዝገባ መረጃዎን ወቅታዊ ማድረግ ይችላሉ።

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ለመምረጥ ለመመዝገብ የሚከተለውን ያስፈልጎታል:

- የዩ.ኤስ. ዜጋ መሆን፣
- የዲ.ሲ. ነዋሪ መሆን፤
- ከሚቀጥለው ምርጫ በፊት ወይም በምርጫው ላይ እድሜዎ ቢያንስ 18 አመት መሆን፣
- በከፍተኛ የወንጀል ጥፋት(ፌሎኒ) እስር ቤት አለመሆን፣
- በፍርድ ቤት " የአእምሮ ብቃት የሌለው" ("mentally incompetent") ተብሎ ያልተወሰነበት፣ እና
- ከዲ.ሲ. ውጪ በማንኛውም ቦታ የመምረጥ መብትን አለመጠየቅ።

ማመልከቻውን ካጠናቀቁ በሶስት (3) ሳምንታት ውስጥ የምርጫ መመዝገቢያ ካርዶ ሊደርሶ ይገባል።

ለበለጠ መረጃ የሚከተለውን ያግኙ:

- የምርጫ እና ስነምግባር ቦርድ (Board of Elections and Ethics) በ www.dcdoee.org ወይም በ 202-727-2525።

መታወቅ ያለባቸው አስፈላጊ ነገሮች

- ሹፌሩ እና በተሽከርካሪዎ ውስጥ ያሉ ተሳፋሪዎች በሙሉ የደህንነት ቀበቶ(ሲት ቤልት) ማድረግ አለባቸው።
- በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ከሞባይል ስልክ ጋር ሲነዱ እጆች ነጻ መሆን አለባቸው።
- ነዋሪዎች የአድራሻ ለውጣቸውን ለተሽከርካሪዎች ዲፓርትመንት (Department of Motor Vehicles) በስልሳ(60) ቀናት ውስጥ ወቅታዊ ማድረግ አለባቸው።
- ተሽከርካሪው ተመዝግቦ እስካለ ድረስ የኢንሹራንስ ሽፋን መቀጠል አለበት። በሽፋኑ ላይ ክፍተት ካለ ለገንዘብ ቅጣት ያጋልጣል። የተሽከርካሪዎ ታርጋዎችዎን ለዲኤምቪ እስኪያስረክቡ ድረስ ኢንሹራንሶን አይሰርዙ።
- በዲስቲሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሞተር ተሽከርካሪ እየነዱ በህግ አስፈጻሚ እንዲቆሙ የተደረጉ እንደሆነ፣ የሚሰራ የመንጃ ፈቃድ፣ የተሽከርካሪ ምዝገባ እና የኢንሹራንስ ማረጋገጫ የማቅረብ ሀላፊነት አለቦት። ይህንን አለማሟላት ለገንዘብ ቅጣት እና/ወይም እስር ሊያጋልጥ ይችል ይሆናል።
- ነጅዎች ለአንዳንድ በመንዳት ላይ ለሚፈጸሙ ጥሰቶች፣ ጥሰቶቹ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ይፈጸሙ ወይም ሌላ ክልል(ስቴት) ይፈጸሙ፣ ነጥቦች ያገኛሉ። አቤቱታ በሚሰማበት ወቅት ጥፋተኛ ሆነው ከተገኙ፣ በተጠየቀው ግዜ ገደብ ትኬት ሳይከፍሉ ከቀሩ፣ በትራፊክ ጥሰት ፍርድቤት ከተፈረደቦት፣ ወይም ትኬቱን ከከፈሉ(መክፈል ጥፋትን መቀበል ነው) ዲኤምቪ (DMV) ነጥቦችን ይይዛል። የሚሰጦት ነጥብ ብዛት በጥሰቱ አይነት ይወሰናል።
- ነጥቦች የመንዳት መዝገቦ ላይ እስከ ሁለት አመት የሚታዩ(አክቲቭ) ሆነው ይቆያሉ።
- ነጥብ የሚያስይዝ የመንቀሳቀስ ነጥቦችን ሳያገኙ ለሙሉ ካላንደር አመት የሚሰራ የዲሲ የመንጃ ፈቃድ ይዘው ከቆዩ፣ በመንጃ መዝገቦ ጥሩ ነጥብ (Good Point) ለማግኘት ብቁ ይሆኑ ይሆናል።
- 10 ወይም 11 ነጥብ ከተጠራቀመቦት፣ የዲሲ የመንጃ ፈቃዶ ይታገዳል እና የመንዳት መብቶን ለዘጠና (90) ቀናት ግዜ ያህል ያጣሉ። በይፋ እንደነበረው እስከሚመለስ ድረስ የመንዳት መብቶ ታግዶ ይቆያል።
- 12 ወይም ከዚያ በላይ ነጥብ ከተጠራቀመቦት፣ የዲሲ የመንጃ ፈቃዶ ይሻራል እና ለስድስት ወራት እንደገና ለማግኘት ብቁ አይሆኑም። በይፋ እንደነበረው እስከሚመለስ ድረስ የመንዳት መብቶ ተሽሮ ይቆያል።
- ደንዝዘው በመንዳት ወይም በተጽኖ ላይ ሆነው በመንዳት (driving while intoxicated or driving under the influence) ጨምሮ በሆነ የወንጀል የትራፊክ ጥሰት በዲሲ ውስጥ ተፈርዶቦት ከሆነ፣ ትንሹ ተሽሮ የሚቆይበት ወቅቶ ለመጀመሪያ ወንጀል 6 ወራት፣ ለሁለተኛ ወንጀል 2 አመት፣ እና ለሶስተኛ እና ከዚያ በሃላ ለሚመጡ ወንጀሎች 3 አመታት ነው።በይፋ እንደነበረው እስከሚመለስ ድረስ የመንዳት መብቶ ተሽሮ ይቆያል እና የመልሶ ማግኛ ክፍያ ይከፈላል።

- ለልጅ የሚከፈል ክፍያ(ቻይልድ ሰፖርት) ባለመክፈል ምክንያት የመንጃ ፈቃዶ እና ተሽከርካሪዎ ሊታገዱ ይችላል።
- የመንዳት ያልሆነ ግንኙነት ባለው የአደንዛዥ እጽ(ድረግ) ወንጀል ከተፈረደቦት፣ የመንጃ ፈቃዶ ሊሻር ይችላል።
- በሚነዳበት ወቅት ወደሃላ ማሳያ መስተዋት ላይ አንድን ነገር ማያያዝ ወይም ማንጠልጠል የዲስትሪልት ኦፍ ኮሎምቢያ ደንቡን የሚጻረር ነው።

የነጂ(አሽከርካሪ) መረጃ

ለመንዳት ብቁ ይሁኑ

መንዳት ሰዎች ከሚያደርጓቸው የተወሳሰቡ ተግባሮች አንዱ ነው እና ሁልግዜ ደህንነትን የሚያስብቅ የመንገድ ተጠቃሚ መሆን ቀላል አይደለም። መንዳት ሰዎች በመደበኛ ከሚያደርጓቸው እና ጉዳት ሊያደርስብን እና ሊገድለን ከሚችሉ ጥቂት ነገሮች አንዱ ነው።

ደህንነትን የሚያስጠብቅ ነጂ መሆን ብዙ ችሎታን፣ ልምድን፣ ሀላፊነትን እና ውሳኔን ይጠይቃል። ይሄ ስራ መንዳትን በመማር ወቅት ደግሞ የበለጠ ይከብዳል። አሽከርካሪው ደህንነት በጠበቀ መንገድ የመንዳት ችሎታው በደንብ የማየት ችሎታው፣ በጣምኑ አለመድከሙ፣ አደንዛዥ እጽ ወስዶ አለመንዳቱን፣ በአጠቃላዩ ጤነኛ መሆኑ፣ እና በስሜት ብቃት መኖር ላይ ይወሰናል።

ዲሲ ዲኤምቪ – በምርጥ ሁኔታ መንዳት

ዲሲ ዲኤምቪ የላቀ የደንበኞች አገልግሎት ለመስጠት፣ ደህንነት የተጠበቀበት የመንጃ አካባቢን ለማበረታታት እና የደንበኞችን ፍላጎት ለመከላከል የቆረጠ ነው።

ለመንዳት የተሰጠ እድል

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ የሞተር ተሽከርከካሪን መንዳት እድል እንጂ መብት አይደለም። የመንጃ ፈቃዶ በጎዳናዎቹ ላይ የሞተር ተሽከርካሪን ደህንነትን ባስጠበቀ እና ሃላፊነት ባለበት መንገድ ለመንዳት እንዲችሉ እድሉን ይሰጦታል።

የውሸት ወይም ፎርጅድ የመታወቂያ ወረቀት፣ የመንጃ ፈቃድ ወይም ሌላ ፈቃድ ማግኘት

ህጉ የውሸት ወይም የተጭበረበረ የመታወቂያ ወረቀት፣ የመንጃ ፈቃድ ወይም ሌላ ፈቃድ ለማግኘት ሙከራ ካደረጉ ወይም እያወቁ የውሸት ወይም የተጭበረበረ የመታወቂያ ወረቀት፣ የመንጃ ፈቃድ ወይም ሌላ ፈቃድ ከያዙ ለገንዘብ ቅጣት ወይም ለእስር ሊጋለጡ ይችላሉ ይላል።

የጎዳና ላይ ምልክቶች

ሁሉንም የሀይዌይ ላይ ምልክቶች ለማንበብ እና ለማብራራት መቻል አለቦት። የእውቀት ፈተናው በርካታ የአካባቢዎ እና የሀይዌይ ምልክቶችን ያካትታል እናም የዲኤምቪ ፈታኙ በመንዳት ፈተናው ወቅት ለምልክቶቹ አትኩሮ ተሰጥቷቸው እንደሆነ ለማረጋገጥ ያስተውላል።

የትራፊክ ህጎች

የትራፊክ ህጎች አላማቸው አደጋን ለመከላከል እና መኪኖች መሄድን እንዲቀጥሉ ለማድረግ ነው። ህጉን ከጣሱ ለአደጋ ምክንያት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ትራፊክን ሊያዘገዩ ይችላሉ ወይም ትኬት እና/ወይም የገንዘብ ቅጣት ሊሰጦት ይችሉ ይሆናል።

የመንዳት አራት ዋና ዋና አካሎች

1. **መመልከት እና ማየት**
2. **ማሰብ እና መወሰን**
3. **ሊያደርጉ ያሉትን ነገር ለሌሎች ማሳወቅ**
4. **ውሳኔን መውሰድ**

መመልከት እና ማየት

የሚመለከቱት በአይኖ ነው የሚያዩት ግን በአእምሮዎ ነው። በአካባቢዎ ለሚካሄዱ ነገሮች የነቃ አእምሮ ይዞ መቆየት በሚነዱበት ወቅት መውሰድ ላለቦት አስፈላጊ ውሳኔዎች ዝግጁ ያደርጎታል።

ማሰብ እና መወሰን

የሚያስፈልገውን ነገር ካዩ በሃላ፣ ስለነገሩ ማሰብ አለቦት እና ምን ማድረግ እንዳለቦት መወሰን አለቦት። ስለራሶ እና ስለሌሎች ደህንነት ግድ የሚሎት ከሆነ የሚያደርጉትን ነገር የሚወስኑት የመጨረሻ ዝቅተኛ አደጋ ማጋለጥን ሊያስከትል በሚችል ነገር ላይ ተመስርቶ ይሆናል። የመጨረሻ ዝቅተኛ አደጋ መጋለጥ ማለታችንን ያስተውሉ። ሁሉም መንዳቶች የተወሰነ አደጋ መጋለጥ አለው። አስተዋይ ነጂ ቶሎ ብሎ ሁኔታውን ይገመግማል፣ የተለያየ ነገሮችን ማድረግ እንደሚችል/እንደምትችል ያስተውላል እና ከሁሉ ባነሰ መልኩ ለአደጋ የሚያጋልጠውን ነገር ለማድረግ ይወስናል።

ሊያደርጉ ያሉትን ለሌሎች ማሳወቅ

መንገድ ላይ ያሉ ሌሎች ነጅዎች እና እግረኞች ከመንገዶ እንዲለቁሎት ምን ሊያደርጉ እንደሆነ ማወቅ አለባቸው። በእጅ ምልክቶች፣ የመታጠፊያ ምልክቶች፣ የፊት መብራት ምልክቶች፣ የፍሬን መብራቶች፣ እና መኪናዎት ቦታ በማስያዝ ያሳውቋቸዋል።

ውሳኔን መውሰድ

የሚያደርጉትን ነገር ከወሰኑ በሃላ፣ ያሎትን ልምድ እና ችሎታዎች በሙሉ ተጠቅመው ማድረግ አለቦት።

የትራፊክ ህጎችን መታዘዝ

ሁሉኑም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የትራፊክ ህጎች ማክበር አለቦት። የመንገድ ምልክቶችን፣ የትራፊክ መጠቆሚያዎችን፣ የመስመሮን(ሌን) ምልክቶችን፣ የፖሊስ መኮንንን ትእዛዞችን፣ እና በአስቸኳይ አደጋ(ኢመርጀንሲ) ሁናቴዎች የእሳት አደጋ መኪናውን አቅጣጫ ለመታዘዝ ሀላፊነት አለቦት።

አጠቃላይ ህጎች

- አጠቃላይ ህጎችን ማወቅ አለቦት።
- ማንኛውን የትራፊክ ህጎች ግንዛቤ ውስጥ ሳያስገቡ ሲቀሩ ወይም ህጉ የሚያስገድዶትን ነገር ሳያደርጉ ሲቀሩ ዝቅተኛ ወንጀል(misdemeanor) ወይም ከፍተኛ ወንጀል (felony) ይፈጽማሉ።
- ከህግ፣ ከምልክቶች ወይም መጠቆያዎች ተቃራኒ ቢሆንም እንኳን የፖሊስ መኮንን ትእዛዝ ማክበር አለቦት። እነዚህ መመሪያዎች መኪኖች(ትራፊኩ) በደህና መሄድ እንዲቀጥል አስፈላጊ ይሆኑ ይሆናል።
- የትራፉክ ወይም የጎዳና ላይ ምልክቶችን ለመሸሽ ሲሉ ጎዳናውን ትተው የግል ንብረት የሆኑ መንገዶች ውስጥ መጋዝ አይችሉም።

ሀይለኛ (Aggressive) አነዳድ

ሀይለኛ አነዳድ የመንቀዥቀዥ(ሬክለስ) አነዳድ አይነት ነው። የብሄራዊ የሀይዌ ትራፊክ ደህንነት አስተዳደር (National Highway Traffic Safety Administration) ሀይለኛ (አግሬሲቭ) ነጅዎች ሞትን ከሚያስከቱልት ግጭቶች በሙሉ 2/3ኛው ምክንያት እንደሆኑ እና ከግጭቶቹ በሙሉ 35% ምክንያት እንደሆኑ ገምቷል።

አንድ ሰው ከሚከተሉት መሀከል አንዱን ካደረገ ለሀይለኛ(አግሬሲቭ) ነጅነት ጥፋተኛ ሊሆን ይችላል:

- የጸና(ሙሉ በሙሉ) **ቀይ** የሚታይ እያለ የትራፉክ መብራትን ማለፍ
- ተሽከርካሪዎችን መቅደም እና ማለፍ
- በቀኝ በኩል ማለፍ
- በድንገት መስመሮችን መቀየር
- በጣም በቅርብ መከተል
- የማለፍ መብትን ሳይሰጡ መቅረት
- ከፍተኛውን የፍጥነት መጠን ማለፍ

ሀይለኛ(አግሬሲቭ) መንዳት በምን ምክያት ይመጣል?

- የተጨናነቀ መንገድ
- በሚቸኩሉበት ግዜ
- የሚሰራ መንገድ
- በሌላ የህይወት ዘርፍ ጭንቀት መኖር
- አደገኛ የመንዳት አመለካከት
- ራስ-ወዳድነት

ሀይለኛ(አግሬሲቭ) ነጂ ከመሆን እንዴት መከላከል እንደሚቻል:

- አስቀድሞ እቅድ ማውጣት
- የፍጥነት ገደቡን መታዘዝ
- አማራጭ መንገዶችን ለይቶ ማወቅ

- በቃ ማርፈድ
- ስርአት ያለው እና ትእግስተኛ ነጂ መሆን

እራሶን ከሀይለኛ ነጂዎች እንዴት መከላከል ይችላሉ:
- መንገዱን በመልቀቅ ሀይለኛ ነጅዎች እንዲያልፉ ማድረግ
- እነሱን አለመፈታተን
- አይን ለአይን መተያየትን ማስወገድ
- ሁልግዜ ስርአት ያለው ነጂ መሆን

ሀይለኛ(አግሬሲቭ) አነዳድን ለመከላከል እገዛ ማድረግ:
- የሀይለኛ ነጅዎችን አጋጣሚዎች ለፖሊስ ሪፖርት ማድረግ
- በእድሜ ለሚያንሱ ነጅዎች አርአያ መሆን

የተንቀዠቀዠ (ሬክለስ) አነዳድ
አንድ ሰው የሞተር ተሽከርካሪ እንደሚከተለው የሚነዳ ከሆነ በተንቀዠቀዠ (በሬክለስ) አነዳድ ጥፋተኛ ነው:
- ሆን ብሎ ለሰዎች እና ለንብረትን ደህንነት ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባት፣ ወይም
- ሆን ብሎ ለሰዎች እና ለንብረትን ደህንነት ግንዛቤ ውስጥ አለማስገባት በሚያሳይ መልኩ ማድረግ

ቸልተኛ አነዳድ
አንድ ሰው የሞተር ተሽከርካሪን ግድ በማይሰጥ መንገድ ወይም ጥንቃቄ በሌለበት ማንኛውንም ንብረት ወይም የማንኛውም ግለሰብ ህይወት አደጋ ላይ የሚጥል መንገድ ከነዳ/ከነዳች በቸልተኛ አነዳድ ጥፋተኛ ይሆናል/ትሆናለች።

የተሽከርካሪ ሽቅድድም(ድራግ ሬሲንግ)
በተለምዶ ድራግ ሬሲንግ ተብሎ የሚጠሩትን በህዝብ መንገዶች እና አውራ ጎዳናዎች ላይ የሚደረጉትን ጨምሮ በማንኛውም የተሽከርካሪ እሽቅድድም፣ ፍጥነትን ማሳየት፣ ወይም የፍጥነት ውድድር መሳተፍ የለበትም።

አደጋዎች
በህጉ መሰረት፣ የአደጋ አካል ሲሆኑ መደረግ ያለባቸው አንዳንድ ግዴታዎች አሉ። በማንኛውም በአደጋ ላይ አካል የሆነ ነጂ ዋና ዋና ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው:

- **ማቆም**
- **መቆየት:** ማንኛውንም የተጎዳን ሰው እርዳታ እስከሚሰጡ እና የራሶትን ማንነት እስከሚያስታውቁ ድረስ በስፍራው በታቻለ ቅርበት መቆየት። ከተቻለ አደጋ ከደረሰበት የመኪና መሄጃ መስመር መኪናዎትን ያንሱ።

- **ማንኛውንም የተጎዳን ሰው መርዳት:** በአደጋ ላይ ጉዳት ለደረሰበት ማንኛውም ሰው እርዳታ መስጠት አለቦት። እንደ ጉዳቱ መጠን ሁኔታ፣ አብዛኛውን ግዜ እርዳታ የሚሰጠው አንቡላንስ በመጥራት ነው። በአጠቃላይ፣ የማይሰማን ወይም ከፍተኛ ጉዳት የደረሰበትን ሰው ለማንቀሳቀስ መሞከር የለቦትም።
- **የራሶን ማንነት ማሳወቅ:** በአደጋ ላይ አካል የሆኑ ነጅዎች ስማቸውን፣ አድራሻቸውን እና በመንዳት ላይ ያሉትን ተሽከርካሪ የምዝገባ መረጃ መስጠት አለባቸው። ሲጠየቁ፣ የመንጃ ፈቃዶን ለሌላኛው አደጋ ላይ አካል ለሆኑ ሰው(ሰዎች) ያሳዩ። ማንም ሰው መረጃውን ለመቀበል የማይችል ከሆነ እና ምንም ፖሊስ መኮንን በቦታው ከሌለ በተቻሎት ፍጥነት መረጃውን በቅርቡ ላለ የፖሊስ ጣቢያ ሪፖርት ማድረግ አለቦት።
- **የኢንሹራንስ መረጃን መስጠት:** የኢንሹራንስ ድርጅቶን ስም እና አድራሻ፣ ያካባቢው ኤጀንት ወይም ቢሮ ስም እና አድራሻ እና የፖሊሲ ቁጥሮን ወይም ሌላ መለያ ቁጥርን መስጠት አለቦት።
- **የጽሁፍ ማስታወሻ መተው:** ብቻውን ያለ ተሽከርካሪ ወይም ንብረት ጉዳት ከደረሰበት ባለቤቱን ለማግኘት ሙከራ መደረግ አለበት። ባለቤቱ ሊገኙ ካልተቻለ፣ እላይ ያሉትን የመለያ መረጃ የያዘ የጽሁፍ ማስታወሻ በተጎዳው ተሽከርካሪ ወይም ንብረት ውስጥ ወይም ላይ በሚታይ እና በማይጠፋ ስፍራ መተው አለበት።
- **የሚያስፈልገውን ሪፖርት ያድርጉ:** እርሶ አካል የሆኑበት ማንኛውም የሞተር ተሽከርካሪ አደጋን ለኢንሹራንስ ድርጅቶ ማሳወቅ (ሪፖርት ማድረግ) አለቦት።

ለማዳ(ዶሜስቲክ) እንስሳን በሞተር ተሽከርካሪ የመቱ(የገጩ) አሽከርካሪ ግዴታዎች

ለማዳ እንስሳን በሞተር ተሽከርካሪ ከገጩ ወዲያውኑ አደጋው ለደረሰበት አካባቢው ስልጣን ላለው ፖሊስ ጣቢያ ማሳወቅ አለቦት። ለእንስሳቱ እንክብካቤ ለማስግኘት ፖሊስ ለተገቢውን ኤጀንሲ ያሳውቃል።

ደህንነት የተጠበቀ ያነዳድ ልማዶች

ሀሳቦን መንዳቶ ላይ ያድርጉ፣ ህጎችን ያክብሩ እና ለሌሎች የሀይዌይ ተጠቃሚዎች አክብሮ ይኑሮት። የትራፊክ ህግንም የሚያከብሩ ቢሆንም እንኳን የመኪና አደጋ ሊያጋጥሞት ይችል ይሆናል። ሌሎች ነጂዎች የትራፊክ ህጉን አያከብሩ ይሆናል ወይም ንቁ ላይሆኑ ይችላል፣ ወይም ተሽከርካሪያቸው በመጥፎ የሜካኒካል ሁናቴ ላይ ሊሆን ይችላል። ደህንነት የሚያስጠብቁ ነጂ ለመሆን ንቁ መሆን፣ አደጋዎችን አስቀድሞ ማየት እና የሌሎችን ስህተት ማለፍ አለቦት። ይህ ክፍል አደጋዎችን ማስወገድ የሚያስችሎትን ወይም ማስወገድ የማይቻል ከሆነ ክብደቱን መቀነስ የሚችሉበትን የደህንነት ልማዶችን ይጠቁሞታል።

ደህንነቶን ለመጠበቅ ዋና ዋና የደህንነት ደንቦች በጣም አስፈላጊ ናቸው:

- የተሽከርካሪውን የውጫዊ አካል ሁኔታ ይመልከቱ – ጎማዎችን ይመርምሩ፣ የላሉ ነገሮች፣ የሚያፈሱ ነገሮች ወዘተ ካሉ ይመልከቱ፣
- ወንበሮን ያስተካክሉ፣
- መስታዋቶችን ያስተካክሉ፣
- የደህንነት ቀበቶዎችን(ሲት ቤልቶችን) በትክክል ያጥብቁ፣
- ቁልፉን ያስገቡ እና ሞተሩን ያስነሱ፣
- አስነስተው ከመጀመሮ በፉት፣ እንደ መብራት፣ የአየር ሁኔታ፣ የመንገድ እና የትራፉክ ሁኔታዎች የመሳሰሉ ጎጂ ሁኔታዎች ጉዞዎን እንዴት ሊጎዳው እንደሚችል ያስቡ፣ እና
- የተሽከርካሪው ፍሬን መብራቶችን እና ምልክቶችን ከመንዳቶ በፉት ያረጋግጡ።

መታጠፍ

ደህንነቱ የተጠበቀ መታጠፍ እቅድ ማውጣትን ይጠይቃል:

- የመታጠፉያ ቦታዎ ላይ ከመድረሶ በደንብ አስቀድመው ውሳኔዎን ያድርጉ። ብዙ ግዜ በመጨረሻ ደቂቃ ላይ የሚደረግ ውሳኔ አደጋዎችን ይፈጥራል።
- መታጠፍ ካለቦት ግዜ በደንብ አስቀድመው ወደ ትክክለኛው መስመር ይግቡ። መኪኖች የሚሄዱበት ፍጥነት ከፍ ያለ እየሆነ ሲመጣ፣ ወደትክክለኛው መስመር የሚገቡበት ፍጥነቶ እየጨመረ ይመጣል።
- ከሃላዎ እና ሁለቱንም ጎኖ ይመልከቱ። መስመር ከመቀየሮ በፉት በህግ እንደሚጠየቀው መሰረት ሀሳቦን በምልክት ያሳዩ። (የመንዳት ህጎችን ገጽ 54 ይመልከቱ)
- ምክንያታዊ ወደሆነ የመታጠፉያ ፍጥነት ያቀዝቅዙ፣ ነገር ግን ቀስ በቀስ ያድርጉት። ከዚህ የተለየ ሁኔታ ያለው የኢንተርስቴት ሌላ ሊሚትድ አክሰስ ሀይዌይን ለቀው በሚወጡበት(ኤግዚት በሚያደርጉበት) ወቅት ብቻ ነው። (ስለ ክልሎች መሀከል ያለ (ኢንተርስቴት) እና ሌሎች ሊሚትደ አክሰስ ሀይዌይ ገፅ. 38 ላይ ይመልከቱ)
- በህጉ መሰረት ይታጠፉ።

ወደሃላ መሄድ

ተሽከርካሪን ወደሃላ መንዳት ችሎታን እና ጥሩ ግምት መውሰድን ይጠይቃል። የሚራመዱ፣ የሚሮጡ፣ ወይም በመጫወቻ መኪና ወይም በልጆች ብስኪሌት የሚጫወቱ ልጆች እንዳይኖሩ ይመልከቱ። አብዛኛውን ግዜ፣ ጭንቅላቶን ካዞሩ እና በሃላ መስኮቱ በኩል ወደሃላ ካዩ እና ሁለቱንም የጎን መስታዋቶች(ስፖክዮ) ካዩ ወደሃላ መሄድ ደህንነትን የጠበቀ(ሴፍ) ይሆናል። በአንድ ወደ ሃላ ማሳያ መስተዋት ብቻ አይተማመኑ። በፍጹም፣ ሩቅ ወይም በፍጥነት ወደሃላ አይሂዱ፣ ይልቁኑ፣ ወደሃላ መዞር የሚችሉበትን መንገድ ይፈልጉ። በፍጹም፣ ከመገናኛ መንገድ(ኢንተርሴክሽን) ወይም ወደ መገናኛ መንገድ ወደሃላ አይሂዱ፣ ይልቁኑም ወደጎን ወዳለ መንገድ ይጠምዘዙ እና እዚያ ወደ ሃላ ይዙሩ ወይም በብሎኩ ዙሪያ ይንዱ። ወደሃላ ለመጠምዘዝ መግቢያ መንገድን(ድራይቨ ዌይ) ከተጠቀሙ ወደሱ ወደሃላ ሄደው እና ከእርሱ ወጥተው ቢነዱ፣ ተቃራኒውን ከማድረግ ይልቅ በተሻለ ሁኔታ ደህንነትን ያስጠብቃል። አንግል ካላቸው የማቆሚያ ስፍራዎች በጥንቃቄ ወደሃላ ይውጡ።

ጥሩንባን (ክላክስ) መጠቀም

ጥሩንባዎን እግረኞችን፣ ባለሳይክሎችን ወይም የሌላ ተሽከርካሪ ነጅዎችን በአደጋ (ኢመርጀንሲ) ግዜ ለማስጠንቀቅ ብቻ ይጠቀሙ። ጥሩንባው የፍሬንን ቦታ ለመተካት የታቀደ አይደለም። በአደጋ ግዜ (ኢመርጀንሲ) ካልሆነ በስተቀር ጥሩንባዎን "የጸጥታ ስፍራ" ("Quiet Zone") ተብሎ በተለጠፈ ስፍራ ላይ መቼም አይጠቀሙ። አደጋ (ኢመርጀንሲ) በሌለበት ግዜ ሞተር አሽከርካሪን፣ ባለሳለይክልን ወይም እግረኛን እርሶ እየመጡ መሆኖን ለማሳወቅ ሲሉ ጥሩንባዎን አይጠቀሙ። ጮክ ያለ ጥሩንባ ባለሳይክል ቁጥጥሩን እንዲስት ሊያደርገው ይችላል።

ከጋራጅ ወይም መግቢያ (ድራቨዌይ) ሲነሱ

- በቅርብ ላሉ ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች ይጠንቀቁ
- አግባብ ባለው ፍጥነት ከትራፊኩ(ከመኪኖች) ጋር ለመቀላቀል በጥንቃቄ ይሂዱ
- ወደሃላዎ መውጣት ሲኖርቦት ከመኪናዎ ሃላ ማየቶን ያረጋግጡ። በመንገዶ ላይ ምንም እንደሌለ ለማረጋገጥ ከመኪናዎ መውጣት ይኖርቦት ይችል ይሆናል።
- ወደሃላ በመሄድ ላይ እያሉ በመስታዋቶቹ በኩል እና ጭንቅላቶትን ወደሃላ በማዞር በመስኮቶቹ ወደ ውጭ በማየት በጥንቃቄ ከመኪናው በሃላ ያለውን ይመልከቱ
- መንገዱ ውስጥ ከመግባቶ በፉት ያቁሙ እና ከመቀጠሎ በፉት እንደገና ይዩ

በልዩ ሁኔታ ላይ የሚደረግ የእጅ ምልክቶች

ጸሀይዋ ደምቃ ስታበራ እና ልክ ከሃላዎ ያሉት ተሽከርካሪዎች የመታጠፊያ ምልክትዎን ሲከልሉት፣ ከመታጠፊያዎ ምልክት በተጨማሪ የእጅ ምልክቶችን ይጠቀሙ።

ተሽከርካሪው ውስጡ ሲጨናነቅ

በሚነዱበት ወቅት በፍጹም ተሳፋሪዎች ወይም እሽጎች እንዲያጣብቦት አይፍቀዱ። ተሽከርካሪ ውስጥ ያለ ማንኛውም ነገር በሁሉም አቅጣጫ እይታዎን እንዲከልሉ በፍጹም አይፍቀዱ። በመንዳት ወቅት ወደሃላ ማያው መስተዋት ላይ አንድን ነገር ማያያዝ ወይም ማንጠልጠል የዲስትሪልት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ደንብን የሚጻረር ነው።

የቤት እንስሳት

በሚነዱበት ወቅት የቤት እንስሳትን ከእርሶ ያርቁ። ታፋዎ ላይ እንዲቀመጡ ወይም ከሹፌሩ መስኮት በኩል ንጹህ አየር እንዲቀበሉ አይፍቀዱላቸው። መቼም ቢሆን የቤት እንስሳትን የሚጠብቃቸው ሳይኖር ተሽከርካሪዎ ውስጥ አይተዋቸው።

የላሉ ነገሮች

የላሉ ነገሮች፣ በተለይም በፊት ዳሽ ቦርድ እና በሃላ የመስታዋት መደርደሪያ ላይ ያሉ በአደጋ ወቅት ሊወረወሩ ይችል ይሆናል። የላሉ ነገሮችን በእቃ መጫኛው(ትራንክ) ወይም በመሬቱ ላይ ያድርጉት፣ ወንበር ላይ የተቀመጡ ነገሮች እንኳን በረው እርሶን ወይም ሌላ ተሳፋሪን ሊመቱ ይችሉ ስለሚሆን። እንደ ጉረሰሪ ከረጢት የመሳሰሉ የሚወድቁ ነገሮች ሊያዘናጋዎት እና አይኖትን ከመንገድ ላይ እንዲያነሱ ወይም እጆትን ከመሪው እንዲያነሱ ሊያደርጎት ይችሉ ይሆናል። ፍሬኑ ወይም ነዳጅ መስጫ ፔዳሎች ጋር ሊያደናቅፉ የሚችሉ ነገሮችን ከመሬቱ ላይ ያንሱ።

የቆሙ መኪኖችን አልፍ መንዳት

የቆሙ መኪኖችን አልፈው ሲነዱ ለሚከፈቱ የመኪና በሮች፣ ከመኪኖች ወይም ከቢስኪሌቶች መሀከል ወጥተው ወይም እየሮጡ ለሚመጡን እግረኞች(በተለይ ለልጆች) ይጠንቀቁ።

የመንዳት ሁኔታዎች

ፍጥነት መቼ እንደሚቀነስ

የሚከተሉት ሲሆን ማብረድ አለቦት:

- መገናኛ መንገድ ላይ፣ የባቡር ሀዲድ መንገዱን ሚያቋርጥበት ላይ፣ ከርብ ላይ፣ ወይም የቁልቁለት ላይኛው ጫፍ ላይ ሲደርሱ፣
- የልጆች መጫወቻ ቦታ ወይም ትምህርት ቤቶች ወይም ልጆች የሚጫወቱበት ቦታ አጠገብ ሲደርሱ፣
- ጠባብ ወይም ጠመዝማዛ መንገድ ላይ ሲጓዙ
- ለእግረኞች አደጋኛ ሁኔታ ሲኖር፣ እና
- የአየር ወይም የሀይዌው ሁኔታ፣ ወይም የራሶ ሁኔታ ለደህንነት ዝግ ያለ ፍጥነት የሚያስፈልገው ሲሆን። ሌሎች በአግባብ ፍጥነት የሚጓዙ ተሽከርካሪዎችን እስከሚያስተኃጉሉ ድረስ መቼም ቢሆን በጣም ቀስ ብለው አይንዱ። በጣም ቀስ ብለው በመንዳት ሌሎች ተሽከርካሪዎችን(ትራፊኩን) የሚዘጉ ወይም የሚያስተጓጉሉ ነጅዎች ለአደጋዎች ምክንያት ሊሆኑ ይችላል።

እርጥብ መንገዶች

እርጥብ መንገዶች ከደረቅ መንገድ በጣም በበለጠ ሁኔታ ያንሸራትታሉ። መንገዱ እርጥብ ሲሆ መጠመዘዣ (ከርብ) ላይ መሬቱን ለመያዝ እጅግ በበለጠ ሁኔታ ከባድ ነው እናም ለማቆም የበለጠ ረጅም ርቀት ይወስዳል። በተለይ ቀላል ዝናብ በሚጀምርበት ግዜ ይጠንቀቁ፣ መንገዱ ላይ የሚሆነው የዘይት እና ውሀ ቅልቅል በይበልጡን አደገኛ ነው። ከብዙ ሰአታት ዝናብ በሃላ እነደሚሆነው ዘይቱ እና ሌሎች የተሽከርካሪዎች ፈሳሾች ገና ታጥበው አልሄዱም። በተመሳሳዩ፣ በልግ (አተም) ላይ መንገዱ ላይ ለሚኖሩት እርጥብ ቅጠሎች ይጠንቀቁ።

የጎማ መንሸራተት (Hydroplaning) እና ጎርፍ

ፍጥነት በሰአት 35 ማይልስ ድረስ ሲጨምር፣ ብዙ ክርክር(ትሬድ) ያላቸው ጎማዎች፣ የመስታዋት ዋይፐር መስተዋቱን እንደሚያጸዳው አይነት፣ መንገዱን "ይጠርጉታል"። ፍጥነት እየጨመረ ሲመጣ፣ የጎማዎቹ መጥረግ ስራቸው ውጤታማነቱ እየቀነሰ ይመጣል እና ጎማዎቹ የውሀ ክምችቱ ላይ መጓዝ ይጀምራሉ፣ ልክ እንደ ውሀ ሰኪይን። ይሄ "ሀይድሮፐላኒንግ" ("hydroplaning") ተብሎ ይጠራል።

ይህ በሚከሰትበት ወቅት ፍሬን መያዝ፣ ፍጥነት መጨመር ወይም በትክክል መዞር አይችሉም። ከቁጥጥሮ ውጪ መሆኑ እንዳወቁ ወዲያውኑ እግሮቱን ከነዳጅ መስጫው ፔዳል ላይ ያንሱ እና መሪውን መሄድ ወዳሰቡበት አቅጣጫ አጥብቀው ይያዙት። ተሽከርካሪዎን መልሶ ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሮ ስር እስኪሆን ድረስ የተሽከርካሪው ፍጥነት እንዲቀንስ ይፍቀዱ።

ጎርፍ ሀይለኛ ዝናብ በሚኖርበት ወቅት ሊከሰት ይችላል። ፈጣን ወራጅ ጎርፍ በፍጥነት እና ሳይጠበቅ ሊመጣ ይችላል። ከከፍተኛ ዝናብ በሃላ ከትንሽ ደቂቃ ወይም ሰአታት ውስጥ ሊከሰቱ ይችላል። ጎርፍ ባለበት አካባቢ ውስጥ አይንዱ። ከፊት ለፊቶ ጎርፍ ያለው መንገድ ካዩ፣ ወደሃላ ይዙሩ እና ወደ መድረሻዎ የሚወስዶት ሌላ መንገድ ይፈልጉ። ጥንቁቅ ይሁኑ፣ በተለይ እይታ የተወሰነ በሚሆንበት በምሽት ወቅት። ከተሽከርካሪው በታቹ ያለው ውሀ ስድስት ኢንች ከደረሰ፣ መቆጣጠር ላይቻል ወይም ሊቆምም ይችላል። ሁለት ጫማ(ፊት) የሆነ ተጋዝ ውሀ አብዛኛዎቹን ተሽከርካሪዎች፣ ስፖርት ዩቲሊቲ ተሽከርካሪዎችን እና ፒክ አፕ ትራኮችን ጨምሮ ተሽክሞ ሊወስድ ይችላል። ውሀው ለመሻገር ዝቅ ያለ መስሎ ቢታይም፣ ጎርፍ ያለበትን መንገድ ለመሻገር አይሞክሩ። ውሀ ያቆረውን ሊደብቅ ይችላል፣ ወይም ከዚህ በከፋ መልኩ የውሀ ጎርፍ ከላይ ያለውን የመንገድ መሬት አጥቦ በመውሰድ መንገዶችን ሊያበላሽ ይችላል። ሌላ አማራጭ መሄጃ መንገድ ከሌለ፣ ከፍ ወዳለ ቦታ ይቀጥሉ እና ውሀው እስኪቀንስ ይጠብቁት።



የመከተያ ርቀት

በድንገት መቆም እንዲቻል በእርሶ ተሽከርካሪ እና ከፊቶ ባለው ተሽከርካሪ መሀከል በተቻሎት መጠን ብዙ ያህል ቦታ ይተዉ። አብዛኛዎቹ የሃላ ግጭቶች የሚፈጠሩት በጣም በቅርበት በመከተል ነው። ከፊቶ ያለው መኪና ምልክት ወይም ከታች ማለፉያ የመሳሰለ የመለያ ነጥቦችን ሲያልፍ ይመልከቱ። ከዚያ "አንድ ሺ አንድ፣ አንድ ሺ ሁለት፣ አንድ ሺ ሶስት፣ አንድ ሺ አራት" እያሉ ይጠሩ። እስከ አንድ ሺ አራት ቆጥረው ሳይጨርሱ ያንን ነጥብ ቦታ ካለፉት በጣም በቅርቡ እየተከተሉ ነው ማለት ነው። ቶሎ ቶሎ የሚቆሙ ተሽከርከሪዎችን ሲከተሉ(ባሶች፣ የፖስታ ቤት ቫን) ከወትሮወ የበለጠ የመከተያ ርቀት መስጠት አለቦት።

በመጥፎ የአየር ሁኔታ ሲነዱ በእርሶ ተሽከርካሪ እና ከፊቶ ባለው መሀከል ያለውን ርቀት በአራት ወይም አምስት ሰከንዶች መጨመር አለቦት።

ያስታውሱ ትራኮችን አቋርጠው አይቅደሙ። ትራኩ ለመቆም በጣም የበለጠ ሰአት እና ርቀት ይፈጅበታል።

ከሶስት እስከ አራት ሰከንድ የመከተያ እና የማቆሚያ ርቀት ደንብ

ደህንነትን የሚያስጠብቅ የመንጃ ፍጥነትን ለመምረጥ እንዲረዳዎት፣ ተሽከርካሪዎን ማቆም የሚችሉበት ርቀት መጠን አስፈላጊ ነው።የሚከተለው እንደ ግምታዊ መመሪያ ተደርጎ ሊጠቀሙበት ይችላል፣ ነገር ግን በእርግጥ የማቆሚያ ርቀቶ በብዙ ነገሮች ላይ ይወሰናል፣ ከነዚህ መሀከል፡

- አደገኛ ሁኔታ እንዳለ ለማየት እና ለማስተዋል አንድን ነጂ የሚወስድበት የግዜ ርዝመት
- አደጋ መኖሩ ከተስተዋለበት ግዜ አንስቶ ፍሬኑን መያዝ እስኪጀመር ድረስ ያለው የግዜ ርዝመት – 3-4 ሰኮንዶች
- የመንገዱ አይነተ እና ሁኔታ
- የመንገዱ ደረጃ ፐርሰንቴጅ
- የጎማው ክርክር(ትሬድ) አይነት እና ሁኔታ
- የመኪናው ዲዛይን እና የሾክ አብዞርበሩ ሁኔታ
- የፍሬኑ አይነት እና ሁኔታ
- የንፋሱ አቅጣጫ እና ፍጥነት

የማቆሚያ ርቀቶች የዩ.ኤስ. የትራንስፖርቴሽን ዲፓርትመንት (U.S. Department of Transportation) በሚያደርጋቸው መፈተኛዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። የነጅው እርምጃ መውሰጃ ግዜ በ 3-4 ሰከንድ እርምጃ መውሰጃ ግዜ ላይ የተመሰረተ ነው።

የተዘናጋ ነጂ ሲንድሮም

ችግሩ

መንዳት አደጋ ያለበት ተግባር ነው። በየአመቱ ከ 40,000 በላይ ሰዎች በተሽከርካሪ አደጋዎች ይገደለሉ እና ከሶስት ሚሊዩን በላይ ሰዎች ጉዳት ይደርስባቸዋል። ጥናት እንደሚጠቁመው ከሁሉም አደጋዎች ከ50 በመቶ በላይ የነጅዎች ትኩረታቸው አለመስብሰብ አስተዋጽኦ ያለው ምክንያት ነው። የነጅዎች አለማተኮር የመንዳትን ተግባሩ ላይ እንዴት ተጽእኖ አለው? የመንዳት አስተማሪዎች ነጅዎች ለእያንዳንዱ ለሚነዱት ማይል 200 ውሳኔዎችን እንደያደርጉ ይገምታሉ። በመንዳት ላይ እያሉ በአእምሮዎ የስራ ወይም የቤተሰብ ችግሮችን እየፈቱ ከሆነ፣ አእምሮዎ ላይ ካለው አጠቃላይ የስራ ሸክም እንደገና እየጨመሩበት ነው። ለሶስት ወይም አራት ሰከንዶች አይኖትን ከመንገዱ ላይ ካነሱ፣ የሚጓዙት በሰአት 55 ማይል ከሆነ

ተሽከርካሪዎ የአንድ እግር ኳስ ሜዳ ርዝመት ያህል ይጓዛል። እንደ ድካም፣ የአየር እና የትራፊክ ሁናቴ የመሳሰሉ ሌሎች ነገሮች በመንዳት ላይ አተኩሮ አለመኖር ላይ አሉታዊ ምክንያትን ሊጨምሩ ይችላሉ።

አይተናቸዋል– በመንገድ ላይ በመንዳት ላይ እያሉ ጋዜጣ የሚያነቡ፣ ሜካፕ የሚያደርጉ ወይም በሞባይል ስልክ ንግግራቸው ላይ ሀሳባቸውን የሚያተኩሩ ። እነዚህ የተዘናጉ ነጅዎች ግልጽ የሆኑ ምሳሌዎች ናቸው። ብዙ ሰዎችን ሊያስደንቅ የሚችለው ነገር መኪናችን ውስጥ የምናደርጋቸው ነገሮች እና ከዋናው የመንዳት ስራ ሀሳባችንን ሊሰርቁ የሚችሉ ነገሮች ብዛት ነው።

- መብላት፣ ለስላሳ መጠጦችን መጠጣት ወይም ማጨስ
- ራዴውን፣ ሲዲ ወይም ቴፕ መቀየር
- መላጨት፣ ሜካፕ ማድረግ፣ ወይም ሌላ የግል መሰናዳት ተግባር ላይ መግባት
- በሞባይል ወይም ከተሳፋሪ ጋር የሞቀ፣ የተወሳሰበ እና ስሜታዊ የሆነ ወይም ረጅም ንግግር ውስጥ መግባት
- የመንገዱን ካርታ፣ ጋዜጣ ማንበብ ወይም ኖት መውሰድ
- ሀሳብን ልጆች ወይም የቤት እንስሶች ላይ ማተኮር፣ በተለይ በመረበሽ ላይ ያሉት ላይ
- ያልጠበቁ ጭነቶችን ወይም ነገሮችን ማንሳት
- መጀመሪያ መስታዋቶቹን እና መቀመጫውን ሳያስተካክሉ፣ መዝናኛ አማራጮቹን ሳይመርጡ፣ እና መብራቱ፣ የመጠመዘዣ ምልክቶቹ እና የመስተዋት ዋይፐሮቹን ሳያገኙ ያለመዱት መኪናን መንዳት
- የሞባይል ስልኮችን መጠቀም

ድካም

ለረጅም መንገድ መንዳት ሊያደነዝዞት እና የሚሆነውን ነገር እንዳያውቁ ሊያደርግ ይችላል። መደንዘዝ እንቅልፍ የመውሰድ የመጀመሪያው ደረጃ ነው። የሚሆነውን ነገር አለማወቅ "ሀይዌይ ሂፕኖሲስ" ("highway hypnosis") ይባላል። ምክንያቱ በተመሳሳይ ድምጽ (ሞኖቶኒ) ነው – የንፋሱ፣ የጎማዎቹ ድምጽ እና አንድ አይነት የሆነው የሞተሩ ዝቅተኛ እና አንድ አይነት ድምጽ

- መጀመሪያ የመደንዘዝ ስሜት ሲሰማዎት፣ አንድ ነገር ያድርጉ። ቁጭ ብለው ዝም ብለው ሊታገሉት አይሞክሩ።
- በመጀመሪያው የማረፊያ ወይም የአገልግሎት ስፍራ ከሀይዌው ይውጡ እና ጋደም ይበሉ ወይም ትንሽ ሰውነቶን ያፍታቱ ወይም እረፍት ይውሰዱ፣ ወይም ከተቻለ ነጂ ይቀይሩ
- "አንቅቶ የሚያቆዩ" ("stay-awake") መድሀኒቶችን ላይ አይመርኮዙ። መንዳቶትን የበለጠ አደገኛ ነው የሚያደርጉት።
- የመኪናውን ውስጡን በተቻለ መጠን ቀዝቃዛ አድርገው ያቆዩት
- የሀይዌይ ሂፕኖሲስን (highway hypnosis) ለማስወገድ ነቅተው ለመቆየት ሙከራ ያድርጉ
- አይኖትን ከመንገዱ አንድ ስፍራ ወደሌላ፣ ቅርብ እና ራቅ ያለ ግራ እና ቀኝ እያዘዋረሩ ይቆዩ። ፉት ለፉቱ ላይ ማፍጠጥን ይተዉ።
- መቀመጫው ላይ ያሎትን አቀማመጥ ይቀይሩ።
- አብሮት ያለውን ሰው ያዋሩ ወይም ሬድዮ ያዳምጡ።
- የተሽከርካሪዎን ፍጥነት ከግዜ ወደ ግዜ በትንሹ ይቀያይሩት።

የደነዘዙ ነጅዎች የአደገኝነት ምልክቶች

- አይኖት ይዘጋሉ ወይም ከአትኩረታቸው በራሳቸው ይወጣሉ
- ጭንቅላቶትን ቀና አድርገው ለማቆነት ያስቸግሮታል
- ማዛጋቶን ማቆም ያቅቶታል
- የተዘበራረቀ፣ ያልተያያዙ ሀሳቦች አሎት
- ላለፉት ትንሽ ደቂቃዎች ሲነዱ አያስታውሱም
- መውጫዎን(ኤግዚቶን) አልፈውታል
- ከመስመሮ ውጪ እየወጡ ደጋግመው ይነዳሉ
- ፍጥነቶ የተለያየ ይሆናል

በመንዳት ላይ እያሉ ከደከሞት ወይም እንቅል እንቅልፍ ካሎት ማረፍ ከሁሉ የተሻለ ነው፣ ወይም የሚቻል ከሆነ ነጂውን ይቀይሩ። መድከም ጭንቅላቶትን ያነፍዛል እና መውሰድ ያለቦትን እርምጃ ያዘገየዋል፣ ይሄ መንዳትን አደገኛ ያደርገዋል። ህይወቶች በጥያቄ ውስጥ እንደሚገቡ ያስታውሱ።

አትኩሮት

ደህንነቱ ለተጠበቀ አነዳድ አትኩሮት በዋነኝነት አስፈላጊ ነው። መንዳት የሙሉ ሰአት ስራ ነው። ያለማቋረጥ መንገዱን እና በአካባቢዎ ያሉትን ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ማስተዋል አለቦት። ነቅተው ይቆዩ እና አደጋን አስቀድመው ሊያዩ እና ሊያስወግዱት ይችሉ ይሆናል። በመንዳት ላይ እያሉ ሬዲዮውን አያስተካክሉ፣ አያንብቡ፣ ሜካፕ አያድርጉ፣ አይላጩ፣ ወይም እጅን ነጽ የሚያደርግ መሳሪያ ሳይጠቀሙ ሞባይልን አይጠቀሙ። በየግዜው ከሃላዎ ያለውን ተሽከርካሪ ያስተውሉ፣ እንዲሁም ከጎኖ እና ከፊቶ ያሉትን።

ስሜቶች መንዳት ላይ ተጽኖ ያደርጋሉ

ተበሳጭተው ወይም ተናደው ከሆነ፣ ከመንዳቶ በፉት ትንሽ ግዜ ይውሰዱ፣ወይም ሌላ ሰው እንዲነዳ ያድርጉ። ስሜቶ በተበሻጨበት ወቅት ፈጽሞ ባይነዱ ይሻሎታል። እየነዱ እያሉ ስሜቶትን መግለጽ አደገኛ ነው።

የእጅ(ሞባይል) ስልኮች

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከሞባይል ስልክ ጋር ለመንዳት እጆቶ ነጻ መሆን አለባቸው። ያስታውሱ፣ እየነዱ ቴክስት ማድረግ በፍጹም አይፈቀድም!

ሀሳብ ለመበታተን መፍትሄ

ሀሳብ መበታተንን ደህንነት በጠበቀ መንገዱ መቆጣጠር እንዲችሉ ለመርዳት የመፍትሄ ሀሳቦች:

- ተሽከርካሪውን ማንቀሳቀስ ከመጀመሮ በፉት ሁሉኑም ሰው እና ሁሉኑም ነገር ያጥብቁ።
- የሙቀት መቆጣጠሩያውን፣ ሬዲዮውን፣ ካሴት ወይም ሲዲ ማጫወቻውን ቀድመው ያስተካክሉ። የመታጠፊያ ምልክቶች፣ ዋይፐሮች፣ እና መብራቶች ተሽከርካሪው የቱ ጋር እንደሚገኙ ይወቁ።
- ጋዜጣ፣ የቢዝነስ ሪፖርት ወይም የቀን እቅድ ማውጫን ለማየት የሚፈታተኖ ከሆነ፣ መድረሻዎ ጋር እስኪደርሱ ድረስ የእቃ መጫኛው(ትራንክ) ውስጥ ያስቀምጧቸው።
- ከመሪ ሃላ ሆነው የግል መሰናዳት ተግባር ላይ አይግቡ።
- የሚወስዱትን መንገድ እቅድ ለማውጣት መንዳት እስከሚጀምሩ ድረስ አይጠብቁ። ከመነሳቶ በፊት እቅድ ያውጡ። ቀደም ብለው ይነሱ እና መድረሻዎ ላይ ደህንነቶ ተጠብቆ እና ብዙ ሳይጨነቁ ይደርሳሉ።
- ውስብስብ ወይም ስሜታዊ የሆኑ የስልክ ወይም ከተሳፋሪዎች ጋር የሚደረጉ ንግግሮችን መድረሻዎ ላይ እስኪደርሱ ድረስ ያቆዩት።
- ተሳፋሪ ሀሳቦን እያበታትነው ከሆነ ደህና በሆነበት እና ህጋዊ በሆነበት ቦታ ላይ ያቁሙ ።
- ሁኔታው በቁጥጥር ውስጥ እስኪሆን ድረስ መንዳት አይጀምሩ።
- ሲርቦት ወይም ሲጠማዎት እረፍት ይውሰዱ።

የጎዳና ላይ ብስጭት እና ሀይለኛ አነዳድ

የመንገዳችን ሲስተም የጥቅም ፍጆታው በ2020 40 በመቶ እንደሚጨምር እና የመንገዱ አቅም በ 9 በመቶ ብቻ እንደሚጨምር ይጠበቃል። የዘንድሮ ነጅዎች ከ 20 አመታት በፊት ከነበረው እጥፍ የመኪና ቁጥር በመደበኛ ሁኔታ የሚያስተናግደው መንገዳችን ላይ መበሳጨታቸው እየጨመረ መጥቷል። የሚጨናነቀው ሰአታት(ራሽ አወር) ትራፊክ፣ ቁጥሩ እየጨመረ የመጣው የግንባታ ስፍራዎች(የስራ ዞኖች) እና የመኪና አደጋዎች የነጅዎች ብስጭትን ይጨምራሉ።

ዋናዎቹ አጥፊዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ጭራ ጭራን መከተል
- ደህንነት ባልተጠበቀ መልኩ መስመርን መቀየር
- ፍጥነት
- ቀይ መብራቶችን እና ማቆሚያ(STOP) ምልክቶችን መጣስ

የመንገድ ላይ ብስጭትን እና ሀይለኛ አነዳድን ለመቀነስ ቀላል ደንቦች

- ሁልግዜ ተጨማሪ የመጓዛ ግዜ ይስጡ
- በአንዴ ከሶስት ሰአታት በላይ መሪ ይዘው አይቆዩ
- በወቅቱ በማቆም ግጭትን ለማስወገድ እንዲችሉ ከፉቶ ካለው ተሽከርካሪ በቂ ርቀት ሆነው ይቆዩ
- ሁልግዜ ሲታጠፉ ወይም መስመር ሲቀይሩ ሀሳቦት ለማሳወቅ ምልክት ያድርጉ
- ቀይ መብራቶች ላይ ወይም የማቆሚያ (ስቶፕ) ምልክቶች ላይ ሙሉ በሙሉ ይቁሙ። ቢጫ መብራቶችን አልጣሱ።
- ሌሎች ነጅዎች መንገዱ ላይ ስርአት ባለው መንገድ እንዲገቡ ያድርጉ
- የማለፊያ መስፈሮችን(ሌኖችን) አይዝጉ
- ለተለጠፉት የፍጥነት ገደቦች ታዘዙ
- መንዳቶ ላይ ሀሳቦን ያሰባስቡ – የሞባይል ስልክ፣ ሙዚቃ፣ ተሳፋሪዎች ወይም ሌላ ሀሳብ ሚበትኑ ነገሮች ላይ ሳይሆን

- ጥሩንባዎን በአደጋ(ኢመርጅነሲ) ግዜ ሌሎችን ነጅዎችን ወይም እግረኞችን ለማሳወቅ ብቻ ይጠቀሙበት
- መጥፎ ፉት ምልክት ማድረግ ወይም ስርአት የሌለው፣ ባለጌ ምልክቶችን የመሳሰሉ አግባብ የሌለው ባህሪ ላይ በፍጹም አይሳተፉ
- አይን ለአይን መተያየትን ያስወግዱ
- ለሌሎች ነጅዎች በሁሉም ግዜያት የተለመደውን አክብሮት ይስጡ። መንዳትን በተሻለ ሁኔታ ደህንነት የተጠበቀበት፣ ባነሰ ሁኔታ የሚያስጨንቅ አና የበለጠ የሚያስደስት ተሞክሮ ለማድረግ ሁሉም ነጅዎች የራሳቸውን ድርሻ መወጣት አለባቸው።

ልዮ የመንዳት ሁኔታዎች

በምሽት(በለሊት) መንዳት

በምሽት መንዳት በቀን ከመንዳት ይልቅ ይከብዳል እና በይበልጡን አደገኛ ነው። በጠቅላላ ብሄራዊ ደረጃ በአንድ ማይል መንዳት ያለው በምሽት የሚሆነው የሞት አደጋ መጠን ሁለት-እና-የአንድ ግማሽ ያህል ከቀኑ ይበልጣል። በምሽት ግዜ ነጅው ከርቀት፣ በፍጥነት ወይም በደንብ ያን ያህል አያይም እና ሁሉም ነገር የተለየ እይታ አለው። የሚወጡት የመኪና መብራት ጮራ ከፊት ለፊት ያለው ምን እንደሆነ የማየት ችግሩን በጣምኑ ይጨምሩታል፣ በተለይ እድሜያቸው ከር ላለ ነጅዎች። ጮራዎቹ የአይናችን ብሌን እንዲኮማተሩ ያደርጓቸውና ዝቅ ያለ መብራት ላይ ወደ ቦታቸው ለመመለስ ግዜ ይወስዳል። ከሚመጣ የመኪና መብራት ጮራን ለማስወገድ፣ በመንገዱ ጎኖች እና ቀጥታ ወደፊት እያቀያየሩ ይመልከቱ። ከዚህ ነገር ሲወጡ፣ የማየት ችሎታዎ ቀንሶ ሊሆን ይችላል። የሚከተሉትን በማድረግ በምሽት መንዳቶን በተሻለ ሁኔታ ደህንነት የሚያስጠብቅ ሊያደርጉ ይችሉ ይሆናል፡

- ወደፉት ሊያዩበት በሚችሉት ርቀት መጠን ማቆም እስኪያስችሎት ድረስ ፍጥነቶች ቀንሰው ያቆዩ
- ሌሎቹ ተሽከርካሪዎች ላይ ሲደርሱ የመኪናቸው የፊት መብራቶች ላይ አያፍጥጡ። የሚከተሉትን ለማድረግ ፈጣን እይታ ያድርጉ:
  - የሚመጣውን ተሽከርካሪዎች ያሉበትን መስመር ማወቅ

- እራሶት ያሉበትን ማወቅ
- ስለ መንገዱ የቀኝ ጠርዝ እርግጠኛ መሆን
- በመስመሮ ላይ ያሉ ነገሮችን ቀጥታ ይመልከቱ
- የፉት መስተዋቶትን ንጹህ ያድርጉ። የፉት መስተዋቶ ንጹህ ከሆነ፣ የሚመጡት መኪኖች ሙብራቶች ያን ያህል አያስቸግሮትም።
- በምሽት የጸሀይ መነጸር አያድርጉ
- ሳይተኙ እና ነቃ ብለው ይጠብቁ። ንጹህ እና ቀዝቃዛ አየር ይረዳል።
- እንዲመራዎት የመንገዱን ጠርዝ ይጠቀሙ። የመንገድ የጠርዝ የተሰመረ መስመር ከሌለው፣ የመሀከለኛውን መስመር እንዲመራዎት ይጠቀሙበት።
- የሀይዌይ ምልክቶችን በጥንቃቄ ይመልከቱ። በምሽት ለማየት በይበልጥ ይከብዳሉ።
- በምሽት ግዜ በተለይ ለእግረኞች እና ለቆሙ ተሽከርካሪዎችን ይጠንቀቁ።
- በምንም ምክንያት እመንገዱ ላይ አይቁሙ።
- በመንገዶች መሀከል መቆምን ማስወገድ የማይቻል ከሆነ ቀይ የማስጠንቀቂያ ሙብራት ወይም የሚብለጨለጭ ሙብራት(ፍሌር) ይያዙ።
- መስኮቶቹ ተዘግተው ተሽከርካሪ በሚነዱበት ወቅት ማጨስን ይቀንሱ።

በዊንተር መንዳት

በዊንተር መንዳት ልዮ ጥንቃቄ ይጠይቃል።

- የሰንሰለት፣ የበረዶ ጎማዎች ወይም ራዲያል ጎማዎችን ይጠቀሙ። ሰንሰለቶች በአብዛኛው ቆንጥጦ መያዝን እና በረዶ(አይስ) ወይም ብናኝ በረዶ(ስኖ) ላይ ማቆምን የተሻለ ያደርጋሉ። ቢሆንም፣ ሰንሰለትም ወይም ራዲያል ወይም የበረዶ ጎማዎችም በበረዶ ወይም ብናኝ በረዶ በተሸፈነ መንገድ ላይ በመደበኛ ፍጥነት መንዳትን ደህነት የሚያስጠብቅ አያደርጉለትም። ዝግ ማለት አለቦት።
- ሰንሰለቶች፣ የበረዶ ጎማዎች ወይም ራዲያል ጎማዎች የበረዶ ኢመርጀንሲ ሲታወጅ የተሰየሙት የኢመርጀንሲ መንገዶች ላይ ብቻ ነው ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው።

- መስኮቶችን እና መብራቶችን ንጹህ ያድርጉ። ሁሉኑም በረዶ እና ብናኝ በረዶ ያስወግዱ እና ያነሱት ይቆዩ።ተሽከርካሪው ውስጥ የበረዶ መፈቅፈቂያ ያስቀምጡ።
- መንገዱ ምን እንደሚመስል ለማወቅ ይሞክሩት። በጣም ቀስ ብለው ይጀምሩት። ከዛ ፍሬኖት ምን ያህል ማቆም እንደሚችሉ ለመፈተን ቀስ ብለው ይሞክሩት። መገናኛ መንገድ(ኢንተርሴክሽን) ላይ ከመድረሶ ወይም ከመታጠፎ በደንብ ቀደም ብለው ማብረድ ይጀምሩ።
- ደህንነትን በሚያስጠብቅ መልክ ርቀቶትን ይጠብቁ። በረዶ እና ብናኝ በረዶ ሲከማች በእርሶ እና ከፊት ለፊቶ ባለው መኪና መሀከል ሊኖር የሚያስፈልገው ርቀት በጣምኑ የበለጠ ነው። የበረዶ ጎማዎች፣ ራዲያል ጎማዎች እና ሰንሰለቶች እንኳን ቢሆን በበረዶ እና በተጠራቀመ ብናኝ በረዶ ላይ ይንሸራተታሉ።
- ፍሬኑን በጣም አይምቱት።
- መሪዎን በጣም አይጠምዝዙ ወይም ፍጥነቶን በቶሎ አይቀይሩ
- ተሽከርካሪዎ ውስጥ የአደጋ ግዜ ሳጥን(ኢመርጀንሲ ኪት) ያስቀምጡ። የሚከተሉትን ሊያካትት ይገባል:
  - የሚብለጨለጩ መብራቶች(ፍሌርስ)
  - የመጀመሪያ ደረጃ እርዳታ ቦርሳ(ፈርስት ኤድ ኪት)
  - ብርድ ልብስ
  - የድመት አፈር(ኪቲ ሊተር) ወይም አሸዋ –ብናኝ በረዶ/በረዶ ላይ ቆንጥጦ እንዲይዝ
  - ትንሽ አካፋ
  - ነዳጅትን ሞልተው ያስቀምጡ
  - የመስኮት ፈሳሾችን ሞልተው ያስቀምጡ

በበረዶ ላይ "ሙሉ በሙሉ ደንህንነት የተጠበቀበት (ሴፍ የሆነ)" ፍጥነት ብሎ ነገር የለም
በዊንተር የአየር ሁኔታ፣ የእያንዳንዱ ከተማ ብሎክ እና የእያንዳንዱ ሀይዌይ መንገድ እንደ ጸሀዩ፣ እንደ ከለላው፣ እንደሚደረገው የጨው መጠን እና በሌሎች ሁኔታዎች መሰረት የተለያየ ሊሆን ይችላል። ለአደገኛ ቦታዎች በጥንቃቄ ከፊት ለፊቶ ይዩ። ጥቁር ሽፋን ያላቸው መንገዶች [አስፋልት ሀይዌዎች] በመቅለጥ እና መልሶ በመቀዝቀዝ የሚሰራ ቀጭን የበረዶ ክምርን (አንዳንድ ግዜ ጥቁር በረዶ ተብሎ የሚጠራው) በቀላሉ ሊደብቁ ይችላሉ እና አደጋገኝነቱን ካላወቁት አደጋ ሊያስከትል ይችላል።

ያስታውሱ: ከሀይዌዮች እና መንገዶች በፊት መሸጋገሪያዎች(ራምፕስ) እና ድልድዮች ቀድመው በረዶ ይይዛሉ። በተጨማሪም የተጠረጉ መንገዶች ለሊት ላይ በረዶ ሊይዙ ወይም የቀን ጸሀይ በረዶውን በማቅለጡ ምክንያት ትንሽ የቀረ በረዶ ሊሰራ ይችላል። ፎር ዊል ድራይቭ ተሽከርካሪዎችም ጭምር በረዶ ላይ ይንሸራተታሉ። የሚነዱት ፎር ዊል ድራይቭ ከሆነ በደረቅ መንገድ ላይ እንደሚነዱት ያህል በበረዶ(ኤይስ) እና በትናኝ በረዶ(ስኖው) ላይ መንዳት እችላለሁ ብለው ግምት አይውሰዱ።

አንታይ ሎክ ብሬክ ሲስተም (Anti-Lock Brake Systems)

ተሽከርካሪዎ መንሸራተት ከጀመረ እና አንታይ ሎክ ብሬክ ሲስተም (anti-lock brake system) ካለው ፍሬኑን ፓምፕ አያድርጉት። በምትኩ፣ ተሽከርካሪዎን ከመንሸራተቱ መልሰው መቆጣጠር እንዲችሉ ፍሬኑ ላይ በአንድ ሀይል ይጫኑት።

መንሸራተትን መከላከል

- በፍጥነቱ ላይ ወይም በአቅጣጫው ላይ የድንገተኛ ለውጥን ያስወግዱ። በእግሮ እና በነዳጅ ወይም በፍሬን ፔዳሉ መሀከል እንቁላል እንዳሎት አድርገው ይንዱ።
- የተጠራቀመ የበረዶ ብናኝ ወይም በረዶ ላይ ለመንዳት ከመሞከሮ በፊት ማቆምን እና ከመንሸራተት መመለስን ደህንነትን በሚያስጠብቅ ቦታ እና በግል ንብረት ላይ ዝግ ባለ ፍጥነት ይለማመዱ
- የማቆሚያ ነጥብ ከመድረሶ በፉት በደንብ ቀደም ብለው ፍጥነት ይቀንሱ።
- በሀይል ፍሬን አይያዙ እና ጎማውን(ዊል) አይቆሉፉት። ጎማው(ዊል) የማይዞር ከሆነ ተሽከርካሪውን መቆጣጠር አይችሉም። አንታይ ሎክ ብሬክ ሲስተም የሌላቸው ተሽከርካሪዎች ላይ የፍሬን ፔዳሉን ፓምፕ ያድርጉት።
- የመንገድ ሁኔታዎቹ መጥፎ ሲሆኑ፣ መቸኮልን ለማስወገድ ወትሮ ከሚወጡበት ሰአት ቀደም ብለው ይውጡ።

መጠምዘዣዎች(ከርቦች)

ከርቦች ማምለጥንን እና መንሸራተትን ስለሚያስከትሉ ይጠንቀቁባቸው፣ በተለይ ቆንጥጦ የመያዝ ችሎታው(ትራክሽን) መጥፎ ሲሆን። በእርጥብ የአየር ሁኔታ ላይ በይበልጥ ለከርቦች ይጠንቀቁ፣ በብናኝ በረዶ(ስኖው) ላይ የበለጠ ጥንቃቄ እና በበረዶ(አይስ) ላይ ከሁሉ የበለጠ ጥንቃቄ ያድርጉ። ከርቭ ላይ ከመግባቶ በፉት ደህንነት ወደሚያስጠብቅ የፍጥነት መጠን ይቀንሱ። በጥሩ የአየር ሁኔታ ላይ በሰአት 35 ማይል ተብሎ በተለጠፈበት ከርቭ ላይ እርጥብ አየር ላይ ደህና ፍጥነት በሰአት 20 ማይል ብቻ ሊሆን ይችላል እና በበረዶ እና በብናኝ በረዶ(ስኖው) ግዜ በሰአት 5 ማይል ብቻ ሊሆን ይችላል።

ከመንሸራተት መመለስ

- አይደንግጡ እና ፍሬን አይያዙ
- ወዲያውኑ በተንሸራተተበት አቅጣጫ ያዙሩት። የሃላ ጎማዎቹ ወደቀኝ መሄድ ከጀመረ፣ የፊት ጎማዎን ወደቀኝ ያዙሩ። እግሮን ከነዳጅ መስጫ ፔዳል(ፍጥነት መጨመሪያ) ይንሱት።

በጭጋግ ውስጥ መንዳት

ጭጋግ በመሬት ደረጃ እንዳለ ደመና ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል። የአየሩ ሁኔታ እስከ ጤዛነት (አየሩ የሚሞላበት የአየር ሁኔታ መጠን) ድረስ ሲወድቅ እና የማይታዩ የውሃ ትናኞች የተንጠለጠሉ የውሀ እንጥብጣቤዎች ለመፍጠር ሲቀየር ይፈጠራል። ጭጋግ እይታን እስከ ¼ ማይል ወይም ከዚያ ያነሰ ድረስ ሊቀንሱት ይችላሉ፣ አደገኛ የመንዳት ሁኔታንም ይፈጥራሉ። ጭጋጋማ ሲሆን፣ ጭራሹኑ አለመንዳት ይሻላል፣ ነገር ግን ግዴታ ከሆነቦት እነዚህ የደህንነት ጥንቃቄዎች ይረዳሉ:

- የመንጃ ፍጥነቶን ከወትሮው ይቀንሱ። የፊት መብራት ወይም የሃላ መብራት ሲያዩ እንደውም የበለጠ ፍጥነት ይቀንሱ።
- የፊት መብራቱ በመንገዱ መሀከል ላይ የሚነዳ ተሽከርካሪ ሊሆን ይችል ይሆናል። የሃላ መብራት ያለበት ተሽከርካሪ በመንገዱ ጎን ላይ ወይም አጠገብ ቆሞ ወይም ልክ የቆመ ያህል በትንሹ እየሄደ ሊሆን ይችላል።
- ለድንገተኛ መቆም ዝግጁ ይሁኑ።
- ጭጋጉ በጣም ጥቅጥቅ ያለ ከሆነ ቢያንስ 10 mph መሄድ የማይችሉ ከሆነ፣ ሙሉ በሙሉ ከሀይዌው ይውጡ ወይም በማረፊያ ስፍራ፣ የአገልግሎት ጣቢያ ወይም ሌላ የማቆሚያ ቦታ ያቁሙ።
- ትንሹን የፋት መብራት፣ ወይም ካሎት ልዮ የሆኑትን የጭጋግ መብራቶች ይጠቀሙ።
- ከፍተኛ መብራት ያለው ብዙ ግዜ መልሶ አይኖ ላይ ያንፀባርቃል እና ያሳውሮታል።
- በምሽት ሲነዱ፣ የመንገዱን ጠርዝ መስመሮች ወይም የመንገዱን የቀኝ በኩል እንደ መምሪያ ይጠቀሙበት። በጣም እስኪዘገይ ድረስ የሀይዌ ምልክቶችን ላያዩት ይችላሉ። ቢጫ የአስፋልት ላይ ምልክቶች በፍፁም በቀኞ በኩል ሊሆን አይገባም፣ ነገር ግን ሁልግዜ በግራዎ በኩል እንጂ።
- ቢጫ በተቃራኒ የሚሄዱን የመንገድ ትራፉክ ለመለየት የሚጠቅም ነው እና የመንገዱን የግራውን የትራፊክ ጠርዝ ያመለክታል። ነጭ የአስፋልት ላይ ምልክቶች የቀኝ የመንገዱን ጠርዝ ይወክላሉ።
- መቸኮልን ለማስወገድ ቀደም ብለው ይውጡ።

በመከላከል መንዳት

እርሶ ሌሎች ነጅዎች ማድረግ አለባቸው ወይም ማድረግ የለባቸውም ብለው የሚያስቡትን ነገር እንዲያደርጉ ወይም በዚያ ሰው ቦታ ቢሆኑ እርሶ ሚያደርጉትን ነገር ያደርጋሉ ብለው አይተማመኑ። ለምሳሌ፣ የግለሰቡ የታጠፊያ መብራት ብልጭ ድርግም እያለ ከሆነ ነጅው ይታጠፋል ብለው ግምት አይውሰዱ። ነጅው በመታጠፊያ ምልክት በሚያሳየው አቅጣጫ ባይታጠፍ ምን እንደሚያደርጉ ቀደም ብለው እቅድ ያውጡ እና ይወስኑ። ሁሉም ነጅ ቀይ የትራፊክ መብራት ወይም የማቆሚያ(ስቶፕ) ምልክት ሲሆር ይቆማል ብለው ግምት አይውሰዱ። አንዳንድ ነጅዎች ሆን ብለው የማቆሚያ(ስቶፕ) ምልክቶችን እና ትራፊክ መብራቶችን "ይጥሳሉ"። በመንዳት ላይ እያሉ ሁልግዜ "የማምለጫ መንገድን" ማሰብ አለቦት። ከትንሽ ሳምታት ልምምድ በሃላ ይህ "ሁለተኛ ተፈጥሮ" ይሆናል። በድንገት የአደጋ ሁኔታ(ኢመርጀንሲ) ቢነሳ፣ ዝግጁ የሆነ የእርምጃ እቅድ ይኖሮታል። ለምሳሌ፣ በመምጣት ላይ ያለ ተሽከርካሪ ማለፍ እየጀመረ እንደሆነ ካዩ እና ትክክለኛው መስመር ላይ መልሶ ለመግባት በቂ ቦታ የለውም ብለው ካሰቡ፣ ቀዝቀዝ ያድርጉ እና ከመንገዱ ጎን ያለውን ቦታ(ሾልደሩን) እና በቅርብ ያሉትን ቦታዎች ይዩ። በዚህ ግዜ፣ ምናልባት አስፈላጊ ከሆነ ወዴት መሄድ እንዳለቦት ማወቅ ይችላሉ። ማየት የሚችሉትን ርቀት ያህል ወደፊት ይመልከቱ። በዚህ መንገድ ከፊት ለፊቶ ካለው ተሽከርካሪ በፊት የሚከሰቱ ችግሮች እና በድንገት ለማዞር ወይም ለማቆም ምክንያት የሚሆኑት ለማየት ይችሉ ይሆናል። ለምሳሌ፣ ከፊት ያለው ተሽከርካሪ ላይ ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ ወይም ቢጫ መብራት ካስተዋሉ፣ መንገዱ ላይ ነገሮች ወይም ሰዎች እንዳሉ ማየት አለቦት። ግጭት የግድ ከሆነ፣ አይደንግጡ። ከዚያ የመውጫ መንገድ ለማግኘት ይሞክሩ። ሌላ ተሽከርካሪ ወይም ነገርን በፊት ለፊቱ ላለመምታት የሚችሉትን ሁሉ ነገር ያድርጉ፣ በአንግል ለመምታት ይሞክሩ። አማራጭ ካሎት፣ ሌላ ተሽከርካሪ ከመምታት፣ ተሽከርካሪዎን ጎድጎድ ያለ ስፍራ(ዲች) ውስጥ ማስገባቱ ይመረጥ ይሆናል።

ከሃላ ከመመታት እንዴት መከላከል እንደሚቻል

የመጨረሻ ሃላ(ሬር ኢንድ) ግጭት ከሁሉም አይነት የሞተር ተሽከርካሪ አደጋዎች በይበልጥ የሚከሰተው ነው። ሌላ ተሽከርካሪ የሚከተለው ነጂ ሲኮኑ፣ ከሃላ የመመታትን እድል ለመቀነስ የሚከተሉትን ማድረግ ይቻላል:

- የፍሬን መብራቶቾ(ስቶፕ ላይቶ) ንጹህ እና የሚሰሩ መሆናቸውን ያረጋግጡ
- ከሃላዎ የሚካሄደውን አውቀው ለመቆየት፣ ወደ ሃላ ማሳያ መስታዋቶን በየግዜው ይዩበት
- የሃላ መስኮቶ ንጹህ እና እንፋሎት ያልሸፈነው መሆን አለበት። ከውጭ ያሉት መስታዋቶቹ ጠቃሚዎች ናቸው።
- ለማቆም፣ ለመታጠፍ እና መስመር ለመቀየር በደንብ ቀደም ብለው ምልክት ያሳዩ
- ቀስ በቀስ እንጂ በድንገት አያቀዝቅዙ
- ፍጥነቶን ከትራፊኩ ፍጥነት ጋር ያድርጉ
- ተሽከርካሪ በጣም በቅርቡ የሚከተል ከሆነ፣ ያቀዝቅዙ እና ያሳልፉት

በክልሎች መሀከል ያለ አውራጎዳና (ኢንተርስቴት ሀይዌይ) እና ሌላ የተወሰነ ሊምትድ አክሰስ ሀይዌይ

ኢንተርስቴት ሀይዌዮችን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚችሉ የሚያውቁ ከሆነ፣ መሄድ የሚፈልጉበት ቦታ በይበልጥ በፈጠነ ግዜ፣ በቀለለ ሁኔታ እና በይበልጥ ደህንነት በሚያስጠብቅ ሁኔታ ያደርሶታል። ነገር ግን የሀይዌይ የደህንነት አሰራሮችን ማወቅ አለቦት።

ከመጀመሮ በፊት

የጎማዎ ሁኔታዎች ለሀይዌይ ፍጥነት ይሆናሉ? በቂ ዘይት እና የማቀዝቀዣ ውሀ አሎት? ተሽከርካሪዎ አደገኛ የሚያደርገው ምንም አይነት የሜካኒካል ችግር አለበት? ይህንን ጉዞ ለማድረግ በጥሩ ሁኔታ ያሉ መስሎ ይሰማውታል? በቂ ነዳጅ አሎት? በቂ እንቅልፍ አግኝተዋል? ናቪጌሽኖን ቀድመው ያስተካክሉ እና የሚወስዷቸውን መንገዶች ከመነሳቶ በፉት ቀድመው ይዩ። ይሄ ደህንነቱ የተጠበቀ እና አስደሳች ጉዞ እንዲኖሮት ይረዳዎታል።

የክልሎች መሀከል ያለው(ኢንተርስቴት)/ሀይዌው ውስጥ ይግቡ

ኢንተርስቴት እና ሌሎች ሊሚትድ አክሰስ ሀይዌይ ብዙ ግዜ በመግቢያ ማገናኛ መንገድ(ኢንትራንስ ራምፕ) እና ፍጥነት በመጨመሪያ ወይም መቀነሻ መስመሮች ነው የሚደረስባቸው። የማገናኛ መግቢያ መንገዱ ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ያስገባዎታል እና የፍጥነት መጨመሪያው መስመሩ በትራፊኩ ፍጥነት ላይ ለመድረስ እድል ይሰጣል። ኢንተርስቴት ሲገቡ መግቢያውን እና ኢንተርስቴቱን የሚከፋፍለው ሙሉ ቀለም ያላቸው መስመሮች ላይ መታለፍ የለባቸውም። ወደ ኢንተርስቴቱ አጭር መግቢያ ካለ እና የፍጥነት መጨመሪያ መስመር ከሌለ ፍጥነቶን ከትራፊኩ እኩል ለማድረግ የሚጨምሩት በትራፊኩ ውስጥ ክፍተት ካገኙ በሃላ ብቻ ነው። በአጠቃላይ፣ ኢንተርስቴት ከመግባቶ በፊት፣ የትራፊኩን ክፍተት እስኪጠብቁ ድረስ ማቆም አለቦት። ኢንተርስቴቱ ውስጥ የሚገቡት በግራ መግቢያ በኩል ከሆነ፣ በመስታዎቶቾ በኩል የሚያዩትን እና በትከሻዎ በላይ አሻቅበው ሲያዩ የሚያዩትን ያነጻጽሩ።

ኢንተርስቴትን/ሀይዌን ጥለው ሲወጡ

መውጫው(ኤግዚቱ) ከሀይዌው በቀኝ በኩል ከሆነ ያለው፣ መውጫው(ኤግዚቱ) ጋር ከመድረሶት በደንብ ቀደም ብለው የቀኝ መስመሩ(ሌን) ላይ ይሁኑ። ዋናው ሀይዌይ ላይ እያሉ አያብርዱ። ፍጥነት መቀነሻው መስመር ላይ ልክ እንደገቡ ማቀዝቀዝ ይጀምሩ እና የመውጫው ማገናኛ መንገድ(ኤግዚት ራምፕ) መጀመሪያ ድረስ ማብረዶን ይቀጥሉ። ፍጥነቶን ለመውጫው ማገናኛ(ኢግዚት ራምፕ) የተለጠፈው የፍጥነት ምልክት ድረስ ያብርዱ፣ አለዚያ በመጠምዘዣዎቹ (በከርቮቹ) ለመዞር ይቸገሩ ይሆናል። ከኢንተርስቴቱ የተሳሳተ ቦታ ላይ ከወጡ፣ የመውጫው ማገናኛን(ኤግዚት ራምፕ) ለቀው እስከሚወጡ ድረስ ይቀጥሉ እና ተመልሰው ወደ ኢንተርስቴቱ የሚገቡበትን መንገድ ይፈልጉ።

በኢንተር ስቴት/ሀይዌይ ላይ ሆነው መስመር መቀየር እና ማለፍ

በኢንተርስቴት እና ሌሎች ሊምትድ አክሰስ ሀይዌዮች ፍጥነቶች ያለማቋረጥ ከፍ ብለው ስለሚቆዩ፣ ጥንቃቄ የተሞላበት የመስመር(የሌን) መቀየር እና ማለፍ ወሳኝ ነው።

የሚከተሉት ሊረዳዎት የሚችሉ አንዳንድ ምክሮች ናቸው:

- በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በግራ ወይም በቀኝ ማለፍ ህጋዊ ነው፣ ነገር ግን ቀስ ብለው የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች በቀኝ መስመር(ሌን) ላይ መቆየት አለባቸው። ስለዚህ፣ አብዛኛውን ግዜ ሲያልፉ በግራ በኩል መሆን አለበት። በተጨማሪም፣ በመንገዶቹ የጎን ቦታዎች(ሾልደር) መስመሮች(ሌኖች) ማለፍ አይችሉም።
- ደህንነት የተጠበቀበት ማለፍ በነጅዎች መሀከል ያለው መተባበር ላይ ይወሰናል። ሌላ በሚያፎት ወቅት ፍጥነቶን አይጨምሩ።
- በከፍተኛ ፍጥነት በቅጽፈት የሚደረግ እንቅስቃሴ ህይወትን የሚያጠፉ ሊሆን ይችላል። ካለፉ በሃላ ወደሌላው መስመር(ሌን) በጣም በፍጥነት አይመለሱ። ተመልሰው መስመሮ(ሌኖ) ላይ ከመግባቶ በፉት ወደሃላ በሚያሳየው መስታዋቶ በኩል የተሽከርካሪዎቹን የፉት መብራቶች ማየት መቻል አለቦት።
- ሁልግዜም የመስመር(የሌን) መቀየርን ምልክት ያድርጉ
- የማይታዮትን ቦታ (ብላይንድ ስፖቶን) በትከሻዎ በላይ አየት በማድረግ ያረጋግጡ
- ወደ ሌላ መስመር(ሌን) ከመቀየሮ በፉት፣ የውጨን መስታዋት ይዩ ወይም በትከሻዎ ላይ በኩል የሃላ ግራ በኩል ወይም የሃላ ቀኝ በኩል ያለውን ያረጋግጡ።
- ከፊቶ ያለ ተሽከርካሪ የማይታየው ቦታ(ብላይንድ ስፖቱ) ጋር በፍጹም አይጓዙ።

አደባባዮች

አደባባይ ክብ የሆነ መገናኛ እና ሁሉም ትራፊክ በካንተርከሎክዋይዝ፣ ሁሌም በቀኝ መሀከል ባለው ደሴት ዙሪያ የሚጓዝበት ነው። ከእያንዳንዱ መገናኛው(ኢንተርሴክሽን) እግር የሚገቡ ሁሉም ተሽከርካሪዎች ቀደም ብሎ አደባባዩ ውስጥ ለገቡት ከግራ ለሚመጡት ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። ተሽከርካሪዎች ወደሚፈልጉት መንገድ ወይም ሀይዌይ ቀላል የሆነ የቀኝ መታጠፍን በማድረግ ከአደባባዩ ይወጣሉ።

አደባባዩ ጋር መጠጋት

አደባባዩ ጋር ሲጠጉ፣ ትክክለኛው መስመር(ሌን) ላይ ለመሆን በተቻሎት መጠን ቀደም ብለው የትኛውን መውጫ መውሰድ እንዳለቦት ይወስኑ። ፍጥነቶን ይቀንሱ፣ እና ከተቻለ አደባባይ ላይ ያለውን የትራፊክ ክፍተት ውስጥ ለመግባት እንዲያስችል ያስተካክሉት።

አደባባይ ውስጥ መግባት

አደባባዩ ጋር ሲደርሱ ከግራ በኩል ለሚመጣ ትራፉክ ቅድሚያ ይስጡ። ቀድመው አደባባይ ውስጥ ላሉ ትራፊክ፣ በተለይ ለባለሳይክል እና ባለሞተር ሳይክል ይጠንቀቁ። የአደጋ (ኢመርጀንሲ) ተሽከርካሪ በሌላው መስመር(ሌን) እየተጠጋ ከሆነ አደባባዩን አይጠጉት። ይሔ ቀድመው አደባባይ ውስጥ ያሉትን ትራፊክ ከኢመርጀንሲ ተሽከርካሪው ፊት እንዲለቁ ይረዳል።

በአደባባይ ውስጥ ስለመጓዝ

ሁልግዜ ባደባባዩ ውስጥ የመሀከል ደሴት ቀኝ በኩል ይቆዩ እና በመሀከሉ ደሴት በክሎክዋይዝ አቅጣጫ በኩል ይጓዙ። ግጭትን ለማስወገድ ካልሆነ በስተቀር አያቁሙ፣ የመንገዱ ቅድሚያ ያሎት እርሶ ኖት። አደባባዩ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ተሽከርካሪዎች ጎን ለጎን ለማስጓዝ ስፋቱ በቂ ሲሆን፣ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን አይቅደሙ። አደባባዩ ላይ ከፊት ለፊቶ ለሚያቋርጡት ትራፊኮች ተጠንቀቁ፣ በተለይ በሚቀጥለው መውጫ(ኤግዚት) ለመውጣት ለሚያቅዱ ተሽከርካሪዎች። የአደጋ ግዜ (ኢመርጀንሲ) ተሽከርካሪዎች እየተጠጉ ባለበት ወቅት፣ አደባባዩ ላይ እንዲጠመዘዙ ግልጽ የሆነ መንገድ ይስጡ።

ከአደባባይ ስለመውጣት

ከአደባባዩ ሲወጡ ዝቅተኛ ፍጥነት ይያዙ። ሁሌም የቀኝ መታጠፊያ ምልክቶን በመጠቀም መውጫዎን ያሳዩ። ሰፉ መዞሪያ ባላቸው አደባባዮች፣ በሚወጡበት ግዜ መንገዳቸውን ለሚያቋርጡባቸውን በቀኝ በኩል ያሉትን ተሽከርካሪዎች፣ ብስክሌቶችን ጨምሮ ይጠንቀቁ። ከመውጣቶ በፊት ቅድሚያ ሊሰጦት እንዳሰቡ ያረጋግጡ። ለእግረኞች ይጠንቀቁ፣ ቅድሚያም ይስጧቸው። መውጫው ላይ የእግረኞች መሻገሪያ ነጥቡን አልፈውት እስከሚሄዱ ድረስ ፍጥነት አይጨምሩ።

ሞተርሳይክሎች እና ብስኪሌቶች

ባለሞተርሳይክሎችን እና ባለብስክሌቶችን በቂ ቦታ ይስጧቸው እና ተገቢውን አስተያየትም ያድርጉላቸው። ባለብስኪሌቶች የመንገዱን መምጫ ላይ ከብስኪሊት መስመር(ሌን) ይጠጉት ይሆናል፣ አደባባይ ላይ ብዙ ግዜ ቀኙ ላይ ይቆያሉ፣ አደባባዩ ላይ እንደሚቀጥሉ ለማሳየት ግራን ይጠቁሙ ይሆን ይሆናል።

ትልቅ ተሽከርካሪዎች

ትልቅ ተሽከርካሪዎችን አይቅደሙ። ትልቅ ተሽከርካሪዎች (ለምሳሌ ትራኮች እና ባሶች) አደባባይ ላይ ሲጠጉ ወይም አደባባይ ላይ ሆነው በሰፉው መወዣወዝ ሊሆርባቸው ይችል ይሆናል። የመታጠፊያ ምልክታቸውን ይመልከቱ እና ብዙ ቦታ ይስጧቸው፣ በተለይ ሌሎች ተሽከርካሪዎችን ሊከልሉ ስለሚችሉ። ትልቅ ተሽከርካሪዎች የመንገዱን ስፋት በሙሉ መጠቀም ሊኖርባቸው ይችል ይሆናል፣ አደባባዩን ለመዞር የሚያስችል ሚወጣበት ቦታ(ማውንታብል አፕሮን) ጨምሮ። ነጂዎቻቸው ከሌሎች የአደባባይ ተጠቃሚዎች መጠንቀቅ አለባቸው፣ እና አደባባይ ውስጥ ከመግባታቸው በፉት ሌሎች ተጠቃሚዎች ስለእነሱ መምጣት ማወቃቸውን እና ቅድሚያ እንደሚሰጧቸው ማመን አለባቸው።

እግረኞች

አደባባይ ላይ ባሉ የእግረኛ መሻገሪያዎች ላይ እግረኞች ቅድሚያ አላቸው፣ ነገር ግን እግረኞች ከከርቡ ወይም ከሌላ ደህና መጠበቂያ ስፍራ በድንገት ለቀው በጣም ቅርብ በመሆኑ ምንክያት ለማቆም ወደማይችል ተሽከርካሪ አቅጣጫ መራመድ አይችሉም።



በርካታ መስመሮች(ሌኖች) ያሉት አደባባይ:

ብዙ መስመሮች(ሌኖች) ላሉዋቸው አደባባዮች፣ መግቢያ እና መውጫ መስመሮን(ኤግዚት ሌኖችን) መድረሻዎ ላይ ተመርኩዘው ይምረጡ። ለምሳሌ፡

- መገናኛው ላይ ቀኝ ለመታጠፍ፣ የቀኝ በኩል መስመርን(ሌንን) ይምረጡ እና በቀኝ መስመር(ሌን) በኩል ይውጡ (ሰማያዊ መኪና)
- በመገናኛው ቀጥታ ለመሄድ፣ አንዱን መስመር(ሌን) ይምረጡ፣ እና በገቡበት መስመር(ሌን) ሆነው ይውጡ (ቀይ መኪና)
- ወደግራ ለመታጠፍ፣ የግራ መስመሮን(ሌኖትን) ይምረጡ፣ እና ይውጡ (ቢጫ መኪና)

ማቆም

ተሽከርካሪ የሚሄድበት የሀይዌይ ክፍል (traveled portion of the highway) ላይ ማቆም የተከለከለ ነው። በመንገዱ ጎና ያለው ቦታ (ሾልደሩ) ላይ ማቆም የሚፈቀደው መኪናዎ አልነሳም ሲል ወይም ሌላ ኢመርጀንሲ ሁኔታ ሲኖር ብቻ ነው። እንደዚህ ሲያጋጥም፣ ኮፈኑን ያንሱት ወይም ነጭ ጨርቅ በግራ በር እጀታ ወይም የሬድዮ አንቴና ላይ ይሰሩበት። መኪናዎት ጋር ይቆዩ፣ ኢንተርስትቴት ወይም ሌላ ሊሚትድ አክሰስ ሀይዌይ አጠገብ በፍጹም አይራመዱ።

ወደሃላ መሄድ

ሀይዌይ ላይ ወደሃላ አይሂዱ፣ በምንም ምክንያት ቢሆን።

የአደጋ ግዜዎች (ኢመርጀንሲዎች)

ፍሬን ሲበላሽ

የፍሬን ፔዳሉን ፓምፕ ለማድረግ ይሞክሩ [ABS- ያልሆነ ሲስተም]። ይሄ የፍሬኑን ችሎታን ካልመለሰው:

- የኢመርጀንሲ (የማቆሚያ) ፍሬኑን ይጠቀሙ
- ከተቻለ ወደ ዝቅተኛ ማርሽ(ሎወር ጊር) ይቀይሩ
- አስፈላጊ ከሆነ የጎማዎቹን ጎኖች ከከርብ(የመንገዱ ጎን) ጋር ያፋትጉት።አንታይ ሎክ ብሬኪንግ ሲስተም (Anti-Lock Braking Systems (ABS)) ፍሬን መያዝ ፍሬን ሲይዙ ጎማዎ(ዊል) እንዳይቆለፍ የታሰበ ነው። መቼም ቢሆን የተሽከረካሪው ኮምፒተር አንድ ወይም ከዚያ በላይ ጎማ መቆለፉን ሲያሳይ፣ ነጂው እንዳይቆለፍ ለማገድ ማድረግ ከሚችለው በጣም በበለጠ ፍጥነት ኤቢኤስ (ABS) ፍሬኑን ፓምፕ ማድረግ ይጀምራል። ኤቢኤስ (ABS) መስራት ሲጀምር፣ ከፍሬኖቹ በኩል ኮሸኮሸታ ይሰማሉ እና የፍሬኑ ፔዳል ከእግሮ በታች ይንቀጠቀጣል። ሹፌሩ ማድረግ ያለበት ነገር የፍሬኑን ፔዳል በሀይል መጫን፣ እዚያው መያዝ፣ እና ተሽከርካሪው እንዲሄድ ወደሚፈልጉበት አቅጣጫ ማዞር ነው። መንሸራተትን ለመከላከል ኤቢኤስ (ABS) ኮምፒውተር የትኛው ጎማ ፍሬን እንደሚይዝ ይቆጣጠራል።

ኤቢኤስ (ABS) በሚሰራበት ግዜ እግሮትን ከፍሬኑ ላይ ለማንሳት የሚያስኞትን ፍላጎት ይቋቋሙት። በፍሬን ፔዳሉ ላይ አንድ አይነት የሆነ ግፊትን በማድረግ ይቆዩ። አንድ አይነት የሆነውን መጫንን ከፍሬን ፔዳሉ ማንሳት ወይም ፍሬኖቹን ፓምፕ ማድረግ ኤቢኤስ (ABS) ከስራው እንደሚያስቆመው ወይም እንደሚያጠፋው ነጅዎች ማወቅ አለባቸው።

ነጅዎች ኤቢኤስን (ABS) መጠቀም መለማመድ አለባቸው እና ተሽከርካሪዎ ለድንገተኛ ወይም የአደጋ ግዜ ፍሬን መያዝ ምን አይነት ምላሽ እንደሚሰጥ መለማመድ አለባቸው። ለመለማመድ ከሁሉ የተሻለ ቦታ ባዶ የሆነ የማቆሚያ ስፍራ ነው።

እርጥብ ፍሬኖች

ጥልቀት ያለው ውሀ መሀከል ከነዱ በሃላ፣ ፍሬኖትን መሞከር አለቦት። ወደ አንዱ በኩል ይጎትቱ ይሆናል ወይም ጭራሽኑ አይዝ ይሆናል። ፍሬኑን ለማድረቅ መኪናውን ትንሽ ማርሽ ላይ ያድርጉት፣ ቀስ ብለው ይንዱ እና ፍሬኑን ቀስ ብለው ይጠቀሙ።ፍሬኑን በየ 200 ጫማው ይሞክሩት፣ የፍሬን ተግባር ወደ ትክክል እስኪመለስ ድረስ ይቀጥሉ።

የፉት መስታዋት መጥረጊያ(ዋይፐር) መበላሸት
አስቸጋሪ የአየር ሁኔታ ላይ የፉት መስታዋት ዋይፐሮችዎ ከተበላሹ፣ መስኮቶትን ይክፈቱ፣ ጭንቅላቶን በመስኮቱ ያውጡ፣ ተሽከርካሪዎትን ወደመንገዱ ውጭ ይንዱት እና **አቁሙ**።

ፍጥነት መጨመሪያ (አክስሌረተር) ፔዳሎ ሲጣበቅ
- የፍጥነት መጨመሪያ ፔዳሉን በእግሮ በጣም ጫን ለቀቅ ያድርጉት
- ወደኒውትራል ይቀይሩ
- ፍሬንን ይጠቀሙ
- ከመንገዱ ውጪ ይውጡ እና ያቁሙ

መሪ ሲበላሽ
በድንገት መሪውን መቆጣጠር ካልቻሉ፣ ፍጥነት መጨመሪያው (አክሲለረተሩን) ቀነስ ያድርጉት። ተሽከርካሪዎ በተፈጥሮው ሚዛን በመሄድ ያሉበት መስመር ላይ ለመሄድ ከቀጠለ፣ እስከሚቀዘቅዝ ድረስ ይጠብቁ እና ከዚያ የአቅጣጫ ለውጥ እንዳይከሰት ፍሬኑን ቀስ ብለው ይጠቀሙት። ተሽከርካሪዎ ከመንገዱ መውጣት ወይም ወደ እግረኞች ወይም ወደሌላ ተሽከርካሪ መሄድ ከጀመረ፣ የመጨረሻውን ሀይል ተጠቅመው ቶሎ ብለው ፍሬኑን ይያዙ።

መቆጣጠር ሲያቅት – መሪ እና የመቆለፊያ መሳሪያ
ተሽከርካሪዎ በእንቅስቃሴ ላይ እያለ የተሽከርካሪውን ማስነሻ መቆለፉያ (ሎክ) ላይ በፍጹም አያድርጉት። ይሄ መሪው እንዲቆልፍ ያደርገዋል እና መሪውን ለማዞር ከሞከሩ ተሽከርካሪው ከቁጥትሮ ውጭ ይሆናል።

የፉት መብራቱ ሲበላሽ
ሀይዌው ብርሀን ያለው ከሆነ፣ በተቻሎት ፍጥነት እና ደህንነት በጠበቀ መልኩ ከመንገዱ ወጥተው ወደ መንገዱ ጎን ቦታ(ሾልደሩ ላይ) ወይም ሌላ ክፍት ቦታ ላይ ይውጡ። ሀይዌው ጨለማ ከሆነ፣ የፓርኪንግ መብራቶን፣ የአቅጣጫ ምልክቶን ወይም የአደጋ ግዜ(ኢመርጀንሲ) መብራቶን ይሞክሩ እና ከመንገዱ ይውጡ። ሁሉም መብራቶች ካልሰሩ፣ መንገዱ ላይ ይቆዩ እና ከመናገዱ በደህና መውጣት እስኪያስችሎ ድረስ ያቀዝቅዙ።

መኪና ውስጥ እሳት
እሳትን እንዴት ማጥፋት እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ ነው። ምን ማድረግ እንዳለባችው በማያውቁ ነጅዎች እሳቶች ይባባሳሉ። የሚከተሉት እሳት ከተነሳ መከተል የሚገባ አንዳንድ አሰራሮች ናቸው፡

ከመንገዱ ይውጡ

የመጀመሪያው ደረጃ ተሽከርካሪውን ከመንገዱ ማውጣት እና ማቆም ነው። ይሄ ሲደረግ:

- ግልፅ የሆነ ቦታ ላይ ያቁሙ፣ ከህንጻ፣ ዛፎች፣ ቁጥቋጦዎች ሌላ ተሽከርካሪዎች ወይም ማንኛውም እሳት ሊያያዝ ከሚችል ነገር አርቆ
- ወደ አገልግሎት ጣቢያ እንይወስዱት!
- ካሉት፣ ለፖሊስ ችግሩን እና ያሉበትን ቦታ ለመንገር የሞባይል ስልኮትን ይጠቀሙ

እሳቱ እንዳይዛባ ያድርጉ

እሳቱን ለማጥፋት ከመሞከሮ በፉት፣ የበለጠ እንደማይዛባ ያረጋግጡ።

- **ለሞተር** እሳት፣ በተቻሎት ፍጥነት ሞተሩን ያጥፉ። አለማድረግ ከቻሉ ኮፈኑን(ሁዱን) አይክፈቱ። የእሳት ማጥፊያውን በክፍተቱ (ሎቨር)፣ በራዲያተሩ ወይም በተሽከርካሪው የታች በኩል ይንፉ።
- በቫን ውስጥ ወይም የሳጥን ተጎታች (በቦክስ ትሬለር) ላለ ለ**ጭነት** እሳት፣ በሮችን ዘግተው ያቆዩ፣ በተለይ ጭነቶ አደገኛ ነገሮች ያሉበት ከሆነ። የቫኑን በሮች መክፈት ለእሳቱ አክስጅን ይሰጠዋል እና እሳቱን ያባብሰዋል።

እሳቱን ማጥፋት

የሚከተሉት እሳትን ለማጥፋት ምንከተላቸው አንዳንድ መመሪያዎች ናቸው:

- የእሳት ማጥፊያው እንዴት እንደሚሰራ ማወቅ። ሊጠቀሙበት ከመፈለጎ **በፉት** ማጥፊያው ላይ የተጻፈውን መመሪያ ያጥኑ።
- ማጥፊያውን ሲጠቀሙ፣ በተቻሎት መጠን ከእሳቱ ይራቁ።
- ኢላማውን እላይ ነበልባሉ ላይ ሳይሆን የእሳቱ ምንጭ ወይም መሰረት ላይ ያድርጉ።
- የራሶን ቦታ ከንፋሱ አቅጣጫ በኩል ያድርጉ። ንፍሱ ነበልባሉን ወደ እርሶ ከሚያመጣው ይልቅ ማጥፊያውን ወደ እሳቱ ይውሰደው።
- ይቃጠል የነበረው ማንኛውም ነገር ሙሉ በሙሉ እስኪቀዘቅዝ ድረስ ይቀጥሉ። የጭስ ወይም የነበልባል አለመኖር እሳቱ ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል ወይም መልሶ አይነሳም ማለት አይደለም።
- የሚያደርጉትን ነገር የሚያውቁ ከሆነ እና ደህንነት በጠበቀ መንገድ ማድረግ የሚቻል ከሆነ ብቻ እሳትን ለማጥፋት ይሞክሩ።

ወደ እርሶ መስመር(ሌን) የሚመጣ ተሽከርካሪ

እርሶ ወዳሉበት መስመር(ሌን) አንድ ተሽከርካሪ ሲመጣ ካዩ፣ ወደ ቀኝ ይጠጉ፣ ያቀዝቅዙ፣ ክላክስ(ጥሩንባዎን) ያሰሙ እና የፊት መብራቶን ብልጭ ድርግም ያድርጉ። ተሽከርካሪው ወደ ለቀቀው መስመር አይታጠፉ ምክንያቱም ነጂው "ሊነቃ"፣ ስህተቱን ሊረዳ እና ወደ ትክክለኛው መስመሩ ሊመለስ ይችል ይሆናል።

የባቡር መስመር ላይ መቆም

ለባቡሮች በሁለቱም መንገድ ይመልከቱ። ባቡር እየመጣ ከሆነ፣ ከተሽከርካሪዎ ይውጡ እና ከአደጋው ፍንጣሪ እንዳይመታዎት ለመከላከል በሀዲዱ ጎን በኩል ወደ ባቡሩ በኩል ይሩጡ።

መንገዱ ለቆ መውጣት

ከመንገዱ ከወጡ ወይም እንዲወጡ ከተገደዱ፣ እነዚህ መመሪያዎች ህይወቶትን ያተርፉ ይሆናል:

- አይደንግጡ
- እግሮትን ከፍጥነት መጨመሪያው ይንሱ
- ፍሬኖቹን አይቀርቅሩት። በጥንቃቄ ፍሬን ይያዙ ወይም ጭራሽኑ አይድርጉ።
- መሪውን አጥብቀው ይያዙ፣ ምክንያቱም መሪው ላይ ያልተለመደ ተጽእኖ ሲኖር ከእጅ ሊያዞረው ስለሚችል
- ተሽከርካሪውን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሮ ውስጥ እስከሚያደርጉት (ፍጥነቱ ወደ 15 mph ወይም ከዚያ በታች እስኪቀነስ) እና ከሃላዎ እና ከጎኖ ያለን ትራፊክ እስኪያዩ ድረስ እመንገዱ ውስጥ ተመልሰው ለመግባት አይሞክሩ። ከዚያ መሪዎችን ወዲያውኑ በሀይል ወደመንገዱ ያዙሩ። ወደመንገዱ መሀከል የተሰመረ መስመር ወይም ወደ ሌላ መስመር(ሌን) ውስጥ እንደማይገቡ እርግጠኛ ይሁኑ።

ራምብል ስትራይፕ

ራምብል ስትራይፕ (Rumble strips) የመንገዱ አባጣ ጎባጣ ትንሽ አካል፣ እላዩ ላይ ሲነዱበት ጎማዎ በሚሰጠው ድምጽ የሚያነቃዎት ነው። ራምብል ስትራይፖች አደገኛ መጋጠሚያ ወይም አንድ ሰው መንገዱ ጠርዝ ላይ በጣም ተጠግቶ ሲነዳ ሊመጣ ካለው አደጋ የሚያስጠነቅቅ ነው።

ጎማዎች

የጎማ ችግሮች እንዳይኖር ተመልከቱ። ችግር ባለባቸው ጎማዎች መንዳት አደገኛ ነው። የሚከተሉትን ይመልከቱ:

- በጣም ያረጀ። ቢያንስ በፊት ጎማ ላይ በእያንዳንዱ ዋና ዋና ክፍተት (ግሩቭ) ውስጥ 4/32-ኢንች ክርክር(ትሬድ) ጥልቀት ያስፈልጎታል። ሌሎቹ ጎማዎች ላይ 2/32 ኢንች ያስፈልጎታል። በክርክሩ(ትሬዱ) ወይም ሳይድዎሉ በኩል ምንም አይነት ክር መታየት የለበትም።
- የተቆረጠ ወይም ሌላ ጉዳት ያለው
- የክርክር(ትሬድ) መለያየት
- እርስ በራሳቸው ወይም ከተሽከርካሪው አካል ጋር የሚነካኩ ጥምር(ድዋል) ጎማዎች
- የማይመጣጠኑ የጎማ መጠን
- አንድ ዘንግ (አክስል) ላይ በጋራ የሚሰራ ራድያል እና ቢያስ-ፕላይ
- የተቆረጠ ወይም የተሰነጠቀ የቫልቭ ሲስተም
- በአውቶቢስ የፊት የጎማ እግር ላይ እንደገና ክፍተት የተደረገለት(ሪ-ግሩቭድ)፣ እንደገና የተሞላ(ሪ-ካፕድ)፣እንደገና-የተከረከረ(ሪ-ትሬድድ) ጎማዎች አይፈቀድም

የጎማ ማረፊያው(ዊል) እና ሪም ችግሮች

- ችግር ያለባቸው የጎማ ማረፊያው(ዊሎች) ወይም ሪሞች አደጋ ሊያመጡ ይችላሉ።
- የታጠፈ ወይም የተሰነጠቀ ሪም ጎማ እንዲተነፍስ ወይም እንዲወልቅ ሊያደርገው ይችላል።
- የጎማ ማረፉያው (ዊል) ብሎኖች ዙሪያ ዝገት ሲኖር ብሎኖቹ ላልተዋል ማለት ነው – መጥበቃቸውን ያረጋግጡ።
- ጎማ ከተቀየረ በፉት ትንሽ ቆየት ብለው ያቁሙ እና እንደገና የብሎኑን መጠበቅ ያረጋግጡ።
- የጠፋ ክላምፕ፣ ስፔሰር፣ ስታድ ወይም ላንግ ማለት አደጋ ማለት ነው።
- የማይመጣጠኑ፣ የታጠፉ፣ ወይም የተሰነጠቀ ሎክ ሪንግ (የማሰሪያ ቀለበት) አደገኞች ናቸው።
- በብየዳ የተጠገኑ ዊል ወይም ሪም ደህንነትን አያስጠብቁም

መፈንዳቶች

መፈንዳቶች ከመንገዱ ውጭ ተፈናጥሮ ወደ አስፋልት ያልሆነ የመንገዱ ጎን(ሶፍት ሾልደር) መሄድ እንደማለት ነው። ጎማዎ ከፈነዳቦት:

- ፍሬኑን አይያዙ
- መሪውን አጥብቀው ይያዙ
- የቀኝ መታጠፉያ ምልክቶን ያሳዩ እና ተሽከርካሪውን ወደ መንገዱ የጎን ቦታ (ሾልደሩ) በደህና ያቁሙ
- ፍጥነት ይቀንሱ እና ከመንገዱ ውጭ በደህና የሚነዱበትን ቦታ ይፈልጉ
- ተሽከርካሪው ልክ ሊቆም እስኪል ድረስ ይጠብቁ

ፍለድድ ሞተር (ኢንጂን)

- የነዳጅ ፔዳሉን ወደመሬቱ ይጫኑ እና ይያዙት
- ቁልፉን ማስነሻው ላይ ያዙሩት እና ለትንሽ ግዜ እዚያ ያቆዩት (10 – 15 ሰከንዶች)
- ሞተሩ ሲነሳ የነዳጅ ፔዳሉን ይልቀቁት
- የጋዝ ፔዳሉን ፓምፕ አያድርጉ፣ ፍለዲንጉን ያብሰዋል

የተበላሸ ተሽከርካሪ

- ከተቻለ ሁሉኑም አራቱንም ጎማዎች ከጎዳናው ያውጡ
- የማቆሚያ(ፓርኪንግ) መብራቶን ወይም የኢመርጀንሲ ብልጭ ድርግም የሚለውን መብራቶች ያብሩ፣ እና ካለ፣ ብልጭ የሚል መብራት(ፍሌር) ወይም የሚያብለጨልጭ ቀይ መብራቶች ወይም የሚያንጸባርቅ ሶስት መአዘን ያድርጉ
- የራዲዮ አንቴና ወይም የግራ በሩ እጀታ ላይ ማህረብ ወይም ነጭ ጨርቅ ይሰሩ እና/ወይም ኮፈኑን ይክፈቱት

ቅድሚያ መስጠት (Right-of-Way)

ህጎች ቅድሚያ መስጠትን ይደነግጋሉ፣ ነገር ግን እነዚህን ህጎች ከደህንነት በፉት በፍጹም አያድርጓቸው። ቅድሚያ መስጠት ማለት አንድ ተሽከርካሪ ወይም እግረኛ በሀይዌ ላይ በህጋዊ መንገድ ከሌላ ተሽከርካሪ ወይም እግረኛ ቀድሞ የመሄድ መብት ማለት ነው። ቅድሚያ የማግኘት መብቱ ካሎት እና ሌሎች ካስቀደሞት ወዲያውኑ ይቀጥሉ።

- በእርግጥ የማቆም(ስቶት) ምልክቶችን፣ ቅድሚ የመስጠት(ይልድ) ምልክቶችን እና መገናኛ ላይ የትራፊክ ምልክቶችን ማክበር አለቦት።
- መገናኛው ላይ ከሌላ ተሽከርካሪ በሃላ ከገቡ፣ ቅድሚያ መስጠት ያለቦት ላይ ቅድሚያ መስጠት አለቦት
- መገናኛ ላይ ወይም ወደ የጓሮ መንገድ (አሊይ) ወይም ወደ የግል መንገድ ወይም ወደ መግቢያ (ደራይቭ ዌይ) ወደ ግራ ሊታጠፉ ደርሰው ከሆነ፣ መታጠፍ ደህና እስኪሆን ድረስ ለሌላ እግረኛች እና ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት አለቦት።
- ከግል መንገድ ወይም ድራይቭ ዌይ ወደ ህዝብ መንገድ ወይም ሀይዌይ እየገቡ ከሆነ ማቆም እና ለሚመጡት ተሽከርካሪዎች እና እግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለቦት።
- የትራፉክ መብራት ለእርሶ አረግጋዴ ከሆነ፣ መገናኛው ላይ ላሉት እግረኞች እና ተሽከርካሪዎችን ማሳለፍ አለቦት። የቀይ መብራት ጣሺዎችን በጥንቃቄ ይመልከቱ።

የፖሊስ መኪና፣ አንቡላስ እና እሳት አደጋዎች የመሳሰሉ ስልጣን ያላቸው የአደጋ ግዜ(ኢመርጀንሲ) ተሽከርካሪዎች የሚሰማም(ሳይረን) ወይም የሚታይ(ብልጭ ድርግም የሚል መብራት) ምልክት በሚሰጡበት ግዜ ቅድሚያ የማግኘት መብት አላቸው ። ተሽከርካሪ ሲመጣ ሲሰሙ ወይም ሲያዩ ወዲያውኑ ወደ ከርብ መንዳት እና ማቆም አለቦት፣ የአደጋ (ኢመርጀንሲ)ተሽከርካሪው እስከሚያልፍ ድረስ ቆመው ይቆዩ። ማንኛውንም የእሳት መሳሪያ ለአደጋ ግዜ ምላሽ በመስጠት ላይ እያለ ከ 500 ጫማ(ፈት) ባነሰ ቅርበት አይከተሉት።

የእግረኞች ቅድሚያ ማግኘት

ሁሉም እግረኞች፣ የትራፉክ መኮንኖች ወይም የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያዎች ትራፊኩን በሚቆጣጠሩበት ወቅት ካልሆነ በስተቀር፣ በከተማ(ሲቲ) እና ትንሽ ከተማ(ታውን) መንገድ የእግረኛ መሻገሪያዎች የቅድሚያ መብት አላቸው። የእግረኛ መሻገሪያው ላይ በቀይ መብራት ካልገቡ በስተቀር ወይም የትራፉክ መኮንን ከሚሰጠው ትእዛዝ ውጪ ካልገቡ በስተቀር፣ ምልክት ቢኖረውም ባይኖረውም መሻገሪያ መንገዱ ላይ ያሉ እግረኞች የቅድሚያ መብት አላቸው።

የእግረኞች ምልክቶች

አንዳንድ በተለይ ቢዚ የሆኑ መገናኛዎች ላይ ከትራፊክ ምልክቶቹ በተጨማሪ የእግረኞች ምልክቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላል። ነጂዎች መደበኛ ትራፊክ ምልክቶችን መከተል አለባቸው። እግረኞች ይራመዱ (WALK) እና አይራመዱ (DON’T WALK) ምልክቶችን መታዘዝ አለባቸው።

የእግረኛ መሻገሪያዎች ላይ መሻገር

እግረኞች ጎዳናውን መሻገሪያ ቦታዎች ላይ በሚከተሉት ሁኔታ ላይ ሲሆን የተሽከርካሪ ነጂ ሙሉ በሙሉ ማቆም አለበት፡

- ተሽከርካሪው የሚጓዝበት የጎዳናው ግማሽ ላይ ከሁኑ፣ ወይም

- **በአደጋ ላይ በሚያደርግ መልኩ ከጎዳነው ሌላኛው ግማሽ ካለው የቅርቡ መስመር(ሌን) እየመጡ በጣም ቀርበው ከሆነ።** መቼም ቢሆን አንድ ተሽከርካሪ መገናኛ ላይ እግረኛ መሻገሪያውን እንዲሻገር ለመፍቀድ ምልክት ባለው ወይም ምልክት በሌለው መሻገሪያ ሲቆም፣ ከሃላ የሚመጣ ማንኛውም የሌላ ተከርካሪ ነጂ የቆመውን ተሽከርካሪ መቅደም እና ማለፍ የለበትም። አንድ እግረኛ ከርቡን ወይምን ሌላ የደህንነት ቦታን ለቆ በድንገት በጣም በመቅረቡ ምክንያት ማቆም ወደማይቻለው ተሽከርካሪ አቅጣጫ መራመድ ወይም መሮጥ የለበትም።

ከእግረኛ መሻገሪያው ውጪ ባለ ቦታ መሻገር

የምናበረታታው ነገር ባይሆንም፣ ማንኛውም እግረኛ ጎዳናውን ከመሻገሪያው ውጪ ከተሻገረ ተሽከርካሪው ለእግረኛው የመሄድ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል። በነዚህ ሁኔታዎች እግረኛው የመቅደም መብት ባይኖረውም፣ ነጂው በነዚህ ሁኔታዎች ሁሌም ለእግረኞች ቅድሚያ መስጠት አለበት።

ልዩ በሆኑ የእግረኞች መሻገሪያዎች መሻገር

የእግረኞች ዋሻ(ታነል) ወይም ከላይ ሚያልፍ (ኦቨርሄድ) ባለበት ቦታ እግረኛ ጎዳናውን ከተሻገረ፣ ጎዳናው ላይ ለሚመጡት ተሽከርካሪዎች እግረኛው ቅድሚያ መስጠት አለበት። ምንም እንኳን እግረኛው የቅድሚያ መብት ባይኖረውም፣ ነጂ ሁልግዜ መገናኛው ላይ ለእግረኞች ቅድሚያ የመስጠት ሀላፊነት አለበት።

አጠገብ ላጠገብ ባሉ መገናኛዎች(ኢንተርሴክሽን) መሀከል መሻገር

የትራፊክ መቆጣጠሪያ ምልክት በሚሰራበት አጠገብ ላጠገብ ባሉ መገናኛዎች(ኢንተርሴክሽን) መሀከል፣ እግረኛ ጎዳናውን መሻገር የሚችለው ምልክት ባለበት የእግረኛ መሻገሪያ ላይ ብቻ ነው ወይም ጎዳናው ላይ ለሚመጣ ማንኛውንም ተሽከርካሪ ቅድሚያ ሰጥቶ ካሳለፈ በሃላ ነው።

ጉዳት(ዲሳቢሊቲ) ያለባቸው ግለሰቦች

ነጅዎች በተለይ መስማት ለተሳናቸው ወይም ምርኩዝ(ኬን)፣ ክራች፣ ዋከር፣ የሚመራ ውሻ(ጋይድ ዶግ)/ የአገልግሎት እንስሳት፣ ዊልቸሮች ወይም ሞተራይዝድ ስኩተር የሚያስፈልጋቸው የአካል ጉዳት ላለባቸው እግረኞች ነቅተው መጠበቅ እና የማለፍ ቅድሚያ መስጠት አለባቸው። እነዚህ ግለሰቦች የሚጠጣውን ትራፊክ ለማወቅ ችግር ሊኖርባቸው ይችላል እናም መንገዱን ለመሻገር ተጨማሪ ግዜ ያስፈልጋቸው ይሆናል። ነጅዎች ለሚመጡ ልጆች ወይም ግራ መጋባታቸው ወይም አቅም እንደሌላቸው ግልጽ ለሆነ ግለሰቦች እጅግ በጣም ጥንቃቄ መውሰድ እና ለማቆም መዘጋጀት አለባቸው።

አምስት ገጽታ ያለው (five-sided) ምልክት የትምህርት ቤት መሻገሪያ እንዳለ ለማስጠንቀቅ ጥቅም ላይ ይውላል። ዳይመንድ ቅርጽ ያላቸው ምልክቶች የእግረኛ መሻገርን ያስጠነቅቃል።

መንገዱን ከሌሎች ጋር ስለመጋራት

የመንገድ የትራፊክ ህጎች እና ደንቦች ዋላው አላማ ብዙ የጎዳና ተጠቃሚዎች፣ የሞተር ተሽከርካሪዎች፣ ብስኪሌቶች እና እግረኞች ጎዳናውን በእኩል እና በፍትዊ መልኩ ሁልግዜ እንዲጋሩት ነው። የጎዳና ደህንነት መንገዱን ከሌሎች ጋር መጋራት ላይ የተመሰረተ ነው።

መንገዱን ከትልቅ ትራክ ጋር መጋራት

እንደልብ ማንቀሳቀስ(ማኑቨራቢሊቲ)

ትራኮች በዋነኝነት ብዙ ምርቶችን ወደ ከተማ እና ከከተማ(ሲቲ) እና ትንሽ ከተማ(ታውን) ለመሸከም የተሰሩ ናቸው፤ አሰራራቸው እንደ መኪኖች እንደፈለጉ ለማንቀሳቀስ የሚያስችሉ አይደሉም። ትራኮች ከሌላ የረዘመ የማቆሚያ እና የማፍጠኛ ርቀት አላቸው፣ ለመታጠፍ ከሌላው የሰፋ ቦታ ይፈልጋሉ እና የበለጠ ክብደት አላቸው። ብዙ መስመር(ሌን) ባለው ሀይዌዎች፣ በሀይዌው ላይ ያለውን ወይም የሚወጣውን የትራፊክ ፍሰት እንዲቀጥል ለማገዝ የጭነት ተጎታቾች ብዙውን ግዜ መሀከለኛው መስመር(ሌን) ላይ ይቆያሉ።በተጨማሪም፣ መሀከለኛው መስመር ላይ መቆየት የትራክ ነጂው አደገኛ ሁኔታን ወይም አደጋን ለማስወገድ መስመር(ሌን) መቀየር ካለባቸው አማራጮቹን ያሰፋላቸዋል።

ማለፍ

ትራክን ሲያልፉ መጀመሪያ ፊት ለፊቶን ይዩ እና ሃላዎን ይዩ፣ እና ግልጽ ሲሆን ብቻ እና በህግ ማለፍ የሚችሉበት ዞን ላይ ከሆኑ ወደማለፊያው መስመር ይግቡ። የፊት መብራቶን ብልጭ በማድረግ እያለፉ መሆኑን ለትራክ ነጂው ያሳውቁት፣ በተለይ በምሽት ግዜ። ነጂው በመስመሩ(በሌኑ) ውስጥ በዚያኛው በኩል በመቆየት ለእርሶ ቀላል ያደርግሎታል።

ደልዳላ በሆነ ሀይዌይ ትራክን ማለፍ መኪና ከማለፍ ከሶስት እስከ አምስት ሰከንድ ብቻ የበለጠ ይፈጃል። ቁልቁለት ላይ የትራኩ የራሱ ሂደት ፍጥነቱን እንዲጨምር ያደርገዋ፣ ስለዚህ ፍጥነቶን መጨመር ሊኖርቦት ይችል ይሆናል። ማለፎትን በተቻለ ፍጥነት ቶሎ ይጨርሱ፣ እና ከሌላው ተሽከርካሪ ጎን አይቆዩ። ካለፉ በሃላ ነጅው መብራቱን ብልጭ ካደረገ፣ ተመልሰው ለመግባት ግልጽ ነው ለማለት ምልክት ይሆን ይሆናል።

ተመልሰው የሚገቡት ወደሃላ በማሳያ መስተዋቶ ውስጥ የትራኩን ፉት ማየት ከቻሉ ብቻ መሆኑን ያረጋግጡ። አንድን ትራክ ካለፉ በሃላ፣ ፍጥቶን ይቀጥሉበት። ብዙ አውቶ/ትራክ አደጋዎች የሚከሰቱት አውቶዎች ቶሎ በትራክ ፊት መስመርን(ሌኑን) በመቀየር፣ ከዛ በትራፊክ መጨናነቅ ምክንያት በድንገት በማቀዝቀዝ ወይም በማቆም፣ የትራክ ነጅውን የደህንነት ቦታን መልሶ ለማስተካከል ግዜ ባለመስጠት ነው።

ትራክን መከተል

ትራክ እየተከተሉ ከሆነ፣ ከ “ከማይታየው ቦታ” (“ብላይንድ ስፖቱ”) ይውጡ፣ ከጋቢናው (ካብ) ፊት ለፉት እስከ 20 ጫማ፣ ከየትኛውም የትራክ ተሳቢው በኩል፣ በተለይ በጋቢናዎቹ ጎኖች በኩል፣ ከሃላ እስከ 200 ጫማ ድረስ።

ከትራኩ ሃላ እና በቀኝ በኩል ከትራክተሩ ቅርብ ይቆዩ። ተሽከርካሪዎን የትራክ ነጂው በጎን መስተዋቱ እሚያይበት ቦታ ያድርጉት፣ ከዚያ ከፊት ለፊቶ ያለውን መንገድ ጥሩ እይታ ይኖሮታል እና ለማቆም ወይም ለመዞር የትራክ ነጅው ብዙ ማስጠንቀቂያ ሊሰጦት ይችላል። እርምጃ ለመውሰድ እና በደህና ለማቆም የበለጠ ግዜ ይኖሮታል። ትራክን በምሽት ሲከተሉ፣ ሁሌም የፉት መብራቶን ያደብዝዙ። ከሃላ ካለ ተሽከርካሪ ሚመጣ የደመቀ ብርሀን በትራኩ ትላልቅ የጎን መስታዋቶች ውስጥ ሲንፀባረቁ የትራክ ነጂውን እያታ ያሳውረዋል። ዳገት ላይ ከትራክ ሃላ ከቆሙ፣ ምናልባት ትራኩ መንቀሳቀስ ሲጀምር ወደሃላ ትንሽ ከተንሸራተተ ከፉት ለፉቶ ቦታ ይተዉ። እንዲሁም፣ ነጂው ከትራኩ ሃላ መቆሞትን እንዲያይ መስመሮ(ሌኖ) ውስጥ ወደ ግራ ሆነው ይቆዩ።

የትራኩን መስተዋቶች ማየት የማይችሉ ከሆነ፣ የትራክ ነጂው እርሶን ሊያዩት አይችልም!

በማንይሆን-ዞን ወይም የጎን የማይሆን-ዞን (No-Zone/Side No-Zones) ላይ አይቆዩ

ትራኮች እና ባሶች በሁለቱም በኩል የማይታያቸው ቦታ(ብላይንድ ስፓት) አላቸው። እርሶ የነጂውን ፊት በጎን ማያ መስታዋቱ ማየት የማይችሉ ከሆነ፣ እርሳቸው አያዩትም። ትራኩ መስመሩን ከቀየረ ችግር ላይ ሊወድቁ ይችላል።

የሃላ የማይሆን-ዞን (Rear No-Zones): ጭራን መከተልን ያስወግዱ። እንደ መኪኖች ሳይሆን፣ ትራኮች እና አውቶብሶች ልክ ከሃላቸው ትልቅ የማይሆን ዞን (ኖ-ዞን) አላቸው። የትራክ ወይም የባስ ነጂው እዚያ ሃላ ያለውን መኪናዎን ሊያይ አይችልም። ትራኩ ወይም ባሱ በድንገት ፍሬን ከያዘ፣ እርሶ የሚሄዱበት ቦታ አይኖሮትም።

የፉት የማይሆን-ዞን (Front No-Zones): ባስ ወይም ትራክ ካለፉ በሃላ በጣም ቶሎ ከፊት አያቋርጡ። የትራክ እና የባስ ነጅዎች መኪኖች ለማቆም ከሚወስድባቸው ሰአት እና ቦታ እጥፍ ገደማ ያስፈልጋቸዋል። ከፉት ከመሄዶ በፉት ወደ ሃላ ማሳያ መስታዋቶ የትራኩን ሙሉውን የፉቱን አካል ይዩ፣ ከዚያ በሃላ ፍጥነቶን አይቀንሱ።

ወደሃላ መሄድ የማይሆን ዞን (Backing up No-Zones): ወደሃላ በመሄድ ላይ ባለ ትራክ ሃላ በፍጹም አያቋርጡ። ወደሃላ የሚሄዱን ትራኮችን ችላ በማለት በየአመቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ ሞተሪስቶች ይገደላሉ ወይም ይጎዳሉ።የትራክ ነጅዎች ወደ ሃላ ማሳያ መስታዋቶች የሷቸውም እና ከሃላቸው ሲያቋርጡ ላትታዮቸው ይችላሉ።

የትራክ መቆሚያ ርቀት

ትራኮች ለመቆም የበለጠ ይወስዳሉ። በሰአት 60 ማይል የሚጓዝ አንድ መኪና በ 366 ጫማ ገደማ መቆም ይችላል። በተመጣጣኝ ፍጥነት የሚጓዝ ትራክ ለመቆም ከ 400 ጫማ በላይ ይወስድበታል።

ቀኝ እና ግራ መታጠፍ

የትራክ የመታጠፊያ ምልክቶችን በቅርበት ያስተውሉ። በእነርሱ እና በከርቡ መሀከል ተጠግቶ ያለን መኪናዎች ማየት አይችሉም። የትራኩ ሃላ ወይም የትራክተሩ ሃላ ወይም ተጎታቹ ከኮርነሩ ወይም ሌላ የቆመ እንቅፋትን ለቆ እስኪሄድ ድረስ ትራክ ነጂዎች ሰፊ ቀኝ ወይም ግራ መታጠፎችን ማድረግ አለባቸው። አንዳንድ ግዜ ኮርነሩን ነጻ ለማድረግ የሌላ መስመር ቦታ ጥቅም ላይ ይውላል። አደጋን ለማስወገድ፣ የማዞሩር ሂደት እስኪፈጸም ድረስ አይለፉ።

መጥፎ አየር

በዝናብ ወይም በበረዶ ከባድ ትራክን መከተል ወይም ማለፍ(ወይም በእርሱ መታለፍ)የእይታ ችግርን ይፈጥራል። ከትራኩ ጎማ እና ተጎታች የሚመጣ መረጨት ወይም ንጥብጣቢ እይታን እስከ ዜሮ አካባቢ ድረስ ሊቀንሰው ይችላል። በእርጥብ አየር በሚነዱበት ግዜ ሁሉ የተሽከርካሪዎ የፊት መስተዋት ዋይፐሮች መስራታቸውን እና ማጠቢያ ማጠራቀሚያው ውስጥ ፈሳሽ መኖሩን ያረጋግጡ። የፉት መብራቶ መብራታቸውን ያረጋግጡ።

በትራኮች አካባቢ ሲነዱ ማስወገድ የሚገባ በአብዛኛው በተደጋጋሚ ከሚደረጉ ስህተቶች አንዳንዶቹ:

- ***መውጫዎ ጋር ወይም መታጠፊያዎ ጋር ለመድረስ የሀይዌ ትራፊክ ላይ ያለን ትራክ አያቋርጡ።*** በትራኩ ፉት ለፉት ያለው ግልጽ ቦታ ላይ ማቋረጥ የትራክ ነጂውን የደህንነት ቦታ ይነሳባቸዋል። ለማቀዝቀዝ ትንሽ ግዜ ይውሰዱ እና ከትራኩ ሃላ ይውጡ – ትንሽ ተጨማሪ ሰከንዶች ብቻ ነው የሚወስድቦት።
- **በሚያልፉበት ግዜ ከትራኩ ጎን ሆነው አይዘግዩ።** ሁልግዜ የትራክ -ተጎታችን ሙሉ በሙሉ እና ሁሌም በግራ በኩል ይለፉት። ማንኛውንም ተሽከርካሪ ሲያልፉ ከዘገዩ፣ ከፉት ለፊቱ መንገድ ላይ እንቅፋት ቢያጋጥም ትራኩ የማምለጫ እርምጃ ለመውሰድ እርሶ ያሉበት ቦታ አያስችለውም።
- **በጣም በቅርብ መከተል ወይም ጭራ መሆን** ትራክን ወይም መኪናን ጭራ ሆኖ በጣም በቅርብ መከተል አደገኛ ነው ምክንያቱም ከፊት ለፊቶ ያለው ተሽከርካሪ ባጭሩ ቢያቆም የራሶትን የደህንነት ቦታ ይወስዳሉ። ከትራክ ሃላ ሲከተሉ፣ የትራክ ነጂውን የውጭ መስታዋቶች ማየት የማይችሉ ከሆነ፣ የትራክ ነጂው እርሶን የሚያይበት ምንም አይነት መንገድ የለም። እርሶ የሚከተሉት ተሽከርካሪ መንገዱ ላይ አንድን ነገር ቢመታ፣ የእርሶን መኪና ከፊቲ ከመምታቱ በፉት እርምጃ ለመውሰድ ምንም ግዜ አይኖሮትም።
- **የሚመጣውን የተጎታች-ትራክተር ፍጥነት እና መጠን በፍጹም አነስተኛ ነው ብለው ግምት አይውሰዱ።**
  የትራክተር-ተጎታች መጠኑ ትልቅ ስለሆነ ብዙ ግዜ ከሚጓዝበት ፍጥነት ባነሰ የሚጓዝ መስሎ ይታያል። በርካታ ቁጥር ያላቸው የመኪና-ትራክ ግጭቶች መገናኛ መንገዶች ላይ የሚፈጸሙት የመኪናዎቹ ነጂዎች ትራኩ ምን ያህል ቅርብ እንደሆነ ወይም በምን ያህል ፍጥነት እየመጣ እንደሆነ ስለማይገነዘቡ ነው።

ለትምህርት ቤት ተሽከርካሪዎች ማቆም

የትምህርት ቤት ተሽከርካሪ ሲቆም ወይም ጎዳናው ላይ ቆሞ ከሆነ እና በየተራ የሚበሩት ቀይ መብራቱን እያሰራ ከሆነ፣ ሁሉም ተሽከርካሪዎች ከትምህርት ቤቱ ተሽከርካሪ ፊት ወይም ሃላ ቢያንስ 20 ጫማ መቆም አለባቸው። በየተራ የሚበሩት ቀይ መብራቶች እስከሚጠፉ ድረስ ማንም መቀጠል አይችልም። የሚበሩት መብራቶች ከጠፉ በሃላም ነጅዎች ጥንቃቄ መውሰድን መቀጠል አለባቸው። የሌሎች ተሽከርካሪዎች ነጂዎች የተከፈለ ሀይዌይ ላይ ሆነው እና የትምህርት ቤት ተሽከርካሪው በተከፋፈለው ሀይዌይ በሌላኛው በኩል ከሆነ የማቆም ግዴታ የለባቸውም።

መንገዱን ከሞተርሳይክሊስቶች ጋር መጋራት

ወደ ግማሽ ገደማ የሚሆኑ ሁሉም ሞት የሚያስከትሉ የሞተር ሳይክል አደጋዎች ከመኪናዎች ጋር የተገናኙ ናቸው። ከሞተር ሳይክሎች ጋር ሲጋጩ፣ ነጅዎች ብዙውን ግዜ ሞተር ሳይክሉን በፍጹም አላየሁትም ይላሉ። መጠናቸው ለማየት በጣም አስቸጋሪ ስለሚያደርገው የመኪናዎች ነጅዎች ሞተር ሳይክሎችን ነቅተው ማየት አለባቸው። ሁልግዜ ነቃ ብለው ይጠብቁ እና ሞተር ሳይክል እያለፎት እንደሆነ ለማረጋገጥ የማይታየውን ቦታዎን(ብላይንድ ስፖቶን) ቶሎቶሎ ያረጋግጡ። በመገናኛ(ኢንተርሴክሽን) ላይ በሚዞሩበት ወቅት እና ከጎን መንገድ ወይም ከመግቢያ መንገዶች(ድራይቨዌይ) ሲወጡ በተለየ ሁኔታ ለሞተርሳይክሎች ነቅተው ማየት አለቦት። ሞተርሳይክል ሙሉውን መስመር ለመጠቀም መብት አለው። ሞተርሳይክል እንደፈለጉ ለማንድረግ በጣም ቀላል ስለሆነ፣ አሽከርካሪው እንቅፋቶችን ለማስወድ በመስመሩ ውስጥ ሆኖ ከአንድ ጎን ወደ ሌላ ጎን ይሄድ ይሆናል። ሞተርሳይክል በሚያልፍ ግዜ በቂ ቦታ ይስጡት እና ሞተርሳይክልን በዚያው መስመር ውስጥ መቅደም ወይም ማለፍ ከህጉ ውጪ እንደሆነ ያስታውሱ። ሞተርሳይክል በሚከተሉበት ግዜ በተለይ ጥንቃቄ ይውሰዱ። ሞተርሳይክል ከመኪናዎች ይልቅ በበለጠ በፍጥነት መቆም ስለሚችል በሁሉም ግዜ ደህንነትን የሚያስጠብቅ የመከተያ ርቀትን ይጠብቁ።

መንገዱን ከብስኪሊቶች ጋር መጋራት

የብስክሊቶች ቅድሚያ የማግኘት መብት

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ብስኪሌቶች እንደ ተሽከርካሪዎች ነው የሚወሰዱት። ሞተር ተሽከርካሮዎች እንዳላቸው ብስኪሌቶችም መብቶች እና ግዴታዎች አሏቸው።
መገናኛዎች(ኢንተርሴክሽኖች) ላይ በሚያልፉበት ግዜ እና በሚታጠፉበት ግዜ ሞተረኞች ለብስኪሌቶች የቅድሚያ መብታቸውን ሊሰጧቸው ይገባል። ብዙ ብሰኪሌቶች የመታጠፉያ ምልክቶች የሏቸውም እና ነጂዎቻቸው ሊያደርጉ ያሰቡትን ሊያስጠነቅቆት ሲፈልጉ የእጅ እና የክንድ ምልክቶችን ይጠቀማሉ።

ባለብስክሊትን መከተል

ባለብስክሊት ጋር ሲጠጉ ያቀዝቅዙ። የክላክስ (ጥሩንባ) መጠቀምን ያስወግዱ። ብዙግዜ ባለባይስክሎች የሚመጣ ተሽከርካሪን በቀላሉ መስማት ይችላሉ እና ከፍ ያለ ድምጽ ሳይክል ነጂውን በማስደንገጥ አደጋ ሊያመጣ ይችላል።
ብስክሊትን በቅርቡ አይከተሉ። ብስክሊቶች ቶሎ ሊቆሙ እና እንደ ፈለገ ሊያንቀሳቅስ ይችላል እና ባለባይስክል የመንገድ አደጋን ለማስወገድ ሲል በፍጥነት ሊዞር ወይም ፍጥነት ሊቀይር ይችላል። በተለይ ወጣት ባለባይስክሎች ያልተጠበቀ የአቅጣጫ ለውጥ የማድረግ እድላቸው የበለጠ ነው።

ባለባይስክልን ማለፍ

ባለባይስክልን ሲያልፉ፣ ደህና እስኪሆን እና በቂ የሆነ ግልፅ ቦታን እስኪኖር ይጠብቁ (ብዙግዜ ከተሽከርካሪዎ ጎን አንስቶ ሶስት ጫማ) እና ብስክሊቱን ወደሃላ በማሳያ መስታዋቶ በግልጽ ማየት ከቻሉ በሃላ ወደ መስመሮ ይመለሱ። ነጅዎቹን ለማስጠንቀቅ ወይም ለማንቃት ክላክስ (ጥሩንባን) አይጠቀሙ። በደህና ማለፍ የማይችሉ ከሆነ፣ ፍጥነቶች ይቀንሱ፣ ብስክሌቱን ይከተሉ እና ለማለፍ ደህና የሆነ እድል እሲያገኙ ድረስ ይጠብቁ። ብስክሊት መነዳት ያለበት በተቻለ መጠን በመንገዱ በቀኝ ጎን በኩል ነው። ሆኖም ግን፣ ባለሳይክሎች የመታጠፉያ መስመሮችንም እንደሚጠቀሙ ይጠበቃል። ሲታጠፉ ከብስክሊት ትራፊክ ጋር በደህና ይቀላቀሉ። የብስክሊት ትራፊክ ባለበት መስመር ወደ ቀኝ አይታጠፉ። ልምድ ያለው ባለሳይክሊስት በሰአት ፍጥነቱ 20-30 ማይል መድረሱ የተለመደ ነው እና ከሚያስቡት በላይ ቅርብ ሊሆን ይችላል።

መንገዱን ከስትሪትካር ጋር መጋራት

ስትሪትካሮች በህዝብ መንገዶችን ላይ በተሰኩ ገመዶች የሚሰሩ የተሳፋሪዎች ተሽከርካሪዎች ናቸው። ተሽከርካሪዎቹ በተቀላቀለ ትራፊክ እና/ወይም ለብቻቸው የቅድሚያ ሚያገኙበት ቦታ ላይ ሊሰሩ ይችላሉ። ከተያያዙ ባሶች(አርቲኩሌትድ ባሶች) ጋር ተመሳሳይ መጠን ያላቸው ሲሆን፣ ስትሪትካሮች የበለጠ ተሳፋሪ ይያዛሉ እና በአማካኝ በሰአት ከ25 እስከ 35 ማይል ይንቀሳቀሳሉ። ስትሪትካሮች የሚንቀሳቀሱበት ፍጥነት ያካባቢ ባሶች ከሚሄዱበት ጋር ተመሳሳይ ሲሆን፣ ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ ያልበለጠ እና ከትራፊኩ ፍሰት ጋር አብረው ሚሄዱበት ነው። ነጅዎች የሚታዩ የትራፉክ ምልክቶችን መከተል አለባቸው እና ለሚንቀሳቀሱ ስትሪክካሮች መጠንቀቅ አለባቸው።

ስትሪትካርን ማለፍ

ተሳፋሪዎች እየገቡ ወይም እየወጡ ሊሆን ስለሚችል የቆመ ስትሪትካርን ሲያልፉ የላቀ ጥንቃቄ ያድርጉ። በአንድ አይነት አቅጣጫ እየተጓዙ የቆመን ስትሪትካርን ሲያልፉ፣ በጣም ከፍተኛ ጥንቃቄ ያድርጉ፣ ደህና እስኪሆን ድረስ ይጠብቁ፣ እና በስትሪት ካሩ በግራ በኩል ይለፉ።

በስትሪትካር መሄጃ መንገድ በኩል ማቆም

የዲስትሪክት ህግ የስትሪትካር መሄጃ መንገድ ላይ ወይም ውስጥ ወይም ከስትሪትካር መደብ አጠገብ አንድን ተሽከርካሪ ማቆም(ፓርክ ማድረግ)፣ መቆም(ስቶፒንግ)፣ ወይም ቆም ማድረግ(ስታንዲንግ) ይከለክላል። ይህንን ህግ የሚጥስ ተሽከርካሪ ለገንዘብ ቅጣት እና መነሳት(ሪሙቪንግ) ወይም ኢምፓንዲንግ ይጋለጣል።

በስትሪትካር መሄጃ መንገች በኩል ሲቆም(ፓርክ ሲደረግ):

- በሀዲዶቹ(ትራኮቹ) ላይ አያቁሙ
- ተሽከርካሪዎን ሙሉ ነጭ ቀለም መስመር ውስጥ ያቁሙ
- የተሽከርካሪን በሮች በሚጠቀሙበት ወቅት ከሚመጡት የስትሪትካሮች ይጠንቀቁ
- ደርቦ ማቆም ህገወጥ ነው

CORQUEES PARK

የማሽከርከር(የመንዳት) ደንቦች

ቀኝዎን ይያዙ

የእርሶ ተሽከርካሪ ሌላ ተሽከርካሪን ወይም ባለብስክሊትን ቀድሞ ለመሄድ ወይም ለማለፍ ወይም ወደግራ ለመታጠፍ በሚልበት ግዜ ካልሆነ በስተቀር ቀኝዎን መያዝይ ኖርብዎታል። በባለሁለት መስመር(ሌን) ወይም በሌላ ጠባብ ሀይዌይ ላይ ለሚመጣው መኪና የተከፈተውን ወይም የተሻሻለውን መንገድ ግማሽ ሊለቁ ይገባል።

ምልክት ማሳየት

ከመታጠፍዎ በፊት ቢያንስ 100 ጫማ ያህል ሲቀርዎ ጀምረው የመታጠፊያ ምልክት፣ የክንድ ወይም የእጅ ምልክት ወይም ሁለቱንም ያለማቋረጥ መስጠት አለቦት። በከፍተኛ ፍጥነት በሚነዱበት ጊዜ ከዚህ በበለጠ ርቀት እና ረዘም ላለ ጊዜ ምልክት ማሳየት አለቦት። በተለይ በሁሉም ሀይዌዮች ላይ መስመሮችን(ሌኖችን) በሚቀይሩበት ጊዜ ይህ አስፍላጊ ነው። የመንገድ መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) እንዳለፉ የሚታጠፉ ከሆነ ወደ መገናኛው(ኢንተርሴክሽን) እንደደረሱ ምልክት ያሳዩ።

ማለፍ

በግራ በኩል ማለፍ ተመራጭ ነው። ይሁንና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በአንድ አቅጣጫ ብቻ ሊሚሄድ መንገድ(ዋን ዌይ ሮድ) ላይ ከአንድ በላይ የትራፊክ መስመር የሚበቃ ስፍራ እስካለ ድረስ በቀኝም ይሁን በግራ በኩል ማለፍ በህግ የተፈቀደ ነው። በተጨማሪም አራት ወይም ከዚያ በላይ መስመሮች(ሌኖች) ባላቸው ሀይዌይ ላይ በቀኝ ወይም በግራ በኩል ማለፍ በህግ ይተፈቀደ ነው።

በባለ ሁለት መስመር(ሌን) ሀይዌዮች ላይ ማለፍ የማይችሉበት ጊዜ

በሚከተሉት ሁኔታዎች ማለፍ ኣይችሉም:

- በመንገዱ መካከል ላይ የተሰመረው ሙሉ(ያልተቆራረጠ) ቢጫ መስመር በእርስዎ በኩል ከሆነ
- ሁለት ሙሉ ቢጫ መስመሮች ያሉ እንደሆነ
- ማለፍ እየመጡ ባሉ ተሽከርካሪዎች ደህነኛ አሰራር ላይ ችግር የሚፈጥር ከሆነ
- ወደ የዳገት ጫፍ ላይ እየተጠጉ ወይም መጠምዘዣ ላይ ከሆኑና ከፊትዎ ያለውን በበቂ ሁኔታ ኣጥርተው ማየት የማይችሉ ከሆነ
- መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) እያቋረጡ ከሆኑ ወይም ከመጋጠሚያው በ100 ጫማ ርቀት ላይ የሚገኙ ከሆነ
- የባቡር ሃዲድ ማቋረጫ ላይ እያቋረጡ ወይም በ100 ጫማ ርቀት ላይ የሚግኙ ከሆነ
- ከማናቸውም ድልድይ፣ መንገዱን የሚሸከም ድልድይ (ቪያደክት) ወይም ዋሻ(ታነል) በ100 ጫማ ርቀት እየተጠጉ ሳሉ እይታው ከተከለለ
- በሀይዌይ የቀኝ ወይም የግራ በመንገዱ ጎን ያለው ቦታ (ሾልደር) ላይ
- በሌላ ተሽከርካሪ በመታለፍ ላይ እያሉ ፍጥነትዎን መጨመር የለብዎትም
- “ማለፍ የማይቻልበት ኣካባቢ” (“no-passing zone”) ምልክት መጨረሻ ላይ ደረሱ ማለት ከዚያ በኋላ ማለፍ ኣስተማማኝ ነው ማለት ሳይሆን ኣስተማማኝ ሲሆን ብቻ ማለፍ በሕግ የተፈቀደ ነው ማለት ነው

በባለ ሁለት መስመር(ሌን) ሀይዌይ ላይ መቅደም እና ማለፍ

በባለሁለት መስመር(ሌን) ሀይዌይ ላይ ማናችውንም ተሽከርካሪ ሲቀድሙ በግራ በኩል ይለፉ። የመካከለኛውን የተሰመረ መስመር ከማለፍዎ በፊት ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ ተሽከርካሪ ከመድረሱ ወይም መተላለፍ የማይቻልበት አካባቢ ከመጀመሩ በፊት ወደቀኙ መስመር(ሌን) ተመልሰው ለመግባት የሚበቃ ጊዜ መኖሩን ያረጋግጡ። በማለፍ ላይ እያሉ ከሚመጣው ትራፊክ ጋር ሳይገናኙ ሙሉ በሙሉ ማለፍ የሚያስችል ጊዜ ላይኖርዎት እንደሚችል ከገመቱ ፍጥነትዎን በመቀነስ እያለፉት ከነበረው ተሽከርካሪ ኋላ ወዳለው መስመር(ሌን) ይመለሱ። በሚገቡበት መስመር(ሌን) አንፃር የቀኝ ወይም የግራ ምልክት (ፍሬቻ) በማብራት ከእርስዎ ኋላ እና ፊት ያሉ አሽከርካሪዎችን ያሳውቁ። አንድን ተሽከርካሪ በሚያልፉበት ጊዜ የታለፈውን መኪና ሁለት የፊት መብራቶች በኋላ ማሳያ መስታወት ሲመለከቱ ወደ ቀኝ መስመር(ሌን) መመለስ ይኖርብዎታል። አንድን ባለሳይክል ሲያልፉ በትንሹ የሶስት ጫማ መተላለፊያ(ክሊራንስ) መተው ይገባዎታል። አንድን ባለሳይክል ሲያልፉ ክላክስ(ጥሩንባ) አያድርጉ።

እየተቀደመ ያለውን ተሽከርካሪ እየነዱ ከሆነ ለሚቀድመው ተሽከርካሪ ወደቀኝ ቦታ ይልቀቁ። ሙሉ በሙሉ አልፎ እስኪጨርስ ድረስ ፍጥነትዎን አይጨምሩ። በቀኝ በኩል ማለፍ የሚችሉት እየተቀደመ ያለው ተሽከርካሪ ወደግራ እየታጠፈ ወይም ሊታጠፍ ከሆነ ብቻ ነው። ነገር ግን በመንገዱ መንዳት በሚፈቀድበት ክፍል መቆየት ይኖርብዎታል። በመንገዱ የጎን ቦታ(ሾልደር) ላይ በመንዳት ሌላ ተሽከርካሪን ማለፍ አይችሉም።

በባለ ምልክት መስመሮች (Marked Lanes) መንገዶች ላይ ስለመንዳት

- በአንድ መስመር(ሌን) ውስጥ መቆየት አለብዎ።
- በከፊል በአንድ መስመር(ሌን) በከፊል ደግሞ በሌላኛው መስመር(ሌን) ማሽከርከር አይችሉም።
- ከአንድ መስመር(ሌን) ወደ ሌላ ሌን በደኅንነት ሁኔታ ማድረግ ካለቻሉ በስተቀር መሸጋገር የለብዎትም።
- መስመር(ሌን) ከመቀየርዎ 300 ጫማ ባላነሰ ርቀት ጀምሮ ሌን ለመቀየር ማሰብዎን የሚያሳይ ምልክት ማሳየት አለብዎ። ከፊትዎ እና ከሃላ ያሉ አሽከርካሪዎች ተገቢውን እርምጃ እንዲወስዱ ከዚህ ቀደም ብለው ምልክት ቢሰጡ ይመረጣል።
- በሚነዱበት አቅጣጫ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ መስመሮች(ሌኖች) ባሉት ሀይዌይ ላይ ካለው የትራፊክ ፍሰት ዝግ ባለ ፍጥነት ሲያሽከረክሩ ወደ ቀኙ ሌን በመቀየር እዚያው ሊቆዩ ይገባል።
- በመንገዱ ጎን ያለው ቦታ (ሾልደሩ) ላይ ተሽከርካሪ ቆሞ ካዩ ፍጥነትዎን በመቀነስ ወደ መስመሮ(ሌንዎ) የግራ ክፍል ወይም ካለ ወደ ቀጣዩ ሌን ይለፉ።

መታጠፍ

ወደቀኝ መታጠፍ

- ከመታጠፍዎ በደንብ አስቀድሞ በሰተቀኝ ወደ ጥግ ወዳለው መስመር(ሌን) ይግቡ
- ለመታጠፍ ማሰብዎን ቢያንስ ለ100 ጫማ ያህል ምልክት ያሳዩ
- በመሻገሪያ ላይ ለሚገኙ እግረኞች ቅድሚያ ይስጡ
- ከእርስዎ ፊት እንደርስዎ ወደቀኝ በመታጠፍ ላይ የሚገኙ ተሽከርካሪዎችን ያስተውሉ።
- በእርስዎ እና በመንገዱ ጎን መካከል ለሚነዱ ብስክሌትኞች ቅድሚያ ይስጡ።
- በእርስዎ አቅጣጫ ወደ ቀኝ ወደሚወስደው መስመር(ሌን) ይታጠፉ።
- ቀይ መብራት ባለበት ወደቀኝ ሕጋዊ መታጠፍ ሲያደርጉ መገናኛው(ኢንተርሴክሽኑ) ላይ ከመድረስዎ በፊት የእግረኛ መሻገሪያው መስመሩ ላይ ሙሉ በሙሉ ማቆም ይኖርብዎታል።

ወደ ግራ መታጠፍ

- ከመታጠፍዎ በደንብ አስቀድሞ እርስዎ ባሉበት ሀይዌይ በሚገኘው የግራ መስመር(ሌን) ይግቡ
- ለመታጠፍ ማሰብዎን ቢያንስ በ100 ጫማ ርቀት ያህል ምልክት ይስጡ።
- ለመጪ ትራፊክ ብስክሌቶችን ጨምሮ ቅድሚያ ይስጡ።
- የእግረኛ መሻገሪያ ላይ ለሚገኙ እግረኞች ቅድሚያ ይስጡ።
- በመምጣት ላይ ያለ ትራፊክ እስከሚያልፍ በመጠበቅ ላይ ሳሉ መገናኛውን(ኢንተርሴክሽን) አይዝጉ።
- በእርስዎ አቅጣጫ ወደ ግራ ወደሚወስደው መስመር(ሌን) ይታጠፉ።
- በመንገድዎ ወዳለው የቀኝ ሌን ሊያስገባዎ በሚችል ሁኔታ ማእዘኑን(ኮርነሩን) አያቋርጡ ወይም መታጠፊያውን በስፋት አይታጠፉ።
- በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በቀይ መብራት ላይ ወደ ግራ መታጠፍ ሕገወጥ ነው።

የፊት መብራት ስለመጠቀም

ትንሽ ጨረር መብራት

የፊት መስታወቱ መጥረጊያዎች በመስራት ላይ ሳሉ ሁልጊዜ የፊት መብራት ያብሩ።ሌሎች ተሽከርካሪዎችን በሚጠጉበት ወይም በቅርበት በሚከተሉበት ጊዜ ትንሹን ጨረር ያብሩ። እንዲሁም፣ ትንሽ ጨረር መብራቶች ከጎዳና መብራቶች ጋር እና በጭጋግ ጊዜ መብራት ኣለባቸው።

- የፊት መብራትዎን ጸጋይ ከጠለቀች ከግማሽ ሰኣት በኋላ እና ጸጋይ ከመውጣቷ ከግማሽ ሰኣት በፊት ማብራት ይኖርብዎታል።
- በሌሎች ጊዜያት በ500 ጫማ ወይም ከዚያ ባነሰ ርቀት ውስጥ በሀይዌይ ላይ የሚገኙ ሰዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን በግልጽ ማየት ካልቻሉ የፊት መብራት ማብራት ይኖርብዎታል።
- በዋሻ (በታነል) ውስጥ ሲነዱ የፊት መብራት ማብራት ይገባዎታል።

ትልቅ ጨረር መብራት

በጨለማ መንገዶች ከፊት ያሉ ሰዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን ለማየት ትልቅ ጨረር መብራቶችን ይጠቀሙ። ትልቅ ጨረር መብራቶችን ከፊትዎ የሚገኙ ሰዎችን ወይም ተሽከርካሪዎችን ለማየት አስፍላጊ በሆነበት ጊዜ ሁሉ መጠቀም ይገባዎታል፣ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በስተቀር ፡

- በመምጣት ላይ ያሉ ተሽከርካሪዎችን ከመገናኘትዎ በፉት 500 ጫማ አስቀድሞ ወደ ትንሹ ጨረር መብራት መቀየር አለብዎ
- አንድን ተሽከርካሪ በ300 ጫማ ወይም ከዚያ ባነሰ ርቀት ሲከተሉ ወደ ትንሹ ጨረር መቀየር አለብዎ

ኃይል ቆጣቢ ምክሮች

በጥንቃቄ በማሽከርከር የተሻለ የነዳጅ ማይሌጅ ማግኘት እና ለነዳጅ የሚያወጡትን ወጪ መቆጠብ ይችላሉ። ይኸውም የሚከተሉትን በማድረግ ነው፡

- ፍጥነትዎን ሲጨምሩ ቀስ በቀስ ይሁን
- በተረጋጋ ሁኔታ እና በመሀከለኛ ፍጥነት ያሽከርክሩ
- ማቆሚያዎችን ቀድሞ በማስላት ባንዴ ማቆምን ያስቀሩ
- አስፈላጊ ያልሆኑ መንዳቶችን ያስወግዱ
- ከተቻለ ጉዞዎችን በአንድ ላይ ያድርጉ እና ተሽከርካሪዎችን በጋራ ይጠቀሙ

የማቆሚያ(ፓርኪንግ) ደንቦች

ተሽከርካሪን በመንገድ ላይ ሲያቆሙ ሞተሩን ማጥፋት፣ ኢግኒሽኑን መቆለፍ፣ ቁልፉን ማውጣት እና የፓርኪንግ ፍሬኑን ማድረግ ይኖርብዎታል። መስታዎቶቹን መዝጋት፣ በሮችን መቆለፍ እና ውድ እቃዎች እንዳይታዩ ማድረግ የሚመከሩት ነው። ልጆች፣ ኣረጋውያን እና የቤት እንስሳት ያለ ጠባቂ ተሽከርካሪ ውስጥ በፍፁም መተው የለባቸውም።



ትይዩ(ፓራራል) ፓርኪንግ

በባለሁለት መንገድ ላይ በትይዩ ፓርክ ሲያደርጉ ያለው ክፍት ስፍራ ለመኪናዎ በቂ መሆኑን ያረጋግጡ፣ እንዲሁም ከከርቡ ትይዩ እና በ12 ኢንች ርቀት ማቆም ይገባዎታል። ወደ ቦታው ሲጠጉ ምልክት ያሳዩ እና ከተሽከርካሪው ሃላ ሊኖሩ የሚችሉ ተሽከርካሪዎችን በመስታወት ማየት ይገባዎታል። እርስዎን የሚከተልዎ ኣሽከርካሪ የሚያቆም ከሆነ ከእርስዎ ብዙ ራቅ ብሎ ማቆም ኣለበት። ነገር ግን ከሃላዎ ያለው ኣሽከርካሪ በጣም በቅርበት የሚከተልዎ ከሆነ በድንገት ኣያቁሙ፣ መንዳትዎን በመቀጠል ሌላ ቦታ ይፈልጉ። ከሃላዎ ሌላ ተሽከርካሪ እያለ በድንገት ማቆም የሃላ ግጭትን ሊያስከትል ይችላል።

የትይዩ ፓርኪንግ ኣደራረግ ደረጃዎች:

A. ቦታውን በማለፍ ወደፊት በመሄድ ከፊት ካቆመው ተሽከርካሪ ከ2-5 ጫማ ርቀት በቀጥታ ትይዩ መሥመር እስከሚይዙ ድረስ ይቀጥሉ። በጣም መቅረብ ወይም በጣም መራቅ ማቆምን ኣስቸጋሪ ያደርገዋል። እግርዎ በፍሬኑ ላይ እንዳለ ወደ ወደሃላ ማርሽ(ሪቨርስ) ይቀይሩ በመዞር ያለውን ትራፊክ ያስተውሉ መተላለፊያው ነጻ መሆኑን ያረጋግጡ።

B. ፍሬኑን ይልቀቁ፣ ወደኋላ በዝግታ መንዳት ይጀምሩ፣ መጀመርያ ወደ ቀኝ ቀጥሎ ውድ ግራ የ ‘S’ መታጠፍ ያድርጉ። በተደጋጋሚ ወደ ፊት እና ወደ ኋላ በመመልከት በመጠምዘዝ ላይ እያሉ በተሽከርካሪው ዙርያ በቂ ሥፍራ መኖሩን ያረጋግጡ።

C. የተሽከርካሪው የኋለኛ ክፍል በኣብዛኛው በሥፍራው ውስጥ ከገባ በኋላ ቀጥ ለማድረግ ወደ ሌለኛው ኣቅጣጫ መጠምዘዝ ይጀምሩ።

D. የተሽከርካሪውን ኣቀማመጥ እንዳስፈላጊነቱ በቦታው መካከል ያስተካክሉ።

E. ጎማዎቹ ከከርቡ በ12 ኢንች ርቀት ላይ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ካልሆኑ ያውጡ እና እንደገና ይሞክሩ። በሩን ከመክፈትዎ በፊት ሁልጊዜ የሚያልፉ ተሽከርካሪዎች እና ሰዎች አለመኖራቸውን ያረጋግጡ።

ተሽከርካሪዎን በመንገድ ላይ ካቆሙበት ሥፍራ ሲያንቀሳቅሱ ምልክት ማሳየት፣ የማለፍ ቅድሚያ መስጠት እና ወደ መንገድ መግባቱ አመቺ ሲሆን መግባት ይኖርብዎታል።

ተሽከርካሪን ደርቦ ማቆም (ደብል ፓርክ) ትራፊክን ስለሚያስተጓጉል እና ኣደጋ ስለሚያስከትል የተከለከለ ነው።

በአቀበት ላይ ማቆም

ተሽከርካሪው በፓርክ ላይ መሆኑን እና የፓርኪንግ(ማቆሚያ) ፍሬኑ በትክክል መያዙን ያረጋግጡ። ማኑዋል ትራንስሚሽን ካለዎ ተሽከርካሪውን በጊር ላይ በመተው የፓርኪንግ ፍሬኑን ያድርጉ። ተሽከርካሪው ወደ ትራፊክ ተንከባሎ እንዳይገባ ለመከላከል የፊት ጎማዎችን እንደሚከተለው ይጠምዝዙ፡

- ቁልቁል ላይ ሲያቆሙ ወደ ከርቡ
- ዳገት ላይ ሲያቆሙ ከከርቡ ወደዚያ

ተሽከርካሪዎን ከርብ በሌለበት ዳገት ወይም ቁልቁል ላይ ሲያቆሙ የፊት ጎማዎቹን ወደ መንገዱ ጠርዝ (ከርቡ ይሆንበት በነበረው ቦታ) ይጠምዝዙ።

በሀይዌይ ላይ ስለማቆም

ተሽከርካሪዎ ካልተበላሸ ወይም ሊንቀሳቀስ ካልቻለ በስተቀር በማናቸውም የተከፈተ(ፔቭድ) ወይም የመንጃ መንገድ በሆነ የሀይዌ ቦታ ላይ በፍፁም ማቆም የለብዎትም። በተቻለዎ መጠን ወደ ቀኝ ይለፉ። በሀይዌው የመንገዱ ጎን ቦታ(ሾልደር) ላይ ከፀሐይ መግቢያ እስከ ፀሐይ መውጫ ባለው ጊዜ ወይም ያለው ብርሃን በ1000 ጫማ ርቀት ሰዎችን ወይም ነገሮችን ማየት የማያስችል በሆነበት ሁኔታ ካቆሙ የሃዛርድ መብራትዎን ወይም የፓርኪንግ መብራትዎን (ተሽከርካሪው ካለው) ማብራት አለብዎ። የትራፊክ ፍሰትን የሚያስተጓጉል ወይም ተሽከርካሪን ወይም ማንኛውንም ሰው ለኣደጋ የሚያጋልጥ በር ኣይክፈቱ። ይልቁንም በከርቡ በኩል ያለውን በር ይጠቀሙ።

ስለማቆም

ኣቁም ማለት እንቅስቃሴን ኣቁም እንጂ ቀስ በቀስ ኣቁም ማለት ኣይደለም

- የአቁም(stop) ምልክት ካለ ከማቆሚያ መስመሩ(ካለ) በፊት ሙሉ ለሙሉ ማቆም ይኖርብዎታል። ከሌለ የእግረኛ መሻገሪያ መስመሩ ውስጥ ከመግባትዎ በፊት ማቆም አለብዎ።
- ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ የትራፊክ መብራት ካለ ሙሉ ለሙሉ ማቆም ኣለብዎ።
- የጸና ቀይ የትራፊክ መብራት ካለ መታጠፍን የሚከለክል ምልክት ከሌለ በስተቀር ወደ መገናኛው(ኢንተርሴክሽን) ላይ በጥንቃቄ በመግባት በቅድሚያ ሙሉ ለሙሉ በማቆም እና ለእግረኞች፣ ለብስክሌትኞች እና ሌሎች መገናኛውን በአግባቡ በመጠቀም ላይ ለሚገኝ ትራፊክ ቅድሚያ በመስጠት ወደ ቀኝ መታጠፍ ይችላሉ።
- ቅድሚያ ስጥ የሚል ምልክት ካለ እና ተሽከርካሪዎች ወይም እግረኞች ከምልክቱ ባሻገር ያለውን መንገድ እንዳይጠቀሙ ከያዙበት ሙሉ ለሙሉ ካቆሙ በኋላ መንገዱ ነጻ ሲሆን መቀጠል አለቦት።
- ከጠባብ መንገድ፣ ከመግቢያ መንገድ፣ ወይም ከግል መንገድ ወይም የፓርኪንግ ሥፍራ በመውጣት ላይ እያሉ ከሆነ እና በእግረኛ መንገድ ላይ አልፈው ወደ ጎዳና መውጣት ካለብዎ ወደ እግረኛ መንገዱ/ወደ መሻገሪያ መስመሩ ከመግባትዎ በፊት ማቆም እና ለእግረኞች፣ ለብስክሌተኞች እንዲሁም ለሌሎች ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት ይኖርብዎታል።
- ከመገናኛው(ኢንተርሴክሽን) ባሻገር ያለው መንገድ በትራፊክ ተዘግቶ ባለበት ሁኔታ ወደ መገናኛው ከመግባትዎ በፊት ማቆም እና መገናኛው መዘጋቱ ሲያበቃ ወደዚያው ማምራት ይኖርብዎታል። ሳጥኑን አይዝጉ! የእግረኛ መሻገሪያ መስመሩን አይዝጉ!
- ዝቅ ያለ መግቢያ እና/ወይም ብልጭ ብልጭ የሚል መብራት ባለው የባቡር ማቋረጫ ጋር ማቆም አለብዎ።

ማናቸውም ኣይነት ማቆም(ስቶፒንግ፣ ሰታንዲንግ፣ ፓርኪንግ) - የተከለከለ

ከሌላ ትራፊክ ጋር መጋጨትን ለማስቀረት ኣስፈላጊ ካልሆነ ወይም የፖሊስ መኮንንን ወይም ይፋዊ የሆነ የትራፊክ መቆጣጠሪያ መሳሪያን በመታዘዝ ካልሆነ በስተቀር በሚከተሉት ሁኔታዎች ተሽከርካሪዎን ኣያቁሙ:

- በሕዝባዊ መግቢያ መንገድ ፊት ለፊት
- በእግረኛ መተላለፊያ መንገድ ላይ
- መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) ውስጥ
- በእግር መሻገሪያ መስመር ላይ
- በደኅንነት ዞን እና የጎኑ ከርብ መካከል ወይም በደኅንነቱ ዞን ጫፎች በቅርብ በተቃራኒው ወገን ባለው ከርብ በ30 ጫማ ርቀት ውስጥ፣ የስቴቱ የሀይዌይ አስየተዳደር ወይም የኣካባቢው ባለስልጣን በምልክት ወይም መጠቆሚያ ሌላ ርቀት ካላስቀመጠ በስተቀር
- በዚያ ቆም ማለት(ሰታንዲንግ) ወይም ማቆም(ስቶፒንግ) ትራፊክን ሊያስትጓጉል የሚችል ከሆነ በማናቸውም የጎዳና ቁፋሮ ወይም ከልካይ ኣጠገብ ወይም በተቃራኒው በኩል

- በማናቸውም ድልድይ ወይም ሌላ ሀይዌይ ላይ በሚገኝ ከፍ ያለ ኣካል ወይም በሀይዌይ ዋሻ (ተነል) ወስጥ
- ማቆም የሚከለክል ይፋዊ ምልክት ባለበት ማናቸውም ሥፍራ
- ከትራፊክ ፍሰቱ ተቃራኒ በሆን ኣቅጣጫ

በሚከተሉት ሁኔታዎች ሰው ያለበትንም ሆነ የሌለበትን ተሽከርካሪ ትንሽ ማቆም(ስታንዲንግ) ወይም ማቆም (ፓርኪንግ) ክልክል ነው፡

- የግል መግቢያ መንገድ፣ የሕዝብ መግቢያ መንገድ፣ ወይም የጎሮ መንገድ(ኣሊይ) ፊት ለፊት ወይም በ5 ጫማ ርቀት
- በእሳት ኣደጋ ማጥፊያ ሀይድራንት 10 ጫማ ርቀት
- በመንገድ ዳርቻ ከሚገኝ ብልጭ ብልጭ ከሚል የመብራት ምልክት፣ ከአቁም(stop) ምልክት ወይም የትራፊክ መቆጣጠርያ ምልክት በ25 ጫማ ርቀት
- ከማናቸውም የእሳት ኣደጋ ጣቢያ መግቢያ መንገድ በ20 ጫማ ርቀት
- በመጠምዘዣ ላይ ወይም በአቀበት መዳረሻ በመንገዱ ገጽ ላይ ማለፍ ክልክል ነው የሚል ሙሉ(ያልተቆራረጠ) መስመሮች በሚታዩበት ሁኔታ
- ለአጭር ግዜ መቆም(ስታንዲንግ) በይፋዊ ምልክት በተከለከለበት ማናቸውም ቦታ
- ማናቸውም በመንገድ ጠርዝ ወይም ከርብ ላይ ባቆመ(ስቶፕ ወይም ፓርክ)ተሽከርካሪ ኣጠገብ በጎዳናው በኩል ባለው ወገን፣ ይህ ደርቦ ማቆም(ደብል ፓርኪንግ) ተደርጎ ይቆጠራል
- መንገድን ለመዝጋት በተቀመጠ መሰናክል ወይም ምልክት ፊት ለፊት

ሰው ያለበትንም ሆነ የሌለበትን ተሽከርካሪ ለጊዜው እቃ ወይም ሰው ለመጫን ካልሆነ በስተቀር በሚከተሉት ስፍራዎች ኣያቁሙ፡

- በአቅራቢያው ባለው የባባቡር ማቋረጫ ሃዲድ 50 ጫማ ውስጥ
- በይፋዊ ምልክት ማቆም(ፓርኪንግ) በተከለከለበት ማናቸውም ሥፍራ
- ጉዳት(ዲሳቢሊቲ) ያለቦት ግለሰብ ካልሆኑ በስተቀር ለጉዳተኞች ኣገልግሎት ብቻ መከለሉን በአግባቡ ምልክት የተደረገበት ቦታ ወይም ዞን ማቆም(ፓርኪንግ)

የትራፊክ ደንቦች

ወደሃላ ማዞር

አንዳንድ ግዜ መኪናዎትን የተዘጋ ቦታ ላይ ለማዞር ያስፈልጋል፣ ለምሳሌ የመንዳት ፈተናዎ ግዜ ወይም መንገዱ ሚያልቅበት (ዴድ ኤንድ) የሆነ መንገድ መጨረሻ ላይ መኪናዎትን ወደሃላ ለማዞር ያስፈልግ ይሆናል።

ይህንን ለማድረግ:

- ከመንገዱ የቀኝ መጨረሻ ይጀምሩ። ሌሎቹን ትራፊኩን ይመልከቱ እና የጸዳ ከሆነ መሪውን ወደግራ እየጠመዘዙ ቀስ ብለው ወደፊት ይቀጥሉ። ከመንገዱ ግራ ከርብ ወይም ከመንገዱ ጠርዝ የተወሰነ ኢንች ውስጥ ያቁሙ።
- ከዚያ መሪውን ወደቀኝ እየጠመዘዙ ቀስ ብለው ወደሃላ ይቀጥሉ።
- ከመንገዱ ቀኝ ከርብ ወይም ከመንገዱ ጠርዝ የተወሰነ ኢንች ውስጥ ያቁሙ።
- መሪውን ወደግራ እያዞሩ ቀስ ብለው ወደፊት ይቀጥሉ። ይሄ መዞሮትን ሊያጠናቅቀው ይገባል። ካልሆነ፣ ይህንኑ ሂደት እንደገና ይድገሙት።

የፍጥነት ገደቦች

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ትራፊክ ህጎች ጠቅላላ የፍጥነት ገደቦችን እና ልዩ የፍጥነት ገደቦችን ይሰጣል። ሁለቱንም መታዘዝ አለቦት። በእርግጥ ያለውን እና ሊመጣ የሚችለውን አደጋ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት፣ ማንም ሰው ባለው ሁኔታ ምክንያታዊ ከሆነው ፍጥነት በላይ ሊነዳ አይገባም። በማንኛውም ሁኔታ፣ መንገዱ ላይ ካለ ወይም በመግባት ላይ ካለ ማንኛውም ሰው፣ ተሽከርካሪ ወይም ሌላ ተጓዝ ጋር መጋጨትን ለማስወገድ ፍጥነት በቁጥጥር ውስጥ መሆን አለበት። ተሽከርካሪውን በደህንነት ለማንቀሳቀስ ወይም በህጉ መሰረት ዝቅተኛ ፍጥነት አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር፣ ማንም ሰው መደበኛውን ወይም ምክንያታዊ የሆነውን የትራፊክ ሂደት እስኪከለክሉ ድረስ ዝቅ ባለ ፍጥነት መንዳት የለባቸውም። ከተለጠፈው የፍጥነት ገደብ በፍጹም አይለፉ። እስከ ገደቡ ድረስ ሆኖ ትራፊክ በሚሄድበት አማካኝ ፍጥነት መጓዝ ደህንነትን ያስጠብቃል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከአማካኙ የትራፉክ ፍጥነት በተለዩ መጠን፣ ከፍተኛ ፍጥነትም ይሁን ዝቅተኛ፣ አደጋ የማጋጠሙ እድሎ መጠን እየጨመረ ይመጣል። አብዛኛዎቹ አደጋዎች ከፍጥነት ሌላ በሆኑ ምክንያቶች ይፈጠራሉ፣ ነገር ግን ፍጥነት የኪሳራውን እና የጉዳቱን ክብደቱን እና መጠኑን ይጨምረዋል።

የሚከተሉትን ፍሬ ነገሮች ግምት ውስጥ ያስገቡ:

- በሰአት 20 ማይል ከሚያጋጥም አደጋ በላይ በሰአት 60 ማይል ላይ የሚሆነው አደጋ ስምንት ግዜ የበለጠ የሞት እድል አለው።
- በተቃራኒ አቅጣጫ የሚሄዱ ተሽከርካሪዎች ከፉት ለፉት ሲጋጩ፣ የግጭቱ ፍጥነት የሁለቱ ተሽከርካሪዎች የነበራቸው ፍጥነት ድምር ነው። እያንዳንዱ በሰአት 50 ማይል ለሚጓዙ ሁለት ተሽከርካሪዎች ድምሩ በሰአት 100 ማይል ይሆናል።
- ጠጣር የሆነ የቆመን ነገር በሰአት 60 ማይል ፍጥነት መምታት ከ 10ኛ ፎቅ ህንጻ ከመውደቅ ጋር እኩል ነው።

የፍጥነት ገደብ ህጎች/ያልተለጠፈበት ከሆነ

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ከተማ ጎዳናዎች በሰዓት 25 ማይል ነው
በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ጓሮ መንገድ (አሊይ) በሰዓት 15 ማይል ነው
በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የትምህርት ቤት ዞን በሰዓት 15 ማይል ነው
በተራ ሀይዌዮች በሰዓት 30 – 50 ማይል
በተከፋፈሉ ሀይዌዮች በሰዓት 30 – 55 ማይል
ስቴቶች በሚያገናኙ(ኢንተርስቴት) ሀይዌዮች በሰዓት 55 – 75 ማይል

የፍጥነት ምልክቶች

የፍጥነት ገደብ ምልክቶች

የፍጥነት ገደብ ምልክቶች በነጭ የጀርባ ቀለም አራት ማዕዘን (ሬክታንግል) ላይ ጥቁር ፊደላት እና ቁጥሮች ያላቸው ሲሆኑ ህጋዊ የሚፈቀዱ ገደቦች ናቸው።

የማሳወቂያ (የምክር) የፍጥነት ምልክቶች

የማሳወቂያ የፍጥነት ምልክቶች በቢጫ ወይም ብርቱካን ጀርባ ውስጥ፣ ጥቁር ፊደላት ሲኖራቸው፣ በአብዛኛው በማስጠንቀቅያ ምልክት ስር ይታያሉ። የማሳወቂያ የፍጥነት ምልክቶች፣ ሁኔታዎች በፍጥነት ለመንዳት በአብዛኛው ደህና ያልሆኑ ሊያደርገው እንደሚችሉ ሊያስጠነቅቅዎ በሀይዌይ መንገድ ክፍሎች ይለጠፋሉ። ምንም እንኳን የማሳወቂያ የፍጥነት ምልክቶች የህግ ያክል ሃይል ባይኖራቸውም፣ ከገደቡ በላይ ከነዱ እና አደጋ ካጋጠሞት፣ አጠቃላይ የፍጥነት ገደብ እንደጣሱ ተደርጎ ይወሰዳል፣ ቲኬትም ሊያሰጥዎት ይችል ይሆናል።

ሌሎች የትራፊክ ህጎች

የደህንነት ዞኖች

በደህንነት ዞኖች፣ ማለት ለእግረኞች ብቻ የሚል ምልክት ያለበት የመንገድ ቦታ፣ በጭራሽ መንዳት የለብዎትም። በትራፊክ አቅራቢያ የቆሙ፣ የሚራመዱ፣ የተቀመጡ ወይም ብስክሌት የሚነዱ ሰዎች ባሉበት ሁሌ በጥንቃቄ ይለፉ።

ኮስቲንግ (Coasting)

ማርሾቹ በኒውትራል ሳሉ፣ ወይም ማርሾቹ ለመቀየር የፍሪስዮን ፔዳል (ክለች ፔዳል)ከሚገባው ጊዜ በላይ ጫና አድርገው በፍጹም አይንዱ። በፍጥነት እርምጃ መውሰድ ቢፈልጉ፣ ተሽከራሪውን ተገቢው ማርሽ ማምጣት ላይችሉ ይችላሉ።

የትምህርት ቤት መሻገርያ ጠባቂዎች(ጋርድስ) እና የትራፊክ ቁጥጥር መኮንኖች

የተፈቀደላቸው የመሻገርያ ጠባቂዎች እና የትራፊክ ቁጥጥር መኮንኖች የሚሰጡት ማንኛቸውም መመርያ መከተል ይኖርቦታል። የትምህርት ቤት መሻገርያ ጠባቂዎች እና የትራፊክ ቁጥጥር መኮንኖች፣ የተሽከርካሪዎች ትራፊክ የማስቆም፣ የመቆጣጠር እና የመምራት ስልጣን አላቸው። በአብዛኛው በትምህርት ቤቶች እና ዝግጅት ባለባቸው ቦታዎች አጠገብ፣ ወይም በማንኛቸውም አስፈላጊ ናቸው የተባሉ ቦታዎች ይገኛሉ።

U-ተርን

በየትኛውም አቅጣጫ የሚሄድ ሌላ ተሽከርካሪን በመንዳት ላይ ያለ ነጂ፣ ተሽከርካሪዎን ቢያንስ በ500 ጫማ ርቀት ማየት የማይችሉ ከሆነ፣ በመጠምዘዣ ወይም በአቀበት U-ተርን ማድረግ የለብዎትም። በትራፊክ መብራቶች በሚመሩ መገናኛ መንገዶ(ኢንተርሴክሽኖች)፣ ወይም በመገናኛ መንገዶቹ አጠገብ ባሉ መሻገሪያ ስፍራዎች U-ተርን ማድረግ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የተከለከሉ ናቸው።

የተለያዩ የጆሮ ማዳመጫዎች (ሄድሰቶች፣ ኢርፎኖች እና የጆሮ መድፈኛዎች) ማድረግ የተከለከለ ነው

አንድ ሰው፣ የሞቶር ተሽከርካሪ እየነዳ፣ ከራድዮ፣ ቴፕ ወይም የሲዲ ማጫወቻዎች ወይም ከሌሎች የድምጽ ማጫወቻዎች ጋር የተገናኙ የተለያዩ የጆሮ ማዳመጫዎች (ሄድሰቶች፣ ኢርፎኖች እና የጆሮ መድፈኛዎች) ማድረግ የለበትም። ለእጅ ስልኮች የጆሮ ማዳመጫዎች (ኢርፎኖች ወይም ኢርፕላጎች) መጠቀም ይፈቀዳል። መስማትን የሚያግዙ(ሂሪንግ ኤድ) መሳርያዎች መጠቀምም ይፈቀዳል።

የተሽከርካሪ መሳሪያ

የዩ.ኤስ መንግስት ከ1965 ጀምሮ፣ አደጋዎችን ለመቀነስ እና የአየር ብክለትን ለመቆጣጠር፣ ሁሉም በዩናይት ስቴትስ ለሽያጭ የሚቀርቡ የሞተር ተሽከርካሪዎች የተለያዩ ደህንነትን የሚጠብቁ መሳርያዎች እና የጭስ (ኢሚሽን) መቆጣጠርያ መሳርያዎች እንዲኖራቸው ያስገድዳል። በፌደራል እና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሞተር ተሽከርካሪ ህጎች መሰረት፣ ማንኛውም ሰው የሚከተሉትን እንዳያደርግ በህግ የተከለከለ ነው፡

- ማንኛውም የዩናይትድ ስቴትስ ወይም የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህግ፣ መመርያ፣ ድንጋጌ ወይም መስፈርት በሚያዘው መሰረት፣ በማንኛውም በሞተር ተሽከርካሪ፣ ተሳቢ፣ ግማሽ-ተሳቢ (ሰማይ-ትረይለር)፣ ወይም የዋልታ ተሳቢ (ፖል ትረይለር) ላይ የተገጠሙ የደህንነት መሳርያዎች ማውጣት ወይም መለወጥ
- ከ1968 ወይም ከዛ በኋላ በወጡ ሞዴሎች፣ በሞተር ተሽከርካሪዎች ፋብሪካዎች የተገጠሙ፣ እና ተሽከርካሪዎ የፌደራል ህግ ወይም ድንጋጌ መመርያ በሚያዘው መሰረት እነዚህ በፋብሪካ የተገጠሙ መሳርያዎች ያለው እንደሆነ፣ ማንኛቸውም የጭስ ማውጫ ሲስተም ጭስ መቆጣጠሪያ መሳሪያ (ኤግዞስት ሲስተም ኢሚሽን ኮንትሮል ዲቫይዝ) (ይሔም፣ ካትይሊክ ኮንቨርተር)፣ የነዳጅ ጋን መሙያ ማስገቢያ (ጋዞሊን ታንክ ፊለር ኢንሌት)፣ ወይም ክራንክኬዝ ቬንቲሌሽን መሳርያ ማውጣት፣ መለወጥ ወይም እንደማይሰሩ ማድረግ

የደህንነት ቀበቶ(ሲት ቤልት) ህግ/ይታጠቁት፣ ካልሆነ ቲኬት ይሰጥዎታል

ህጉ በ1997 ከወጣ በኋላ፣ ዲስትሪክትቱ በአገሪቱ ካሉት ጠንካራ እና ከሁሉ በይበልጥ አጠቃላይ የሆነ የደህንነት ቀበቶ ህጎች ያለው ሆኗል። የደህንነት ቀበቶ ተጠቃሚነት በ24% ጨመረ። ጉዳቶችን መከላከል ተቻለ። ሂወቶችም ተረፉ።

የደህንነት ቀበቶን ለመታጠቅ ጥቂት ሰኮንዶች ነው የሚወስደው። በጣም ቀላል ነው። ሆኖም፣ ሂወትዎንና የሚወድዋቸውን ሂወት ለመከላከል የሚወስዱት ከሁሉም የሚበልጥ አስፈላጊ እርምጃ ሊሆን ይችላል። የደህንነት ቀበቶ መታጠቅ በግጭት ጊዜ የመትረፍ እድሎን በከፍተኛ ይጨምረዋል። በተጨማሪ፣ ከሰከረ፣ ከደከመው ወይም ከሀይለኛ(አግሬሲቭ) ነጂ የሚከላከሉበት ዋነኛ መሳርያ ነው።

የደህንነት ቀበቶዎች መታጠቅ ይኖርባቸዋል

የተሳፋሪ መኪኖች፣ ትራኮች ፣ ትራክተሮች፣ ብዙ የተለያየ ጥቅም ያላቸውሸተሽከርካሪዎች ወይም የተሳፋሪ አውቶቡሶች ነጂዎች እና ሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ እንዲታጠቁ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ህግ ያዛል። አንድ ሰው አሽከርካሪው እና እያንዳንዱ ያለው ሰው የደህንነት ቀበቶ ካልታጠቁ በስተቀር እነዚህን ተሽከርካሪዎች ማንቀሳቀስ የለበትም።

ወደ ዳር እንዲቆሙ (ፑል ኦቨር) ይደረጋሉ

በሌሎች ብዙ ክልሎች (ስቴቶች) እንደሚደረገው፣ የተሽከርካሪ ነጂዎች ወይም ተሳፋሪዎች የመኪና ቀበቶ በስነ ስርዓት ስላልታጠቁ ብቻ ፖሊስ ተሽከርካሪዎች እንዲያቆም የዲስትሪክቱ ህግ ይፈቅዳል።

የ$50 መቀጮ እና 2 ነጥቦች

ነጂዎች፣ እና በፊት እና በኋላ ያሉ ሁሉም ተሳፋሪዎች፣ ከጥቂት ነገሮች በስተቀር፣ የደህንነት ቀበቶዎን በስነ ስርዓት ባለመታጠቅ የሚከፍሉት መቀጮ ነው። ነጂዎች፣ ሁሉም ተሳፋሪዎች የደህንነት ቀበቶ ግዴታን እንዲያሟሉ የማድረግ ሃላፊነት አላቸው።

የአካል ጎዳተኛ የሆኑ ሰዎች

አንድ የህክምና ስራ እንዲሰራ ፈቃድ ያለው ሐኪም፣ አንድን ሰው ባለው የአካል ጉዳት ወይም በሌላ የሕክምና ችግር ምክንያት፣ የደህንነት ቀበቶ መጠቀም ተገቢውን የሆነ መያዣን ሊከለክል ይችላል ብሎ ከወሰነ እና በጽሑፍ ካረጋገጠ፣ የደህንነት ቀበቶ ማድረግን የሚመለከቱ አንቀፆች እዚህ ሰው ላይ አይሰሩም ማለት ነው። የሐኪሙ ማረጋገጫ፣ የአካል ጉዳተኛው ሁኔታ እና የደህንነት ቀበቶ በታሰሩ ተገቢ እንዳልሆነ የሚያሳይ ምክንያት መዘርዘር አለበት። ሰርቲፊኬቱ (ማረጋገጫው) ተሽከርካሪ ውስጥ መቀመጥ ይኖርበታል። አንቀጾቹን የሚጥስ ሰው ህጉ የሚያዛቸው መቀጮዎች ይቀጣል።

የራስ መገደብያዎች (ሄድ ሪስትሬይንትስ)

የራስ መገደብያዎች የሚገጠሙት የአከርካሪ (ስፓይናል) እና የዊፕላሽ፣ ተሽከርካሪ ከኋላ ስትገጭ የሚያጋጥም የጭንቅላት ጉዳት፣ ጉዳትን ለመከላከል ነው። ተሽከርካሪዋን ለመንዳት ከማስነሳትዎ በፊት፣ በወንበርዎ የራስ መደገፍያ (ሄድ ረስት) ከጭንቅላትዎ ልክ በኋላ እንዲሆን አድርገው ያስተካክሉት። ይሄ ቦታ ከያንዳንዱ ነጂ የተለየ ነው፣ ስለዚህ፣ የራስ መደገፍያውን (ሄድ ረስት) በደንብ እንደሚከላከል ተደርጎ መስተካከል አለበት። አንዳንድ ተሽከርካሪዎች ሊስተካከል የማይችል ከፍ ያለ የጀርባ መደገፍያ ወንበር አላቸው።

የልጅ የደህንነት መቀመጫዎች (ቻይልድ ሴፍቲ ሲትስ)

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ፣ አንድ የሞቶር ተሽከርካሪ ነጂ፣ ማንኛውም ከ3ት ዓመት በታች ዕድሜ ያለው ልጅ፣ ልጁን በልጆች የደህንነት መቀመጫ በመኪናው ኋላ በስነ ስርዓት ታስሮ ካልተቀመጠ በስተቀር፣ ማጓጓዝ አይችልም።

ኤይር ባጎች

የኤየር ባጎች አስፈላጊ የደህንነት መሳርያዎች ናቸው። አመርቂ ውጤት የሚያስገኙት፣ ነጂዎች እና ተሳፋሪዎች በጭን እና ትከሻ ቀበቶዎች በደንብ ሲታጠቁና እና በተቻላቸው መጠን ወደ ኋላ ርቀው ሲቀመጡ ነው። አብዛኛዎቹ ኤየር ባጎች፣ ከመካከለኛ-እስከ-አደገኛ የከፊት-ለፊት አደጋ ሲያጋጥም እንዲነፉ ተደርገው ነው የተሰሩት። አንዳንድ በአናሳ ፍጥነት የሚያጋጥሙ አደጋዎች ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፤ ነገር ግን በአጠቃላይ፣ ኤየር ባጎች እንዲነፉባቸው እንደሚያደርጉ አይነት፣ አሳሳቢ ጉዳቶች አይደሉም። በማንኛውም ጊዜ የጭን እና የትከሻ ቀበቶዎች መጠቀም ያስፈልጋል፣ የኤየር ባጎች ያሉዋቸው መኪኖች ጋም ቢሆንም።

የኤየር ባጎች የሂወት ማትረፍ ችሎታ ለመጨመር፡

- የጭን እና ትኸሻ ቀበቶዎች በመጠቀም በማንኛውም ጊዜ የደህንነት ቀበቶን በስነ ስርዓት ይሰሩ
- እርጉዝ ሴቶች፣ የደህንነት ቀበቶን የጭን ክፍል ከሆድ በታች፣ በተቻለ መጠን ወደ ታች ወደ ዳሌዎች እና የጭን ላይኛው ክፍል አከባቢ፣ ያድርጉት
- በተቻለ መጠን ከመሪው እስከሚቻልዎት ድረስ ርቀው ይቀመጡ፤ ከመኪናው መሪ እስከ ደረት ያለው ርቀት ከ10-12 ኢንች ለማድረግ ይሞክሩ
- ዕድሜአቸው 12 እና ከዛ በታች የሆኑ ልጆች ሲጓዙ፣ ከኋላ ባለው የመኪና ወንበር፣ በልጆች የደህንነት ወንበር (ቻይልድ ሴፍቲ ሲት) ወይም ለዕድሜአቸው እና መጠናቸው ተገቢ የሆነ ቀበቶ አድርገው መቀመጥ ይኖርባቸዋል
- ህጻናት(ኢንፋንትስ)፣ የተሳፋሪ ወንበር የኤየር ባግ ባለበት በተሽከርካሪ የፊተኛ ተሳፋሪ ወንበር በኩል በፍጹም መጓዝ የለባቸውም
- እነዚህ የደህንነት ምክቶች መከተል የማይቻልዎት ከሆነ፣ የኤየር ባጎችን ቢያጠፍዋቸው የተሻለ ሊሆን ይችላል። ከሚከተሉት የአደጋ ቡድኖች መካከል አንዱ ላይ ያሉ ሰዎች የኤየር ባግ ማጥፊያና ማብሪያ ስዊች (አን-ኦፍ ስዊች) ስለ መግጠም ማሰብ ይኖርባቸዋል።
    - ህጻናትን በፊተኛው የተሳፋሪዎች ወንበር ወደ ኋላ በዞረ የህጻናት ወንበር የግድ ማጓጓዝ ግዴታ የሆነባቸው
    - ከ12 ዓመት በታች የሆኑ ልጆችን ከፊት በሚገኘው የተሳፋሪ ወንበር አድርገው ሚያጓጉዙ ግዴታ የሆነባቸው
    - የተለመደ የአነዳድ ቦታቸው መቀየር፣ እና ከመኪናው መሪ መሀከል እስከ መሀከለኛው የደረት አጥንታቸው ያለው ርቀት 10 ኢንች ማድረግ የማይችሉ ነጂዎች
    - በጤና ሁኔታ ምክንያት የኤየር ባጎች እንዲሰሩ ቢደረጉ የሚያደርሱት ልዩ አደጋ፣ በመኪና አደጋ ጊዜ ሊደርስ ከሚችል የራስ፣ የአንገት ወይም የደረት የመመታት አደጋ የበለጠ መሆኑ ሐኪማቸው ያሳሰበላቸው ሰዎች

የስራ ዞኖች

የስራ ዞን የሚባለው በሀይዌይ አከባቢ ያለ ግንባታ፣ እድሳት፣ ወይም የመጠቀሚያዎች (ዩቲሊቲ) ስራ እየተደረገበት ያለ ቦታ ነው። የስራ ዞኖች በአብዛኛው ጊዜ ያልተጠበቁ እና፣ አንዳንዴ ደግሞ ረጋ ያለ የትራፊክ ፍሰት የሚያሰናክሉ ስለሆኑ፣ ከፍተኛ ክህሎት አላቸው ለሚባሉ ነጂዎችም ሳይቀር ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ። ነጂዎች እነዚህን ቦታዎች ሲቃረቡ እና ሲያልፉ፣ ለነርሱ ለነጂዎቹ፣ ለእግረኞች እና ለሰራተኞች ደህንነት፣ ነጂዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ይገባቸዋል። ልዩ የስራ ዞን ትራፊክ ምልክቶች እና ሌሎች መሳርያዎች ስራው ከሚከናወንበት ቦታ አስቀድመው፣ እስከ የስራ ቦታው አልፎ ባሉ ቦታዎች ይተከላሉ። ዞኑ ቋሚ (እንደ ድልድይ የማስፋት ስራ እየተከናወነ ያለ) ስራ ሊሆን ይችላል፣ ወይም ደግሞ በመንገድ ቀስ ተብሎ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንደሚደረግ የአስፋልት መንገድ (ፔቭመንት) ማስለቀቅ ወይም መለጠፍ ያጠቃለለ ተንቀሳቃሽ ስራ ሊሆን ይችላል።

ትራፊክን ደህንነቱ በጠበቀ መንገድ በዞኑ እንዲያልፉ ለማድረግ፣ በአብዛኛው እንደ ቋሚ ወይም ተንቀሳቃሽ ምልክቶች፣ ተለዋዋጭ የመልእክት ምልክቶች፣ የቀስት ክፍሎች፣ የአስፋልት (ፔቭመንት) ስላቶች/ማርኪንግስ፣ እና/ወይም የመምርያ መሳርያዎች (ኮኖች፣ ከበሮዎች፣ መዝጊያዎች፣ መከልከያዎች፣ ወዘተ) የመሳሰሉ ጊዚያዊ መሳርያዎች ይተከላሉ። በስራ ዞን አከባቢ ያሉ የትራፊክ ማስጠንቀቂያ ምልክቶች በአብዛኛው **ብርቱካናማ** ናቸው።

ወደ ስራ ዞን ሲቀርቡ ወይም ሲያልፉ፣ ተቀያያሪ የትራፊክ አካሄዶች እና ፍጥነታቸው የቀነሰ ወይም የቆሙ ተሽከርካሪዎች ሊኖር ስለሚችል ይጠንቀቁ። በመጠምዘዣ ወይም በዳገት ላይ የቆሙ ተሽከርካሪዎች ተደብቀው ሊኖሩ ይችላሉ። በስራ ዞን ደህንነቱ በጠበቀ አኳሃን ሊመርዎት የተቀመጡትን እንደነ ኮኖች፣ ከበሮዎች፣ መዝጊያዎች፣ መከልከያዎች፣ ወይም ስላቶች/ማርኪንግስ የመሳሰሉ የትራፊክ ምልክቶች እና ሌሎች መሳርያዎች በጥሞና መከታተል ያስፈልጎታል። የፖሊሶች እና የምልክት ሰጪዎች (ፍላገርስ) መመርያን ይከተሉ።

- ከፊት ለፊቶ ያለ የመስመር (ሌን) መዘጋቶች ምልክት ካዩ፣ ከተዘጋው መስመር (ሌን)ለመቀየር ይዘጋጁ
- የተቀነሰውን ፍጥነት ገደቦችን ይመልከቱ
- ሌሎች ነጂዎች የሚያደርጉትን ይታዘቡ፣ የድንገት እንቅስቃሴዎች ከማድረግም ይቆጠቡ። ከአንድ መስመር (ሌን) ወደ ሌላ መስመር (ሌን) ደጋግመው አይቀያይሩ። ከኋላቸው ላሉ ነጂዎች ፍጥነታቸው እንዲቀንሱ በቂ ጊዜ ለመስጠት ቀስ በቀስ ፍሬን ይያዙ። የትራፊኩን ፍሰት ጋር ተመሳስለው ይሂዱ።
- እንደነ ሻካራ ስፍራ፣ የብረት ሠሌዳዎች፣ በመስመሮች (ሌኖች) መካከል የሚገኙ ያልተደላደሉ አስፋልቶች (ፔቭመንት)፣ እና በአስፋልቱ (ፔቭመንት) ጫፍ ላይ የሚገኙ የወዳደቁ ነገሮች የሚያጠቃልል ያልተለመዱ ያልሆነ የአስፍልት (ፔቭመንት) ሁኔታዎችን ይጠንቀቁ። ተሽከርካሪዎን ለመቆጣጠር በጣም አዳጋች ሊያደጉ ይችላሉ። በእንደነዚህ ሁናቴዎች፣ ቀስ በቀስ የሚደረግ፣ ሊቆጣጠሩት የሚችሉ እንቅስቃሴዎች ማድረግ በጣሙን ያስፈልጋል።
- በተሽከርካሪዎች መካከል ምክንያታዊ ፍጥነት እና ክፍተት ይኑርዎት። በጣም በፍጥነት እየተጓዙ ከሆነ ወይም በጣም በቅርበት እየተከተሉ ከሆነ፣ ከፊትዎ ያለው ተሽከርካሪ በድንገት ፍጥነቱን ቢቀንስ ወይም ቢቆም የሚሄዱበት ቦታ አይኖርም።
- ትዕግስት ይኑርዎት፣ በተጨማሪ የሰራተኞች እና ሌሎች የመንገዱ ተጠቃሚዎችን ፍላጎት ግምት ውስጥ ያስገቡ። አንዳንድ ጊዜ፣ በስራ ዞን ያለ ትራፊክ መቆም ይኖርበታል። ይሌ በአብዛኛው የሚሆነው፣ ከተቃራኒ አቅጣጫ የሚመጣ ትራፊክ አንድ መስመር (ሌን) ተጠቅሞ ተራ መውሰድ ካለበት፣ ሰራተኞቹ ወይም መሳርያ ትራፊክ ወዳለበት መስመር (ሌን) መግባት ካለባቸው፣ ወይም አንዳንድ እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ለሚያልፉ ተሽከርካሪዎች አደገኛ ከሆኑ ነው። እንደዚህ በሚሆንበት ጊዜ፣ ጊዚያዊ የትራፊክ ምልክቶች ሊደረጉ ይችላሉ፣ ወይም ደግሞ ፖሊስ ቆሞ ለትራፊኩ መመርያ ሊሰጥ ይችላል። በአብዛኛው፣ ቁም/ቀስ በል የሚል ምልክት (STOP/SLOW paddles) ያነገቡ፣ የሰለጠኑ እና ሰርቲፋይድ የሆኑ (መመዘኛ ያለፉ) ምልክት ሰጪዎች፣ ትራፊክን በስራ ዞኖች የማስቆም፣ ፍጥነት እንዲቀንሱ የማድረግ እና/ወይም የማሳለፍ ስራ ይሰራሉ።

EXIT 1
NORTH
1
395
NORTH
14th Street
National Mall
Capitol Hill
Verizon Cntr
Nationals Park

ማሳያዎች/ሲግናሎች፣ ምልክቶች እና ስላቶች/ማርኪንጎች

የመቆጣጠሪያ ምልክቶች

እነዚህ ምልክቶች፣ ነጂዎችን የፍጥነት ገደቦች፣ እና ሌሎች ህጎች እና መመርያዎች በተመለከተ የሚያሳዩ ናቸው። በስራ ቦታዎች የፍጥነት ገደቦች ሊቀንሱ ይችላሉ።

የማስጠንቀቅያ ምልክቶች

የማስጠንቀቅያ ምልክቶች፣ ነጂዎችን በስራ ቦታ ላይ ወይም በስራ ቦታ አቅራቢያ ሊከሰቱ ስለሚችሉ ያልተለመዱ ወይም አደገኛ ሊሆኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን ያስጠነቅቃሉ። አብዛኛዎች በሀይዌዮች እና መንገዶች ስራ ቦታዎች የሚጠቀሙ ምልክቶች ብርቱካንማ እና የዳይመንድ ቅርጽ አላቸው።

የመምርያ መሳርያዎች

መከለያዎች፣ ኮኖች እና ከበሮዎች፣ ነጂዎችን በስራ ቦታዎች ደህንነትን በጠበቀ አኳሃን ለመምራት በብዛት የምንጠቀምባቸው መሳርያዎች ናቸው። በምሽት በደንብ እንዲታዩ ተብሎ የማስጠንቀቅያ መብራቶች ሊደረጉባቸው ይችላሉ።

የሚቀያየር መልእክት የሚያሳዩ ምልክቶች

እነዚህ፣ ስለ መንገድ ሁኔታዎች፣ የትራፊክ ችግሮች፣ የድንገተኛ(ኢመርጀንሲ) ሁኔታዎች፣ ልዩ ዝግጅቶች እና ወዘተ የሚጠቁሙ የተለያዩ መልዕክቶች ሊያሳዩ የሚችሉ የኤሌክትሮኒክ ምልክቶች፣ በብዛት ነጂዎችን በስራ ዞኖች ሊኖሩ የሚችሉ ልዩ ሁኔታዎች ለባለሞተሪስቶች ለማስጠንቀቅ ይጠቅማሉ።

የቀስት ፓነሎች

የቀስት ፓነሎች፣ ነጂዎችን በቀንና በማታ አስፈላጊ ከሆነ ወደ ግራ ወይም ቀኝ በኩል ወዳለው መስመር (ሌን) እንዲቀይሩ አስቀድሞ ለማስጠንቀቅና የአቅጣጫ መረጃ ለመስጠት ይጠቅማሉ።

የትራፊክ ማሳያዎች/ሲግናሎች

የትራፊክ ማሳያዎች/ሲግናሎች፣ ለሁሉም በመንገድም ይሁን በሃይዌይ ለሚራመዱ፣ ለሚነዱ ወይም ብስክሌት ለሚነዱ የሚመለከቱ ናቸው። የማሳያዎች/ሲግናሎች መልዕክትን አለመታዘዝ ዋነኛ የአደጋዎች መንስኤ ነው። አንድ በትራፊክ መቆጣጠርያ መሳርያ ወደሚቆጣጠረው መገናኛ መንገድ እየቀረበ ያለ ነጂ፣ የትራፊክ መቆጣጠርያ መሳርያ መመርያ ላለመከተል ብሎ፣ በእንደ ነዳጅ ማደያዎች፣ የሱቆች ማቆምያዎች እና ወዘተ በመሳሰሉ የግል ንብረቶች ተሻግሮ መንዳት አይፈቀድለትም።

የትራፊክ ማሳያዎች/ሲግናሎች፣ በአብዛኛው ከላይ ወደታች ወይም ከግራ ወደ ቀኝ ቀይ፣ ቢጫ እና አረንጓዴ ናቸው። በአንዳንድ መገናኛ መንገዶች አንድ ቀይ፣ ቢጫ ወይም አረንጓዴ መብራቶች ብቻ ሊኖሩ ይችላሉ። አንዳንድ የትራፊክ ማሳያዎች/ሲግናሎች የጸኑ ሲሆኑ አንዳንዱ ግን ብልጭ ድርግም የሚሉ ናቸው። አንዳንዱ ክብ ሲሆኑ አንዳንዱ ደግሞ ቀስቶች ናቸው። ወደ መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) መንገድ ሲደርሱ የትራፊክ መብራቶች ወይም መቆጣጠርያዎች ከስራ ውጪ የሆኑ ወይም በአግባብ እየሰሩ ያልሆኑ እንደሆነ፣ በማቆምያ ምልክት ባለበት እንደሚቆሙት በመገናኛ መንገዱ ሙሉ በሙሉ መቆም እንዳለብዎት ህጉ ያዛል። በመቀጠል፣ በትራፊክ መኮንን እንዲቀጥሉ ካልተነገርዎት በስተቀር፣ በቅድሚያ መስጠት ህግ መሰረት መቀጠል ይኖርቦታል።

የጸና ቀይ ማሳያ/ሲግናል

ይቁሙ። የማቆምያ መስመር ካለ መስመሩ ላይ፣ ወይም ወደ መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) መንገዱ ከመድረስዎ በፊት ሙሉ በሙሉ ይቁሙ። ካልሆነ፣ ማቋረጫ ቦታው ከመግባትዎ በፊት በመቆም፣ ማሳያው/ሲግናሉ ቀይ እስከሆነ ድረስ ቆመው ይጠብቁ። በመገናኛ መንገዱ ላይ “በቀይ መታጠፍ አይፈቀድም” (“No Turn on Red”) የሚሉ የተለጠፉ ምልክቶች ከሌሉ፣ በቀይ መብራት ላይ ሙሉ በሙሉ ከቆሙ በኋላ ወደ ቀኝ መታጠፍ ይችላሉ። በቀይ መብራት ሲታጠፉ ለእግረኞች፣ ብስክሌት ለሚነዱ እና ለሁሉም ሌሎች ትራፊኮች ቅድሚያ መስጠት ይኖርቦታል። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ በቀይ መብራት ወደ ግራ መታጠፍ በህግ የተከለከለ ነው።

የጸና ቢጫ ማሳያ/ሲግናል

ይሔ ማለት፣ ማሳያው/ሲግናሉ ከአረንጓዴ ወደ ቀይ እየተቀየረ ነው ማለት ነው። አላማው፣ መብራቱ ወደ ቀይ ከመቀየሩ በፊት ወደ መገናኛው(ኢንተርሴክሽን) መንገድ በኩል ሲጓዙ የነበሩ ተሽከርካሪዎች ደህንነቱ በጠበቀ መልኩ እንዲቆሙ እና ሌሎቹ ተሽከርካሪዎች ከመገናኛው(ኢንተርሴክሽን) መንገዱ እንዲወጡ ጊዜ ለመስጠት ነው።

የጸና አረንጓዴ ማሳያ/ሲግናል

መጀመርያ ሌሎች ተሽከርካሪዎች በመጋጠሚያ መንገዱ እንደሌሉ ካረጋገጡ በኋላ፣ በጥንቃቄ ይቀጥሉ። ለመቀጠል አመቺ ሲሆን በቀጥታ ወደ ፊት ለመሄድ ወይም፣ መታጠፍን የሚከለክል ምልክት ወይም ተጨማሪ ማሳያ/ሲግናል ከሌለ በስተቀር፣ ለመታጠፍ ወደ መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) መንገዱ መግባት ይችላሉ። በመገናኛ(ኢንተርሴክሽን) መንገዱ ላሉ እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት ይኖርቦታል።

የጸና ቀይ ቀስት ማሳያ/ሲግናል

ይቁሙ። ወደ መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) መንገዱ፣ ማቆምያ መስመር ወይም በቀስቱ የተመለከተ የመሻገሪያ መንገድ አቅጣጫ ከመድረስዎ በፊት ሙሉ በሙሉ ይቁሙ። የቀስቱ ማሳያ/ሲግናል ቀይ እስከሆነ ድረስ ቆመው ይጠብቁ።

የጸና ቢጫ ቀስት ማሳያ/ሲግናል

ልክ እንደ የጸና ቢጫ ማሳያ/ሲግናል፣ ቢጫ ቀስት ማለት ማሳያው/ሲግናሉ ከአረንጓዴ ወደ ቀይ እየተቀየረ ነው ማለት ነው። አላማው፣ መብራቱ ወደ ቀይ ከመቀየሩ በፊት ወደ መገናኛው(ኢንተርሴክሽን) መንገድ በኩል ሲጓዙ የነበሩ ተሽከርካሪዎች ደህንነቱ በጠበቀ መልኩ እንዲቆሙ እና ሌሎቹ ተሽከርካሪዎች ከመገናኛው(ኢንተርሴክሽኑ) ከመንገዱ እንዲወጡ ጊዜ ለመስጠት ነው።

የጸና አረንጓዴ ቀስት ማሳያ/ሲግናል

ቀስቱ ወደሚያመለክተው አቅጣጫ በጥንቃቄ ይቀጥሉ። በመገናኛ(ኢንተርሴክሽን) መንገዱ ላሉ እግረኞች እና ተሽከርካሪዎች ቅድሚያ መስጠት እንዳለቦት ያስታውሱ።

ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ ማሳያ/ሲግናል

ሙሉ በሙሉ መቆም ይኖርቦታል፣ ለሌሎች ትራፊኮች እና እግረኞች ቅድሚያ ይስጡ። መንገዱ ነጻ ሲሆን ይቀጥሉ።

በባቡር ሃዲድ ማቋረጫ ያለ ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ ማሳያ/ሲግናል

ከደወሎች ጋር አብሮ ሊሆን የሚችል ብልጭ ድርግም የሚል ቀይ ማሳያ/ሲግናል፣ ባቡር እየመጣች እንደሆነ የሚያስጠነቅቅ ነው። ባቡርዋ እስክትሄድ ድረስ እና በተቃራኒው የባቡር ሃዲድ መንገድ ሌላ ባቡር እየመጣች እንዳልሆነ እስኪያረጋግጡ ድረስ መቆም ይኖርቦታል።

ምንም የማስጠንቀቅያ ሲስተም (እንደ ብልጭ ድርግም የሚሉ መብራቶች ወይም መዝጊያዎች) ወደ ሌሉበት የባቡር መሻገርያ መንገድ ሲደርሱ፣ ፍጥነታቸው በመቀነስ የምትመጣ ባቡር ያለች እንደሆነ መመልከትና መስማት፣ እየመጣች ያለ እንደሆነ ደግሞ የባቡር ሃዲድ መንገዱ ጋር ከመድረስዎ በፊት መቆም ይኖርቦታል። ባቡሮች ሁሌ የሚጓዙት፣ እኛ ከርቀት ከምንታዘበው ፍጥነት በበለጠ ነው፣ ስለዚህ ነጂዎች በፍጹም ባቡርን እቀድማለሁ ብለው መሞከር የለባቸውም። ነጭ “X” እና “RR” የሚሉ ፊደሎች ያሉዋቸው የመንገድ ምልክቶች/ማርኪንጎች የባቡር ሃዲድ መንገድ ሊያቋርጡ እንደቀረቡ እና በፍጥነት መቆም የማይችሉትን ባቡሮችን መከታተል እንዳለቦት የሚያስጠነቅቆት ናቸው።

ብልጭ ድርግም የሚል ቢጫ ማሳያ/ሲግናል

ፍጥነትዎን በመቀነስ በጥንቃቄ መቀጠል አለብዎት።

የተለያዩ ማሳያዎች/ሲግናሎች

ማሳያዎቹ/ሲግናሎቹ፣ ትራፊክ በአረንጓዴ መብራት ወደ ግራ መታጠፍን ለመፍቀድ ይጠቅማሉ።

የመስመር (ሌን) አጠቃቀም ማሳያዎች(ሲግናሎች)

ማሳያዎቹ/ሲግናሎቹ፣ በተለያዩ ሰዓታት ላይ የመስመሮቹ (ሌኖቹ) አቅጣጫ በተቃራኒው በማድረግ፣ የትራፊክ ፍሰት ለመቆጣጠር ይጠቅማሉ። መስመሮቹ (ሌኖቹ) እና አቅጣጫዎቻቸው በምልክት እና በማሳያዎች/ሲግናሎች ሊደረግባቸው ይችላል። ቀይ “X” ምልክት ባለው መስመር(ሌን) በፍጹም መንዳት የለብዎትም። አረንጓዴ የቀስት ማሳያ/ሲግናል ባለበት መስመር (ሌን) መንዳት ይፈቀድሎታል። የጸና ቢጫ “X” ማሳያ/ሲግናል ማለት፣ ነጂው ደህንነቱ በጠበቀ መንገድ ከመስመሩ (ሌኑ) በተቻለው ፍጥነት፣

መውጣት አለበት ማለት ነው። ብልጭ ድርግም እያለ የሚያበራ ቢጫ “X” ማሳያ/ሲግናል ማለት ነጂው መስመሩን (ሌኑን) ተጠቅሞ ወደ ግራ መታጠፍ ይችላል ማለት ነው። መስመሩ (ሌኑ) በተቃራኒ አቅጣጫ ከሚመጡ ወደ ግራ የሚታጠፉ ተሽከርካሪዎች ጋር የመጋራቱ ዕድል የበዛ ነው።

ምልክቶችን በቀለማት እና በቅርጾች መለየት

ምልክቶችን በቅርጻቸው፣ ቀለማቸው እንዲሁም ላያቸው ባሉት ቃላት፣ ቁጥሮች ወይም ምስል ይለዩዋቸው።

የምልክት ቀለሞች

የመንገድ ምልክት ቀለም ልክ ሲያዩት ምን አይነት መረጃ ሊሰጦት እንደሆነ ሊነግሮት ይችላል።

ቀይ

ቁም፣ ቅድሚያ ስጥ፣ እዚህ አትግባ፣ ወይም የተሳሳተ መንገድ ነው።

ቢጫ

እንደ ትምህርት ቤት ወይም የሚሻገሩ እግረኞች የመሳሰሉ ከፊት ሊመጣ ስላለው ነገሮች ጠቅላላ ማስጠንቀቂያ

ነጭ

የፍጥነት ገደብ ወይም የማቆሚያ(ፓርኪንግ) መመሪያን የመሳሰሉ የመቆጣጠሪያ ምልክቶች

ብርትኳንማ
የግንባታ እና እደሳ ስራ ቦታዎች ማስጠንቀቂያ

አረግኛዴ
እንደ ርቀት ወይም አቅጣጫ የመሳሰሉ የመምሪያ መረጃ

ሰማያዊ
የሞተረኞች አገልግሎቶች

ቡናማ
የመዝናኛ እና የባህላዊ ቦታዎች



የምልክት ቅርጾች

የትራፊክ ምልክት ቅርጽ ልክ እንደ ቀለሙ ያህል የምልክቱን መልእክት ይነግሮታል። እንደ ከፍተኛ ጭጋግ በመሳሰለ መጥፎ እይታ ባለበት፣የምልክቱን ቅርጽ ብቻ ሊለዩት ይችሉ ይሆናል።

ስምንት መአዘን(ኦክታጎን): ቁም

ኦክታጎን (ስምንት-ጎኖች) ቅርጽ ሁልግዜም ቁም ማለት ነው። ምልክቱ ላይ፣ የማቆሚያ መስመር ላይ፣ እግረኛ ሲሻገር ወይም መገናኛው ውስጥ ከመግባቶ በፊት ሙሉ በሙሉ ማቆም አለቦት።

ሶስት መአዘን: ያሳልፉ

ያቀዝቅዙ ወይም አስፈላጊ ከሆነ ያቁሙ እና መንገዶን የሚያልፍን ተሽከርካሪ ቅድሚያ አግኝቶ ማልፍ መብቱን ይስጡት።

ዳይመንድ: ማስጠንቀቂያ

እነዚህ ምልክቶች ከፊቶ ያለን ልዩ ሁኔታዎችን ወይም አደገኛ ሁኔታዎች ያስጠቀቅቆታል። ማቀዝቀዝ ሊሆሩቦት ይችላል ስለዚህ ይዘጋጁ።

አራት ማእዘን: ደንቦች ወይም መምሪያ
ከላይ ወደታች(ቨርቲካል) ምልክቶች ባጠቃላዩ መመሪያዎችን ለመስጠት ወይም ህጎቹን ሊነግሮት ይጠቅማሉ። ወደጎን(ሆሪዞንታል) ላሉት፣ ምልክቶቹ አቅጣጫዎችን ወይም መረጃዎችን ይሰጡ ይሆናል።

ፔንታጎን(አምስት መአዘን): ትምህርት ቤት እና ትምህርት ቤት መሻገሮች
ፔንታጎን (አምስት ጎን) የትምህርት ቤት ዞኖችን ያስጠነቅቆታል እና ለትምህርት ቤት መሻገሪያዎችን ምልክት ይሆናል።

ክብ: የባቡር ሀዲድ ማስጠንቀቂያ
ጥቁር እና ቢጫ የባቡር ሀዲድ ከፊት ለፊት እንደሚያቋርጥ ለማስጠንቀቅ ብቻ ይጠቅማል።

INTERSTATE
695
TO
INTERSTATE
395
Capitol Hill

የመቆጣጠሪያ ምልክቶች

ቁም

ቁም የሚል ምልክት ጋር ሲደርሱ፣ የማቆሚያው መስመር ላይ ሙሉ በሙሉ ማቆም አለቦት። የማቆሚያ መስመር ከሌለ፣ ከእግረኛ መሻገሪያው በፉት ያቁሙ። የእግረኛ መሻገሪያ ከሌለ፣ ቁም የሚለው ምልክት ከተለጠፈበት በፊት ያቁሙ። ከመቀጠሎ በፉት መሻገሪያው ላይ ላሉ ለማንኛውም እግረኛ ወይም ብስኪሌት ቅድሚያ መስጠት አለቦት። መሻገሪያው መፅዳቱን ካረጋገጡ በሃላ፣ በመገናኛው ከማለፎት በፊት መንገዱ ከተሽከርካሪዎች እንደፀዳ ለማረጋገጥ በጥንቃቄ ይቀጥሉ።

ያሳልፉ

ያሳልፎ የሚል ምልክት ጋር ሲጠጉ ያቀዝቅዙ። ወደ ግራ ይመልከቱ፣ ወደ ቀኝ ይመልከቱ፣ ከዚያ መልሰው ወደ ግራ ይመልከቱ። ለማንኛውም እግረኛ፣ ባለብስክሊት ወይም ተሽከርካሪ ቀድሞ የማለፍ መብትን መስጠት አለቦት። በደህና ማለፍ ሲችሉ ሊቀጥሉ ይችላሉ።

የፍጥነት ገደብ

አነዚህ ምልክቶች ትራፊክን ለመቆጣጠር የሚጠቅሙ ናቸው። ይሄ ምልክት ለተለጠፈበት የጎዳና ርቀት በሙሉ ከፍተኛውን የፍጥነት ገደብ ይነግሮታል።

ማቆም(ፓርኪንግ)

ማቆምን(ፓርኪንግን) የሚያግዱ ብዙ ምልክቶች አሉ።

ከላይ ያሉ መስመር(ሌን) አጠቃቀሞች

እነዚህ ምልክቶች መገናኛ(ኢንተርሴክሽን) ላይ ከአንድ የተወሰነ መስመር(ሌን) ላይ መታጠፍ ግዴታ የሚሆኑበትን ወይም ያልተለመዱ መታጠፉያዎች የተፈቀዱበትን ለማሳየት ይጠቅማሉ።

ከፍተኛ ይዞታ ያለው ተሽከርካሪ

ይህ ምልክት የተጠቆሙት መስመር(ሌን) ወይም መስመሮች(ሌኖች) ቢያንስ በምልክቱ ላይ የተጠቀሰውን ያህል ባለይዞታ ላላቸው ባሶች እና ተሽከርካሪዎች ብቻ የተመደበ ነው ማለት ነው።

አጥብቦ (ሻርፕ) ወደ ቀኝ መታጠፍ
ከፊት ባለው መንገድ ላይ አጥብቦ(ሻርፕ) ወደ ቀኝ መታጠፊያ አለ።

ቀኝ ከርቭ(መጠምዘዣ)
ከፉት ወደ ቀኝ ከርቭ አለ።

አጥብቦ(ሻርፕ) ወደ ቀኝ እና ግራ መታጠፊያዎች
ከፊት ያለው መንገድ አጥብቦ ወደ ቀኝ ከዚያ ወደ ግራ ይታጠፉል።

የማስጠንቀቂያ የትራፊክ ምልክቶች

አብዛኛዎቹ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ቢጫ እና ጥቁር ናቸው እና ብዙዎች የዳይመንድ ቅርጽ አላቸው። ቀስ ያድርጉት እና ተከትለው ሊመጡ የሚችሉትን ሌሎች ምልክቶች ወይም መጠቆሚያዎችን ይከታተሉ።

ከፊት ለፊት የመቆሚያ (STOP) ምክልት

ቀስ ያድርጉት እና ከፉት ለፉት መቆሚያው ምልክት ላይ ለማቆም ይዘጋጁ።

የ4- መንገድ መቆሚያ (STOP)

ይህ ምልክት መገናኛው(ኢንተርሴክሽኑ) ላይ አራት የማቆም (STOP) ምልክቶች አሉ ማለቱ ነው። ከሁሉም አቅጣጫ የሚመጣ ትራፊክ መቆም አለበት። የመጀመሪያ ያቆመው ነጂ፣ መጀመሪያ የሚሄደው ነጂ ይሆናል። ሌሎች ነጅዎች ተራቸውን መጠበቅ አለባቸው። እንዲሁም 3-በኩል (3-WAY)፣ 5-በኩል (5-WAY) ወይም በሁሉም በኩል (ALL-WAY) የሚሉ ምልክቶች ሊያዩ ይችል ይሆናል።

ከፊት ለፊት ምልክት

ቀስ ይበሉ እና ከፊት ለፊት ያለው ምልክት ላይ ለማቆም ይዘጋጁ።

ከፊት ለፊት ያሳልፉ የሚል ምልክት

ቀስ ይበሉ እና ያሳልፉ የሚለው ምልክት ላይ ለማቆም ይዘጋጁ ወይም ፍጥነቶን ከትራፊኩ ፍሰት ጋር አመሳስለው ያስተካክሉ።

ጠመዝማዛ መንገድ

ከፊት ለፊት ያለው መንገድ በሚከታተሉ ከርቮች(መጠምዘዣዎች) እና መታጠፊያዎች ይጠማዘዛል። ፍጥነቶትን ያስተካክሉ።

የጎን መንገድ

የጎን መንገድ ሀይዌው ውስጥ ከቀኝ በኩል ይገባል። ወደ ጎን መንገዱ የሚገቡ ወይም የሚወጡ ተሽከርካሪዎችን ለማየት እንዲችሉ ፍጥነቶትን ያስተካክሉ።

መስቀለኛ መንገድ

ሀይዌውን ከፉት ሌላ መንገድ ያቋርጠዋል። የሚያቋርጥ ትራፊክን ወይም የመቆጣጠሪያ ምልክቶችን ወይም ማሳያዎችን(ሲግናሎችን) ነቅተው ይጠብቁ።

ማለፍ አይቻልም ፔናንት(ጫፍ ያለው ተውለብላቢ ባንዲራ)

የፔናንት ቅርጽ ያለው፣ ማለፍ አይቻልም (DO NOT PASS) የሚለውን የደንብ ምልክት ይደግፈዋል። ፔናንቱ በመንገዱ በግራ በኩል የሚደረግ ሲሆን ማለፍ የማይቻልበት ዞኑን መጀመሪያ ያመለክታል።

የመውጫን ፍጥነት ማሳወቂያ

ለመግባት ወይም ለመውጣት ደህነትን የሚያስጠብቅው ከፍተኛው ፍጥነት።

የሚጋጠም

ከቀኝ የሚጋጠም ትራፊክ ልክ ከፊት ለፊቶ አለ።

ትምህርት ቤት የእግረኛ መሻገሪያ

ትምህርት ቤት መሻገሪያ፣ ቀስ ይበሉ፣ እግረኞች ካሉ ለመቆም ይዘጋጁ።

“T” መገናኛ(ኢንተርሴክሽን)

መንገዱ ከፊት ለፊቶ ያበቃል። ቀስ ይበሉ እና ከመታጠፎ በፊት ለመቆም ወይም ቅድሚያ ለመስጠት ይዘጋጁ።

የፍጥነት ማሳወቂያ

ሀይዌው የተወሰነ ርቀት ድረስ ይሄ ከፍተኛው ደህንነትን የሚያስጠብቅ ፍጥነት ነው እና ሌሎች ማስጠንቀቂያ ምልክቶች ላይም ተለጥፏል። ፍጥነቶትን ወደሚታየው የፍጥነት ማሳወቂያ ድረስ ዝግ ያድርጉ።

“Y” መገናኛ (ኢንተርሴክሽን)

ከፊት ለፊቶ ቀኝን ወይም ግራን መያዝ አለቦት። ቀስ ይበሉ እና የትራፊክ ፍሰቱን በንቃት ይጠብቁ።

የሚከፋፈል ሀይዌይ ይጀምራል

ቀኝን ይዘው ይቆዩ

ወደ ግራ ይቀላቀሉ

የቀኙ መስመር(ሌን) ከፊት ለፊቶ ያበቃል

የተከፋፈለው ሀይዌይ ከፊት ለፉት ያበቃል

ከፊት ለፊት ከፍተኛ አቀበት

ብስኪሌት እያቋረጠ ነው/የባይክ መንገድ

በጥንቃቄ ይንዱ

እርጥብ ሲሆን የሚያንሸራትት መንገድ፣ ፍጥነት ይቀንሱ

የዝናብ የመጀመሪያው ግማሽ ሰአት ከሁሉ የበለጠ አደገኛ ነው።

የጎዳና (ራውት) መለያዎች(ማርከርስ)

እንስሳት እየተሻገረ ነው

እነዚህ ቦታዎች ላይ በምልክቱ ላይ ያለው የእንስሳት የተለመደ ነው፣ በተለይ ሲነጋጋ፣ ሲጨላልም እና በለሊት(ምሽት) ሰአታት መንገዱን ለሚሻገሩ ለነዚህ ዝርያዎች ይጠንቀቁ።

የመታጠፊያ ምልክቶች፣ የድንገተኛ ግዜ(ኢመርጅንሲ ምልክቶች) እና የእጅ ምልክቶች

ሊታጠፉ መሆኑን ለማሳየት የእጅ ምልክቶችን ወይም የአቅጣጫ ምልክቶችን መጠቀም አለቦት። የመታጠፉያ ምልክቶች መስመሮችን ሲቀይሩ ወይም ተሽከርካሪን ሲቀድሙ አስፈላጊ ናቸው። ከሃላዎት ያሉን ነጂዎች ማለፍ ይችላሉ ብሎ ለመንገር የመታጠፉያ ምልክቶችን መጠቀም ህጉን የሚጻረር ነው። የሀዛርድ መብራቶች ተሽከርካሪዎ ቆሞ ሳለ ወይም ሀይዌው ላይ ሲበላሽ ወይም በድንገተኛ(ኢመርጀንሲ) ወቅት የመንገዱ የጎን ቦታ(ሾልደር) ላይ በሚሆንበት ወቅት ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው። ቢስኪሊቶች እንቅስቀሴያቸውን ለሌላ ነጅዎች ለማሳወቅ የእጅ ምልክቶችን ይጠቀማሉ።

እግረኞች እየተሻገሩ ነው

እግረኞች እየተሻገሩ ነው፣ ይመልከቱ እና እግረኞች ካሉ ለማቆም ይዘጋጁ።

ቀስ ብሎ የሚሄድ ተሽከርካሪ

በሁለት መንገድ የሚሄድ ትራፊክ

ወደ ቀኝ መታጠፍ አይቻልም

U-ተርን ማድረግ አይቻልም

መግባት አይቻልም

በክልሎች (ስቴቶች) መሀከል ያለው ሲስተም ጋሻ የሚመስል ጎዳና (ራውት) ማሳያ አለው። የላይኛው በነጭ ቀለም እና የጀርባ ቀይ ቀለም ውስጥ INTERSTATE የሚለውን ይይዛል። የታችኛው ሰማያዊ ሲሆን የጎዳናው (የራውት) በትልቁ ነጭ ቀለም የሆነ ቁጥር ነው።

የዩናይትድ ስቴትስ ቁጥር የተሰጣቸው ጎዳናዎች (ራውት) (United States Numbered Routes)(በክልሎች መሀከል ካሉት ጎዳናዎች(ራውቶች) ውጪ) የጀርባ ቀለሙ ነጭ በሆነ በተለመደው የዩ.ኤስ. ጋሻ ውስጥ በሆነ ጥቁር ቀለም ቁጥር ምልክት የተደረጉ ናቸው።

የክልል(የስቴት) ጎዳናዎች(ራውቶች) በነጭ አራት መአዘን ውስጥ በጥቁር ፉደሎች ምልክት የተደረጉ ናቸው።

ዲሲ ራውት (DC Route)

DC 295፣ የአናኮስቲያ ፍሪ ዌይ (Anacostia Freeway) በመባልም የሚታወቀው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ውስጥ ፍሪ ዌይ ነው፣ እና በአሁኑ ወቅት በዲስትሪክቱ ውስጥ በክልሎች መሀከል ያለ ሀይ ዌይ ወይም ዩ.ኤስ. ሀይዌይ ያልሆነ ቁጥር የተሰጠው ብቸኛ ፍሪዌይ ነው።

ማስታወሻ: